

# መጽሐፍ ቅዱሳዊና ጴንጤቆስጣዊ

# ነገረ ልሳን

ዘላለም መንግሥቱ

ማውጫ

መግቢያ

ገጽ 3

ዳራው፥ እኔ ጴንጤ አይደለሁም

ገጽ 4

በልሳናት የመናገርና የመተርጎም ስጦታ፤ ከመቅካቀ ምዕ. 2

ገጽ 7

አሜሪካዊ ክርስትና፥ ኢትዮጵያዊ ነጸብራቅ፥ ስደት፥ እና የአምልኮ ነፃነት
ገጽ 13

የልሳኖች ቀውስ፤ ከመቅካቀ ምዕ. 4

ገጽ 24

መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ጴንጤቆስጣዊ ነገረ ልሳን

ገጽ 40

## መግቢያ

ለዚህች መጽሐፊት መነሻ የሆነው በፌስቡክ ገጼ፥ ‘እኔ ጴንጤ አይደለሁም።’ ብዬ የለጠፍኩት እና ያልሆንኩባቸውን ሦስት ምክንያቶች መጻፌ ያስነሣው የማኅበራዊ ገጽ አቧራ ነው። ይህችን መጽሐፊት ሳሰናዳም አቧራው አልጠፋም። እኔ ጴንጤ አይደለሁም ስል ይህ የመጀመሪያው አይደለም። ይህኛውን ምን እና ለምን ልዩ እንዳደረገው አላውቅም። ከጴንጤነት ይልቅ የገነነው ተያያዥ ቢሆንም የነገረ ልሳን ጉዳይ ነው።







በዚህች ታናሽ መጽሐፊት ከዳራው በመነሣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገረ ልሳንን እና ጴንጤቆስጣዊ ነገረ ልሳንን እዳስሳለሁ። መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ነገረ ልሳን ወይም የልሳን የጸጋ ስጦታን *መንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች* ከተሰኘው፥ 1989 (እኤአ 1996) የታተመ እና ለሁለተኛ እትም እየዳበረ ካለው መጽሐፌ የወሰድኩት ነው። በዚያ መጽሐፍ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነገረ መንፈስ ቅዱስ ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ ውስጥ በአዲስ ኪዳን የተዘረዘሩት የጸጋ ስጦታዎች ሁሉም ተዳስሰዋል። በምዕራፍ ሦስት ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄዎችና እንቅስቃሴዎች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተከሰቱባቸው ታሪክ ክፍል ነው። አራተኛውና የመጨረሻው ደግሞ በካሪዝማዊነት ስም የተፈጠሩ ቀውሶች የተዳሰሱበት ነው። እውነተኛ ፈውስ እንዳለ ሁሉ የፈውስ ቀውስም አለ። እውነተኛ ልሳን እንዳለ ሁሉ የልሳኖች ቀውስም አለ። ከዚያ መጽሐፍ ሁለቱንም የጸጋው ስጦታ የተዳሰሰበትንም ቀውሶቹ የተወሱበትንም ክፍል እዚህ አካፍላለሁ።

በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ጴንጤ እየተባለ የተጠራበት ታሪካዊ ስሕተት ደግሞ *መጽሐፍ ቅዱስ እና የአፈታት ስሕተቶች* በተባለው መጽሐፌ ሁለተኛው እትም 2017 (እኤአ 2025) በመጠነኛ ስፋት የዳሰስኩት ነው። በመንፈስ

*ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች ሦስተኛ ምዕራፍ ስለ ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ በዓለም ዙሪያ የተዳሰሰ ቢሆንም የአገራችን ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ አልተካተተም። ይህኛውም ጠቅላላው እንቅስቃሴ እንጂ አገራዊው ንቅናቄ ጴንጤቆስጣውያን ባልሆኑት በጥልቀት ተጽፎ አላነበብኩም። እኔ ጴንጤ አይደለሁም ለሚለው ዳራ እንዲሆን ግን ያንን ንዑስ ርእስ እዚህም አካፍለዋለሁ።*

## ዳራው፤ እኔ ጴንጤ አይደለሁም።

ከላይ ላልኩት የማኅበራዊ ሚድያ አቧራ መነሣት ምክንያት የሆነችው Feb. 20, 2026 የጻፍኳት አጭር ጽሑፍ ይህች ናት።

> እኔ ወንጌላዊ አማኝ ነኝ፤ ጴንጤ አይደለሁም። ከዚህ በፊት እንደመሰከርኩት የእምነቴን መግለጫ አልፎ አልፎ እናገራለሁ ወይም እምነቴን እገልጣለሁ። ይህኛውን ከዚህ በፊት ብዬዋለሁ፤ አሁንም እደግማለሁ።
>
> ጴንጤ አይደለሁም ማለት ጴንጤቆስጣዊ አይደለሁም ማለት ነው። በአገራችን አማኞችን 'ጴንጤ' ብሎ መጥራት በአንድ ወቅት የተፈጸመ ታሪካዊ ስህተት ነው። ወንጌአላዊ አማኝና እና ጴንጤቆስጣዊ ሰው የተለያዩ ናቸው። ይህ መታወቅ አለበት።
>
> ጴንጤቆስጣዊ ማለት በአዲሱ ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ የመጣው፥ የጴንጤቆስጤው ቀን ክስተት ዛሬም ይደገማል፤ አንድ ሰው ዳግም ከተወለደ በኋላ፥ ወይም ጌታን ተቀብሎ ካመነና ከዳነ በኋላ ቆይቶ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃል፤ ከድነት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ሲጠመቅ የመጠመቁ ምልክትም በልሳን መናገር ነው ብሎ የሚያስተምር የስህተት ትምህርት ነው።
>
> ይህ ትምህርት ስሕተት መሆኑን ላሳይ። ሦስት ስሕተቶች ናቸው በዝርዝር።
>
> አንደኛ፥ የጴንጤቆስጤ ድግግሞሽ
>
> ጴንጤቆስጤ በአማርኛ በዓለ ኀምሳ የተባለው ቀን ነው። ያ ቀን መንፈስ ቅዱስ የወረደበት እና ቤተ ክርስቲያንም የተወለደችበት የልደቷ ቀን ነው። የጴንጤቆስጤው ቀን ክስተት የሚደጋገም ከሆነ ዛሬም መንፈስ ቅዱስ በወረደ ቁጥር እንደሚነጥቅ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምጽ መሰማትና፥ እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳናኖች መታየት ነበረባቸው። ወይም ያንን የሚመስሉና የሚተኩ ምልክቶች መሰማትም መታየትም ነበረባቸው። በተያያዥ በዚያ ቀን እንደሆነው ያለ በሚታወቁ ቋንቋዎች የእግዚአብሔርን ድንቅ ነገር፥ ማለትም ላልዳኑ ሰዎች የጌታን ማዳን በቋንቋቸው

የሚናገሩ ሰዎች መኖር ነበረባቸው። ይህ ሆኖ አያውቅም። ስለዚህ፥ የጴንጤቆስጤው ቀን ክስተት የማይደጋገም ነውና ይደጋገማል የሚለው ትምህርት የስሕተት ትምህርት ነው።

ሁለተኛ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

ጴንጤቆስጣውያን አንድ ሰው ከዳነ በኋላ፥ ጌታን ተቀብሎ ድነትን ካገኘ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ይጠበቅበታል፤ የመጠመቁ ምልክትም በልሳን መናገሩ ነው' ይላሉ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ይህ ጥምቀት ካልተከናወነ ያ ሰው አልዳምም ይላሉ። ይህ በጣም ግልጽ የስህተት ትምህርት ነው። ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቀው ጌታን በተቀበለና በዳነ፥ ወደ ክርስቶስ አካል በገባና የአካሉ፥ የቤተ ክርስቲያን ብልት በሆነ ጊዜ ነው። 1ቆሮ. 12፥13 እንዲህ ይላል፥ አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።

ከዚህ በጣም ግልጽ ምንባብ እንደምንገነዘበው፥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የክርስቶስ አካል ብልት ያደርገናል፥ አንድን አማኝ ከክርስቶስ አካል ጋር አንድ ያደርጋል እንጂ በልሳን አያናግርም። ጎዶሎ መዳንንም ሙሉ አያደርግም። ይህ ጥቅስ የሚለው ልክ ካልሆነና ጴንጤቆስጣውያን የሚሉት ልክ ከሆነ፥ አንድ ሰው ጌታን ተቀብሎ ከዳነ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ እስኪጠመቅ ድረስ የክርስቶስ አካል ክፍል አይደለም። ይህ ሌላው ስህተት ነው።

ሦስተኛ፥ ነገረ ልሳን

ሌላው የጴንጤቆስጣዊነት ስህተት የዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት ነው የሚሉት በልሳን መናገር ነው የሚለው ትምህርት ነው። ይህንን ትምህርት ከማለት ይልቅ ልምምድ ብንለው የተሻለው ቃል ነው። ይህም ትምህርትና ሰው ሠራሽ ልምምድ እጅግ ስሕተት የሆነ ነገር ነው።

ልሳን የጸጋ ስጦታና ከስጦታዎቹም አንዱ ነው። ልክ እንደ ሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ ለአካሉ መታነጽ የተሰጠ፥ መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ የሚሰጠው፥ ለሁሉም ያልሆነ፥ የሚታወቅ ቋንቋ ወይም ጉባኤው የማያውቀው ከሆነ ደግሞ ተተርጉሞ ጉባኤውን ማነጽ ያለበት፥ ካልተተረጎመ ተናጋሪው ለጉባኤ መናገር የሌለበት ቋንቋ ነው።

በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ ልሳን የሚባለው ነገር በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጀመረ የአዲሱ ጴንጤቆስጣዊነት ልምምድ ነው። የልሳኖች ልምምድ ተብሎም

ይታወቃል። ስለዚህ ጉዳይ ከ30 ዓመታት በፊት መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፌ ምዕራፍ 3 በሰፊው ጽፌአለሁ።

ዛሬ ይህ ልሳን የሚባለው ነገር የሰዎች ልምምድ እንጂ የጸጋ ስጦታ አለመሆኑን ነው እዚህ ስሕተት የምለው። በስነ ቋንቋ ሊቃውንት (ክርስቲያኖችም ጭምር) ከቋንቋዎች ጋር ተደባልቀው የተፈተሹና የተገመገሙ ልሳኖችን ዘገባ አንብቤአለሁ፤ አዳምጫለሁ። እነዚህ ልሳን እና ቋንቋዎች ተሰባጥረው የቀረቡላቸው ሊቃውንት የቋንቋ መስፈርትን የማያሟሉትንና የማያሟሉትን በቀላሉ ሲለዩ ልሳናትን ከቋንቋ አልመደቧቸውም። የLinguistics ኮርሶች እንደወሰድው የቋንቋ ተማሪ ምርምሩ ይገባኛል።

በጣም ብዙ የሚሆኑ ሰዎች ልሳኖችን ሰምቼ አውቃለሁ። በጣም ብዙ የሆኑ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ አነጋግሬአለሁ። ካነጋገርኳቸው ውስጥ ብዙዎቹ እንዴት እንደተናገሩት የሚሰጡት መልስ ተመሳሳይ ነው። በአጭሩ በሦስት ቃላት መልሳቸውን ስገድበው መጠባበቅ ወይም መናፈቅ፥ ግፊት፥ እና ልምምድ ናቸው።

ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው። ይህ በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ ልሳን የሚባለው ነገር ደግሞ ቋንቋ ሳይሆን የጥቂት ቃላት ድግግሞሽ ብቻ መሆኑን ነው በቡድናዊ ግፊት እና በልምምድ ምክንያት የተገኘ የሚያስብለው። ከላይ እንዳልኩት የቋንቋ መስፈርትን አያሟላም።

እኔ ከሰማሁዋቸው የልሳን ንግግሮች ውስጥ 99.9% የሚሆኑት የልምምድ ልሳኖች ናቸው። ቋንቋ ያልሆነ ልሳን የቋንቋ መስፈርትን የማያሟላ ልሳን ማለት ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ዛሬ አንድም በሚታወቅ ምድራዊ ቋንቋ የተናገረ፥ ሰውየው የማያውቀው እና ሰሚዎቹ በሚያውቁት የራሳቸው ቋንቋ ተናግሮ ን ክርስቶስን እንዲያውቁ ያደረጋቸው ሰው ገጥሞኝም ሰምቼውም አላውቅም። አንድ ሰው ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ነገር ሲናገር ሰምቻለሁ፤ የተረጋገጠ ፍን አይደለም። መረጋገጥ አለበት እንዴ? ሊባል ይቻላል። አዎ መረጋገጥ አለበት። የሌለ ፈውስ ፈውስ እየተባለ ሲሸጥ ለምንድነው የማይረጋገጠው? የሌለ ብልጽግና ብልጽግና እየተባለ ሲሸጥ ለምንድነው የማረጋገጠው? የሌለ ልሳንስ ቋንቋ እየተባለ ሲቀርብ ለምን አይፈተሽም? መረጋገጥማ አለበት እንጂ! መረጋገጥ አለበት።

ከላይ 99.9% ያልኩት 100% ያላልኩት የፀጋ ስጦታ ተቋርጧል ስለማልል ነው። የጸጋ ስጦታ ካለ ልሳንም ስጦታ ነውና ይኖራል። ይህ ስጦታ እንደ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከኖረ ትክክለኛ ምንነቱ በሌላ ቦታዎች በአዲስ ኪዳን፥ በተለይም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት እንደተጻፈው መቀጠል አለበት። በ1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 14 እንደተጻፈው ቋንቋ ሆኖ፥ የቋንቋ መስፈርቶችን በሙሉ ያሟላ ሆኖ የተገለጠ መሆን አለበት። ለሰሚዎቹ እንግዳ ቋንቋ ከሆነ መተርጎም አለበት።

ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ወይም ደሞ ከቻይንኛ ወደ ስፓኒሽ እንደሚተረጉም ቋንቋ ማለት ነው።

ስደመድም፥ ጴንጤቆስጣዊነት ማለት ልምምድን፥ በተለይም የልሳን ልምምድን የሚያደራጅ እና የሚያሰራጭ ትምህርት በመሆኑ ወንጌላዊ አማኝ እና ጴንጤ የሚለው አጠራር ሞክሼ ማወቅ አለብን። ከዚህ በፊት እንደመሰከርኩት አሁንም እደግማለሁ መግለጫ አልፎ አልፎም ቢሆን እናገራለሁ ወይም እምነቴን እገልጣለሁ።

ዘላለም ነኝ።

በዚያች ጽሑፍ ከተናገርኩት ውስጥ ከጴንጤነትም ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ጎልቶ የወጣው የልሳን ጉዳይ ነው። ልሳን ምንድር ነው? ቀደም ሲል ባልኩት መጽሐፍ፥ *መንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች* ከተሰኘው፥ ስለ ጸጋ ስጦታዎች ስጽፍ ስለ ልሳን ያልኩትን እዚህ ላካፍል።

## በልሳናት የመናገርና የመተርጎም ስጦታ

'ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል።' (1ቆሮ. 12፥10) ልሳን ማለት በተለምዷዊው አማርኛ ቋንቋ አንደበት ወይም የመናገሪያ ብልት ማለት ሲሆን በዚህ ክፍልና በጠቅላላውም በአዲስ ኪዳን እንደምናገኘው ግን በአጭሩ ቋንቋ ማለት ነው። በሌሎች ልሳናት መናገር ማለትም በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ማለት ነው። አንድ ሰው በአንድ ቋንቋ ለመናገር ወይ አፉን በዚያ ቋንቋ መፍታት አለበት ያለዚያም ያን ቋንቋ በትጋት መማር አለበት። አፉን ሳይፈታበት ወይም ሳይማር አንድን ቋንቋ ከተናገረ ያንን ንግግር ያገኘው ከራሱ ውጪ ከሆነ ሌላ ምንጭ ነው ማለት ነው።

ልሳን ወይም በግሪክ ቋንቋ γλῶσσα (ግሎሳ) የሚባለው ቃል በአዲስ ኪዳን 50 ጊዜያት ተጽፏል። ከነዚህ ውስጥ ከፊል ያህሉ 'ልሳን' ሲሰኙ የቀሩት ደግሞ 'መላስ' ለምሳሌ፥ ማር. 7፥33 እና 35፤ ሉቃ. 1፥64፤ 1ጴጥ. 3፥10። 'ቋንቋ' ለምሳሌ፥ ማር. 16፥17 እና ራዕ. 5፥9 ወዘተ። እንዲሁም ' አንደበት' ለምሳሌ፥ 1ቆሮ. 14፥9፤ ያዕ.1፥26 እና 3፥5-8፤ 1ዮሐ. 3፥18፤ ተብለው ተተርጉመዋል። ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ቋንቋዎች በተናገሩባቸው ቦታዎች ማለትም በሐዋ. 2፥4፤ 10፥46 እና 19፥6 'ልሳን' ተብሎ ተጠቅሶአል። በተረፈ ልሳን የሚለውን ቃል ክምችት የምናገኘው በ1ቆሮ. 12-

14ነው። እነዚህም፥ 1ቆሮ. 12፥10፥28 እና 30፤ 1ቆሮ. 13፥1 እና 8፤ 1ቆሮ. 14፥2፥4፥5፥6፥13፥14፥18፥19፥22፥23፥26፥27 እና 39 ናቸው።

በአዲስ ኪዳን በሌሎች ልሳናት መናገር ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱ መሆኑ ተጠቅሷል። ስጦታው 'በአዲስ ቋንቋ መናገር'፥ 'በሌላ ልሳኖች መናገር'፥ 'በልዩ ልሳን መናገር'፥ 'በሰዎችና በመላእክት ልሳን መናገር' በመባል ተጠቅሷል። ይህን ስጦታ በብሉይ ኪዳን አናገኘውም። በአዲስ ኪዳንም የተለያየ ደረጃ፥ ክፍፍል ወይም ዓይነትነት ያለው ሆኖ አናገኘውም። ሆኖም ግን ከሌሎች ስጦታዎቸ በአንድ ነጥብ ብቻ ለየት ያለ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ያም ስጦታዎች ሁሉ (ልሳንም ጭምር) ማኅበር እንዲታነጽበት የተሰጡ ሲሆን በልሳኖች መናገር ግን በተጨማሪ ተናጋሪውም የሚታነጽበት ስጦታ መሆኑ ነው።

ያ በሌሎች ልሳናት የተነገረው ነገር በሚታወቅ ቋንቋ፥ ማለትም፥ ተናጋሪው በማያውቀው ሰሚዎቹ ግን በሚያውቁት ቋንቋ ሊሆን ይችላል። በሐዋ. 2፥4-13 የምናገኘው ይህንን ነው። ይህ በሆነበት በበዓለ ኀምሳ ዕለት በሌሎች ቋንቋዎች የተናገሩት አይሁድ ሲሆኑ የተናገሩበትን ቋንቋ ከቶውኑ አያውቁትም። አፋቸውን አልፈቱበትም፤ አልተማሩትም፤ ነገር ግን በግልጽ ተናገሩት። ሰሚዎቹ ደግሞ ያለ አስተርጓሚ የገዛ ቋንቋቸውን ይሰሙ ነበር። ልሳን ማለት በመጀመሪያ ደረጃ፥ የሚሰሙትና የሚረድዱት ቋንቋ ነው።

በሌላ ቦታ ደግሞ፥ በ1ቆሮ. 14 የእግዚአብሔር ቃል ስለ ልሳኖች ሲናገር ተናጋሪውም ሆነ ሰሚዎቹም የማያውቁት ቋንቋ እንዳለም ይናገራል። እንዲህ ያለው ልሳን በጉባኤ በሚነገርበት ጊዜ ተናጋሪውም ሆነ ሰሚዎቹ ለተነገረው ነገር እንግዳ መሆናቸው እርግጥ ነው። ስለዚህ የተነገረው ነገር ሰዎቹ ወይም ሰሚዎቹ የማያውቁት ስለሆነ፥ በሚያውቁት ቋንቋ መትተርጎምና ሰሚዎቹ (ተናጋሪውም እንደ ሰሚ) በተነገረው ነገር መታነጽ አለባቸው። ስጦታዎች ሁሉ የተሰጡት አካሉን ለማነጽ ነውና። በልሳናት የተነገረውን መተርጎም ራሱ በልሳናት እንደ መናገር ሁሉ ስጦታ ነው። በልሳናት የሚናገር ሰው የተነገረውን እንዲተረጉም እንዲችል ወይም የመተርጎም ስጦታም እንዲኖረው መጸለይ እንዳለበት የተነገረው ለዚህ ነው። 1ቆሮ. 14፥13 እንዲህ ይላል፤ *ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ።* ትርጉሙ ተናጋሪው የመተርጎምም ስጦታ ካለው በራሱ በተናጋሪው፥ ይህ ካልሆነ ደግሞ፥ በሌላ በልሳናት የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ባለው ሰው ሊተረጎም ያስፈልገዋል። ካልተተረጎመ ማኅበሩ ሊታነጽበት በምንም መንገድ አይችልም። ስለዚህ ካልተተረጎመ መነገር የለበትም፤ 1ቆሮ. 14፥28 እንዲህ ይላል፤ *የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር።*

በ1ቆሮ. 14፥4 *በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።* ይላልና ልሳን ከሌሎቹ ስጦታዎች በተለየ ተናጋሪውንም ሊያንጽ ይችላል። ራስን ማነጽ የሚባለው ይህን ስጦታ ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው ባሕርይ፥ ተናጋሪው ይህን በሚናገርበት ጊዜ ራሱን እራሱ በሚገባው መንገድ የሚያንጽበትና ሊተረጉመው የማያስፈልገው ነው። ራሱን የሚያንጸውም እንዴት እንደሆነ አልተጻፈም። የመንፈስ ቅዱስን ሕልውና በሕይወቱ በመረዳቱ፥ ወይም ስለማያውቀው ነገር እንደሚጸልይ ስለሚገምት ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ሳያቋርጥ ሲናገር ብዙ የጸለየ ስለሚመስለውም ሊሆን ይችላል። ደግሞም በልሳን የሚናገረው ሰው የሚናገረው ለራሱ እንደሆነ ካወቀ እንደማይተረጎምና መተርጎምም እንደሌለበት ከተረዳ ይህን የሚያደርገው በማኅበር ወይም በጉባኤ ከሆነ ድምጹን ማሰማት አይኖርበትም። በልሳናት መናገር ማነጫ ወይም መታነጫ እንጂ ማወኪያ ወይም ልዩ የመሆን መታወቂያ አይደለም። ይህን ከተረዳ ያ ሰው በማኅበር ውስጥ ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር ነው መናገር ያለበት። *የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር።* 1ቆሮ. 14፥28።

በልሳኖች መናገር ትኩረቱ ላላመኑት ምልክትና እንዲሁም እንደ ሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ደግሞ ማኅበረ ምዕመናንን ማነጽ ነው። ላላመኑ ምልክት የሚሆነው በነዚያ በማያምኑት ሰዎች ቋንቋ የሚነገር ስለሆነ ነው። ያኔ የሚነገረው ነገር መነገሩ ብቻ ሳይሆን እነርሱን የተመለከተ መሆኑም ይታወቃቸዋል። ልሳን ለማያምኑ ምልክት ነው። በሐዋ. 2 የሆነው ይህ ነው፤ ያላመኑት ናቸው በቋንቋቸው ሲነገር ሰምተው የዳኑትና የተጠመቁት። የልሳን ለማያምኑ ምልክትነት በጳውሎስ መልእክትም አልተለወጠም። *እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።* 1ቆሮ. 14፥22።

ሲጀመርም በትንቢት የተነገረው ልሳን ለማያምኑ እስራኤላውያን ነበረ። 1ቆሮ. 14፥21 የተወሰደው ከኢሳ. 28፥11-12 ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፤ *በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል፤ እርሱም፦ ዕረፍት ይህች ናት፥ የደከመውን አሳርፉ፤ ይህችም ማረፊያ ናት አላቸው፤ እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ።* ነቢያት ሲነግሯቸው ሲያስጠነቅቋቸው እንቢ ባሉት አይሁድ ላይ በባዕድ ልሳን በማያውቁት ቋንቋ የሚናገሯቸውን አሦራውያንን እና ባቢሎናውያንን ላከባቸው። በኢሳይያስ ዘመን ነበር የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ፈርሶ ወደ አሦር የተጋዘው። ከዘመኑ 100 ዓመት ሳይሞላ ደግሞ ይሁዳ ወደ ባቢሎን ተጋዘ። ባዕድ ልሳን አላመኑምና ለማያምኑ የአለማመናቸው ምልክት ነበረ። ጳውሎስ ይህንን ትንቢት ከጠቀሰ በኋላ ነው ልሳን ለማያምኑ ምልክት መሆኑን የጻፈው።

ልሳን ሲነገር የማያምኑ ከመጡ ምልክት ሊሆናቸውና ወደ መዳን የሚያመጣቸውን እውነት እንዲጨብጡ ሊረዳቸው የተገባ ስጦታ ነው። ይህ የሚሆነው ልሳን ይህንን የምልክትነት ሚና ከተጫወተ ነው። ይህ ካልሆነና፥ እንዲያውም የዚህ ተቃራኒ ከሆነስ? የማያምኑ ሰዎች ልሳንን ሲሰሙ ወደ መዳን ሳይሆን ከመዳን ወደ መራቅ ነው የሚሄዱት። በጳውሎስ ቋንቋ፥ 'አብደዋል!' ነው የሚሉት።

በጉባኤ ውስጥ በልሳኖች ከተነገረ ትርጉሙም መጠበቅ አለበት። ትርጉም ካልኖረ ጉባኤው አይታነጽበትምና እንደዚያ መቀጠል የለበትም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እንደ ቃሉ ሁሉ ነገር በሥርዓትና በአግባብ መሆኑን ማየት አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ማድረጋቸው የመንፈስ ቅዱስን ሥራ መከልከል መስሎ መታየት የለበትም። በእርግጥ መስሎ የሚታይበትም ሆነ የሚሆንበት ሁኔታም ሊኖር ይችላልና ጠንቃቃ መሆንም ያሻል። ሚዛኑ ከተጠበቀ፥ ጤናማና ገንቢ እንጂ ጎጂና አፍራሽ አይደለም። በተጨማሪም ሥርዓትና አገባብ ብቻ ሳይሆን መናፍስትን የመለየት ስጦታም በሥራ ላይ ውሎ መታየት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም በልሳኖች መናገር ከመንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ ሁሉ ከአጋንንትም ሆነ በስሜት ከመነዳት እንዲሁም ከሌሎች ብዙ ጊዜ ከመስማት የተነሣ በኩረጃም ሊመጣ ይችላል። ይህንን በምዕራፍ 4 ስለ ልሳን ቀውሶች ስናገር እመለስበታለሁ። ተናጋሪው አንዳንድ ጥያቄዎችን ቢጠየቅ በጥሞና ለመስማትና በትሕትና ለመመለስ ፈቃደኛ መሆንም አለበት። በልሳኖች የሚናገር አማኝ ስጦታውን የማክበር፥ ፍቅርን የማሳየትና ሌሎችንም ለማነጽ የመትጋት ኃላፊነት አለበት።

በልሳኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ማለት አንድ አማኝ በልሳኖች ሲነገር የተነገረውን ነገር ጉባኤው በሚያውቀው ቋንቋ ለጉባኤው እንዲናገር ለዚያ ሰው የሚሰጠው የመልእክቱ ምንነት መከሰት ወይም መታወቅ ነው። የመተርጎም ስጦታ ቃል በቃል መልዕክቱን የማስተላለፍ የቱርጁማንነት አገልግሎት አይደለም። መልዕክቱ የተነገረበት ቋንቋ የመላእክት ይሁን የሰው፥ ከሰውም የዚህ ይሁን ወይም የዚያ፥ ያ የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ያንን ቋንቋ አያውቀውም። ጉዳዩም ከመልእክቱ እንጂ ከቋንቋው አይደለም። ያ ሰው ትርጉሙንም ያወቀው ቋንቋውን ስላወቀው አይደለም። የቋንቋው እውቀት የለውም። ምናልባት ቋንቋው የሚታወቅም ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፥ በልሳን የተነገረው መልእክት ካንቶንኛ በሚባለው የቻይና ቋንቋ ቢሆን የመተርጎም ስጦታ ያለው ሰው ያንን ቋንቋ የሚያውቅ ቢሆን የሚተረጉመው ግን እንደ አስተርጓሚ ሳይሆን እንደ ተርጓሚ ወይም እንደ መልእክት አስተላላፊ በመሆን ነው። የመተርጎም ስጦታውም ልክ እንደ ልሳኑ ሁሉ መለኮታዊ ስጦታ ነው።

በጉባኤ ትርጉም ከሌለ ማኅበሩ መታነጽ አይችልም። ለዚህም ነው ጳውሎስ በጉባኤ ከልተተረጎመ እልፍ (አስር ሺህ) ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት

በአእምሮ፥ ማለትም፥ ጉባኤው በሚያውቀው ቋንቋ መናገር የመረጠው። የማይተረጎም ልሳን በጉባኤ ውስጥ ከቶም መነገር የለበትም። ትርጉም በሚታወቅ ቋንቋ የሚደረግ በመሆኑ ደግሞ ይህ ስጦታ ከልሳኖችም ይልቅ ተጨማሪ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ተናጋሪው እንዲተረጉም መጸለይ አለበት። የግድ ግን ተርጓሚው እርሱ ብቻ መሆን አለበት ማለት አይደለም። አንድ አማኝ ስጦታው ይህ ከሆነ ለመተርጎም በልሳኖች የሚናገር መሆን የለበትም። መተርጎምም በራሱ ስጦታ ስለሆነ መናገር ሳይችልም መተርጎም ይችላል። የሚተላለፈው ደግሞ ቃል በቃል በመተርጎም ሳይሆን መልእክቱ ነውና፥ የሚጠበቀው የሚነገረው ቃልም ትርጉሙም እኩል እንደሚሆኑ ቢሆንም፥ በልሳኖች የተነገረውና የተተረጎመው የሚወስዱት ጊዜ እኩል ላይሆን ይችላል። ጊዜው የግድ መሳ ለመሳ መሆን የለበትም። አንድ መልእክት በልሳናት ከተነገረ የአምልኮው መሪ ወይም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል አንዱ የሚተረጉም እንዳለና እንዲተረጉም በመጠየቅ ጊዜ መፍቀድ አለበት። በልሳናት እንደ መናገርም ሁሉ በሚተረጎምም ጊዜ መናፍስትን የመለየት ስጦታ መኖር አስፈላጊ ነው። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ያላቸው አማኞች በልሳናት የተነገረው ያ መልእክት ከመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ከሌላ ምንጭ መሆኑ ከታወቃቸው ሌላና ተጨማሪ ውዥንብር ስለሚፈጥር መተርጎሙ አስፈላጊ አይሆንም።

በልሳናት መናገርና ትንቢትን መናገር ከሌሎቹ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ይልቅ ሰፋ ያለ ትንታኔ ተሰጥቷቸዋል፤ ይህን በ1ቆሮ. 14 እናገኛለን። ይህ ማለት ስጦታን ከስጦታ ለማበላለጥ ሳይሆን የማነጽ ደረጃቸውን ማበላለጡ ነው። መፍፈለግ ያለበት ይበልጥ የሚያንጸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ትንቢትን መናገር በልሳኖች ከመናገር ይልቅ ጉባኤውን ያንጻልና የቆሮንቶስ ምዕመናን ከልሳኖች ይልቅ ትንቢትን እንዲፈልጉና እንዲናገሩ ያበረታታቸዋል። ትንቢት ከልሳኖች እንደሚሻልና ይበልጥም ጠቀሜታ እንዳለው ሐዋርያው ይህን የተናገረበትን በተለይ በ14፥1፥5 እና 19 እናገኛለን።

በልሳኖች መናገርን በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ (1ቆሮ. 14) ያሰፈራቸው መሠረታዊ መመሪያዎች አሉ እነዚህም፤

ሀ. በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ (14፥2) (ትንቢት የሚናገር ግን ለሰው ይናገራል።) ለእግዚአብሔር የሚናገር በግሉ ይናገር ዘንድ ተጽፎአል።

ለ. ልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ (14፥4) (ትንቢት የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል)

ሐ. በልሳን የተነገረ ነገር ካልተተረጎመ ከንቱ ነው፤ (14፥5-12)

መ. በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ፤ (14፥13)

ሡ. ለሌሎች ትምህርት ይሆን ዘንድ በልሳን 10 ሺህ ቃላት ከመናገር ይልቅ የሚታወቁ አምስት ቃላት መናገር ይበልጣል፤ (14፥19)

ረ. በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው፤ (14፥22) ትንቢት ግን ለሚያምኑ ነው። (በልሳኖች መናገር ለማያምኑ እንዴት ምልክት እንደሚሆን በተለይ በሐዋ. 2 ከተጻፈው እንማራለን ወይም መረዳት እንችላለን።)

ሰ. ሁሉ በልሳኖች በሚናገሩበት ያልተማሩ ወይም ያላመኑ ቢገቡ ነገሩ እብደት ሊመስል ይችላል፤ (14፥23) (ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን ውጤቱ መወቀስና ስግደት ነው።)

ሸ. በልሳን የሚናገሩ ከኖሩ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም፤ (14፥27) በጉባኤ ሁሉ በልሳን እንዲናገሩ ማበረታታት የቃሉ ትምህርት አይደለም።

ቀ. የሚተረጉም ከሌለ ተናጋሪው በማኅበር መካከል ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር፤ (14፥28)

በ. በልሳኖች መናገር መከልከል የለበትም፤ (14፥39)

ከላይ የተዘረዘሩት እስከተፈጸሙ ድረስ በልሳኖች መናገር መከልከል የለበትም። አካሉን ወይም ጉባኤል የማያንጽ ልሳን ደግሞ እንደ ቃሉ አይደለም።

. . . . .

ይህ ከላይ ያካፈልኩት ስለ ልሳን የጸጋ ስጦታነት ሲሆን ስለ ልሳን ቀውሶች በዚያው መጽሐፍ የጻፍኩትን ከማካፈሌ በፊት በሌላኛው መጽሐፍ፥ *መጽሐፍ ቅዱስ እና የአፈታት ስሕተቶች* በተባለው ስለ ጴንጤነት ጥቂት ወይም የአገራችን ጴንጤቆስጣዊና ካሪዝማዊ ቀለም ከጻፍኩት ጥቂት ገጾች ልውሰድ።

# አሜሪካዊ ክርስትና፥ ኢትዮጵያዊ ነጸብራቅ፥ ስደት፥ እና የአምልኮ ነፃነት

አንድ ኢራቃዊ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ክርስትና በተለያዩ አገሮች እንዴት እንደሚታይ ባቀረበው የጥናት ጽሑፍ ላይ፥ ክርስትና በተጀመረበት በቅርብ ምሥራቅ ውስጥ ሃይማኖት፤ በግሪክ ፍልስፍና፤ በሮም አውሮጳ ድርጅታዊ ተቋም፥ እንዲሁም በአሜሪካ ደግሞ ማትረፊያ ንግድ ሆኖአል ማለቱን ከአንድ ሰባኪ ሰምቼ ነበር። ይህን በደፈናው እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ባይቻልም በዘመናት ከሆኑት ነገሮች አንፃር ሲታይ አባባሉ መጠነኛ እውነትነት አለው። በዘመናዊው ዓለም ሃይማኖት የሰዎች መሳሪያ፥ ኢየሱስም ማትረፊያ እየሆኑ መጥተዋል።

የሰሜን አሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት በወንጌል ስርጭትና ሚስዮናውያንን በመላክ እጅግ ያሸበረቀ ሚና ለመጫወታቸው ያለፉት ሁለት መቶ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምስክር ነው። ይህ የአብያተ እምነቶች ሚስዮናዊ ሚና የዚህ ጽሑፍ ዓላማ አይደለምና ብዙ ልልበት አልችልም። ይሁን እንጂ የዘመን አመጣሹ ካሪዝማዊ ስሕተት ሙሉ በሙሉም ባይሆን እንደ ዋና ምንጭ ሊጠየቅ የሚገባው ሰሜን አሜሪካዊው ክርስትና ነው። ለዚህ በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፍ 3ኛ ምዕራፍ ላይ ብዙ ተብሎአል። ይህ ዘመን በአጠቃላይ ሲታይ በአውሮጳ ክርስትና በእጅጉ እየተዳከመ ሲሄድ በአሜሪካ ደግሞ እየቀጠነ፥ ዓይነቱም እየበዛና እየተቀየጠ (syncretism የሚባለው) አዳዲስ ትምህርቶችና ልምምዶችም እንደ አሸን እየበዙ የመጡበት ዘመን ነው። ቅይጥነታቸው አንዱ ከሌላው ጋር ለመቻቻል የሚደረገው ሙከራ ሲሆን ይህ ቅይጥነት ዘመናዊ ስምና መልክ እየተሰጣቸው ከመጡት ምሥራቃውያን ሃይማኖቶች ጋርም ጭምር ነው።

የኮሚኒዝም ፍልስፍና በአገራችን ከታወጀ በኋላ ብዙዎች በስደትም ያለ ስደትም ከአገር ወጥተዋል። ፍልሰቱ ክርስቲያኖችንም ይጨምራል። በነዚህ ዓመታት የብዙዎቹ መሸሻና 'የተስፋ ምድር' የሆነው ይህ የሰሜን አሜሪካ አህጉር ነው። ከነዚያ ዓመታት በኋላ በቀጥታም በተዘዋዋሪም በጽሑፍም፥ በቪዲዮዎችና በድምጽ ካሴቶችም ይወነጨፉ የጀመሩት ትምህርቶች በአገራችን ክርስትና ላይ አሉታዊ ተጋቦት አሳድረዋል። በኋላ ለተፈጠሩት የስሕተት ልምምዶችና ትምህርቶች ቀጥተኛ ምንጭ የሆኑት እነዚህ የአሜሪካዊ ክርስትና ስሕተቶች ናቸው።

ቦታው ብቻ ሳይሆን ጊዜውም በኛ አቆጣጠር 1970ዎቹ መሆኑ የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አለውና ይህም ሊስተዋል ይገባዋል። ከዚያ ጊዜ፥ ማለትም ከ70ዎቹ ቀደም ሲል በአሜሪካ የነበረው ክርስቲያናዊ ባሕል እየተሸረሸረ፥ መንፈሳዊ ጥማትም እየቀዘቀዘ የመጣበት ጊዜ ነው። ያ መሸርሸርና መቀዛቀዝ እስከ አሁንም በክርስትና ማሽቆልቆል

ላይ ያለ ሂደት ነው። ከ1930ዎቹ ትልቁ የምጣኔ ሀብት ቀውስና ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ አሜሪካ ከገባችባቸው የጦርነቶች ቀውስ ውስጥ የወጣችበትና የተደላደለችበት ዘመን ነው። ከ2ኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የተወለዱት ያንን ሰቆቃ እንደገና እንዳያዩ ጥረት ተደርጎአል። በጥረቱም ምጣኔ ሀብትና የገንዘብ ኃይል በጣም አደገ። ሳይንስና ቴክኖሎጂም መጠቁ። የዘርና የቀለም መድልዎ ቢኖርም የማኅበራዊ ደኅንነት መርሆዎች እየተሻሻሉ፥ ማኅበራዊ መረቦችም እየተዘረጉ መጡ። ውስጣዊ እርካታና መንፈሳዊ እረፍትን ግን በነዚህ ውጪያዊና ቁሳዊ ነገሮች መተካት አልተቻለም። የኢየሱስ ትውልድ ወይም የኢየሱስ ንቅናቄ የተባለው የ60ዎቹ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ለዚህ እርካታ ላጣ የወጣቶች ትውልድ ኢየሱስን በማስተዋወቅ ረገድ በራሱ ስልት አስተዋጽዖ አበርክቶአል። ሆኖም ከነበረበት አሠርት፥ ማለትም ከ1960ዎቹ አልዘለለም።

በነዚህና በቀጠሉት በርካታ ዓመታት ከቢሊ ግሬሃም የጀማ የወንጌል አገልግሎት ሌላ ትልቅ ትኩረት የሳበ አገራዊ የወንጌል እንቅስቃሴ አልነበረም። ይሁን እንጂ በክፍለ ዘመኑ መግቢያና ከዚያም በፊት ተዘርተውና ተጽፈው የነበሩት የጴንጤቆስጣዊ ትምህርት ዘሮች በ1950ዎቹ እንደገና ከአዳዲስ ቅርንጫፎች ጋር ማቆጥቆጥ ጀምረዋል የካሪዝማዊ ንቅናቄ እርሾም ሆነዋል። በ1970ዎቹ ደግሞ መበርከትና ሌሎችም ትናንሽ ከቤተ እምነት ነፃ የሆኑ ማኅበሮችና በርካታ አገልግሎቶች እየተመሠረቱ መንቀሳቀስ ጀምረዋል። ከቤተ እምነት ነጻ መሆን ከትምህርታዊ ተጠያቂነት ነጻ መሆንም ነው። በተመሳሳይ ጊዜም በኢትዮጵያም ካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ስር መስደድ ጀምሮአል።

ታዲያ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ አሜሪካ በሄዱባቸው በነዚያ ዓመታት ውስጥ ከላይ የተባሉት ውስጣዊ ንቅናቄዎች በጣም ትልቅ ሆነው ጠንካራ ተጽእኖ ባያሳድሩም የታወቁ ግን ነበሩ። በኋለኞቹ የኮሚኒዝም ፍልስፍና አስቸጋሪ ዓመታት ከአገር የወጡ በርካታዎች እንደ ተስፋ ወደሚያዩአት አገር ከመድረሳቸው በፊት በጎረቤት አገሮች የስደት ቦታዎች በቆዩባቸው ጊዜያት ክርስቶስን ማወቃቸው አጋጣሚ ሊባል የማይገባው ነገር ነው። እግዚአብሔር ያንን የመከራና የጭንቀት ከበባ ብዙዎች ወደ እርሱ የሚጠጉበት መጥሪያና መሳቢያ አድርጎት ነበር። ጥቂት ያልሆኑት ወደሚሄዱበት ከደረሱ በኋላ በእምነታቸው የሟሙ ቢኖሩም ብዙዎች በጥንካሬ ዘልቀዋል።

የነዚያ የ60ዎቹና 70ዎቹ ስደት ሕዝቦችን ያመሳቀለና ከስፍራ የነቀለ ዓለም አቀፋዊ ክስተት እንጂ በአንድ አገር ወይም ወገን ብቻ ላይ ያተኮረም አልነበረም። ኢትዮጵያም ከብዙዎቹ የስደት ሰልፈኞች አንድዋ ናት እንጂ ብቸኛዋም አልበረችም። ከተሰደዱት ውስጥ በርካታ ክርስቲያኖችም በተለያዩ አቅጣጫዎች ወጥተው ሄደዋል። ብዙዎቹ

እንደ ኢትዮጵያው ወንጌላዊ ክርስትና እንደራሱ በወጣት ዕድሜ የሚገኙ ነበሩ። ይህ ባሕላዊውን ሃይማኖት ሳንነካው ነው። ይህ እንግዲህ ኢትዮጵያን ብቻ የተመለከተ ስደት ተደርጎ መታየት እንደሌለበት ለማሳየት ነው። ሌላው አጋጣሚ ከአገር ውስጥ የወጡትና በአሜሪካ ኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናትን የመጀመርና የማደራጀት ኃላፊነትን የወሰዱ ወይም የተቀበሉት ሰዎች በአንድ መልክ ወይም በሌላ ከካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ ልምምዶች ጋር የተያያዙ መሆናቸው ነው።

ከዚህ ሁኔታ የተነሣ የሰሜን አሜሪካ አብዛኛዎቹ፥ በሙሉ ማለትም ይቻላል፥ አብያተ ክርስቲያናት አንድ መልክ ነው የነበራቸውና አሁንም ያላቸው። ያም በካሪዝማዊ ንቅናቄዎች የቀለመ ጴንጤቆስጣዊ መልክ ነው። አብዛኞቹ በስም ብቻ ነው፥ 'ወንጌላዊ' የሚባሉት እንጂ በአስተምህሮ ረገድ ወንጌላውያን አይደሉም። አንዳንዶቹም ስለመቻቻል ተብሎ ኅብረት እየተባሉ ቢጠሩ ከስም በቀር ቅርጻቸውም ይዘታቸውም ጴንጤቆስጣዊ ቤተ ክርስቲያን ነው። በአገራችን፥ 'ጴንጤ' ማለት ጴንጤቆስጣዊ ሳይሆን ወንጌላዊ እንደማለት እስኪመስል ድረስ በስደቱ ዓመታት የታወቀ ስም ቢሆንም፥ ጴንጤቆስጣዊ እና ወንጌላዊ የሚሉት አጠራሮች አንድ አለመሆናቸውን አንባቢ ሊያስተውል ይገባል። ይህ ጴንጤቆስጣዊ ቅርጽና ይዘት ጠቅላላውን ባይሆንም አብዛኛውን የአሜሪካ ኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚመለከት እውነት ነው። በእስታቲስቲክስ ረገድ ከበርካታ ትልልቆች የሰሜን አሜሪካ ከተሞች ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች ቁጥርና አማኙ ሲነጻጸር ከ1.5 እስከ 3.5% ብቻ ነው። ይህ ከአገር ቤቱ አማካይ መቶኛ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በጣም ያነሰ አኀዝ ነው። የብዙዎቹ አጥቢያዎች ትኩረትም ከወንጌል ስርጭት ይልቅ ከወንጌል ለተረፈው ለሌላው ሁሉ ነገር ነው።

ከላይ፥ 'ጴንጤቆስጣዊ እና ወንጌላዊ የሚሉት አጠራሮች አንድ አለመሆናቸውን አንባቢ ሊያስተውል የተገባ መሆኑን አውስቻለሁ። ከአብዮቱ ጥቂት ቀደም ሲልና በተለይም በአብዮቱ ዘመናት በአገር ውስጥም ወንጌላዊ ክርስትናና ጴንጤነት ሞክሼ ሆነዋል። ይህ የአጋጣሚ ስያሜ ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት፥ ከ1960ዎቹ በፊት፥ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች በየኖሩባቸው ቦታዎች 'አማኞች' ወይም 'የኢየሱስ ሰዎች' በመባል ነው ይጠሩ የነበረው። ጴንጤ የሚለው ስም ጴንጤቆስጣውያኑ 'ክርስቲያን' ከሚለው መጠሪያ ይልቅ የሚጠቀሙበት መጠሪያ ቃል ነው። ይህና በተለይም በናዝሬት፥ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተማዎች በኅብረተ ሰቡ ዘንድ ጥሩነት ከሌላቸው ልምምዶች ጋር በመጣበቅ የተዋሕዶ ተከታይ ያልሆነው ክርስቲያን ሁሉ እንኳ፥ ቀድሞ ካቶሊክ ሆነ ወይም ኮተለከ እንደሚባለው ወንጌላዊው አማኝ ማኅበረ ሰብ፥ በጴንጤ ወይም መጤ፥ እና በጅሆቫ ስም ታወቀ። ይህንን ስም ከአማኙ ማኅበረ ሰብ ወይም ወንጌላዊው የክርስቲያን ጎራ ይልቅ አማኝ ያልሆነው ሕዝብ አብዝቶ

አወቀው። በእምነትም ሆነ በልምምድ ጴንጤቆስጣዊ ያልሆኑትም ሁሉ ይህን ስም ያለችግር እስኪቀበሉት ድረስ ስያሜው በሁሉ ላይ የተርከፈከፈ ነበር።

በዚያው ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የስደት ገፈት ዘመኗ ነበርና ስም ትልቅ ቁም ነገር ያለው ጉዳይ አልነበረም። ይህ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኖች የተዘጉባቸው፥ የወንጌል እንቅስቃሴዎች የተወሰኑባቸው፥ አንዲት አጥቢያ ብዙ ትንንሽ ሆና በቤት ውስጥ ያመለከችባቸው ዓመታት ነበሩ። እነዚህን ብዙ ትንንሽ ቡድኖች ለማገልገል በርካታ አገልጋዮች አስፈለጉ። በብዙ ረገድ ስደቱ ድንገተኛ ይመስላልና በቂ የአገልጋዮችም ዝግጅትም አልነበረም። ልክ እንደ ስደቱ ሁሉ ድንገተኛ አገልጋዮችም በዙ። በአንዳንድ ቦታዎችም ልክ ደርግ በታጠቅ ማሰልጠኛ የ3 ወር ለብ ለብ ስልጠና ሚሊሻዎች አሰልጥኖ ወደ ሱማሌ ግንባር እንዳሰማራው የነበረ በአጫጭር ጊዜ ትምህርቶች የሰለጠኑ የቡድን መሪዎች ተመረቱ።

እያንዳንዱን ትንንሽ ቡድን መያዝ ራሱን የቻለ ችግር ነበርና በአንዲት አጥቢያ ብቻ እንኳ መሪዎቹን የመሰሉ ጉራማይሌ ቡድኖች እያደጉ መጡ። ጊዜው ለብዙዎቹ በቂ መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ስንቅ ያልነበረበት፥ የትምህርትና የስልጠና መጻሕፍት ጠንቅቀው ያልተዘጋጁበት፥ አዲስ ኪዳን እንኳ እንደልብ ማግኘት ያስቸገረበት ጊዜም ነበር። በችግር ጊዜ የተወለዱ ወይም የሚያድጉ ልጆች ለመኖር በሚያደርጉት ትግል ይጠነክራሉና ስደቱ ራሱ መጠንከሪያ ነው ሊባል ቢቻልም፥ የምዕመናን ቀለብ ግን የዕለት ጉርስ ዓይነት ነበር። አጋጣሚ ሆኖ በነዚሁ ጊዜዎች ውስጥ ነበር እነዚህ የአሜሪካዊ ክርስትና ትህርቶች በተለይ በቪዲዮ ቴፖች ውቅያኖስ እየተሻገሩ ወደ አገር ውስጥ በብዛት የገቡት። ቀድሞ በነበሩት ላይ እየተጨመሩና እየተባዙ አዳዲስ ጴንጤቆስጣዊ ትምህርቶችና ልምምዶችም በእጅጉ ተባዙ።

ከስደቱ ዓመታት በፊት የተደረገው መዘጋጃ አገር አቀፍ ኮንፈረንስ በ1972 በናዝሬት መጽሐፍ ቅዱስ አካዳሚ የተደረገው ነው ማለት ይቻላል። ያ መጻዒውን የአገሪቱን ቤተ ክርስቲያን የስደት አካሄድ በስሱ የተነበየም ይመስላል። ከኮሚኒስት አገሮች ልምድ የመቅሰም ምክክርም በትንሹ ተደርጎበታል። ጠለቅ ብለን ስንመለከተው የ66ቱ ሕዝባዊ አብዮትና ቀጥሎ የተመረጠው ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮት ጎዳና ለቤተ ክርስቲያን ያመጣላት ጥቅምም፥ ያመጣባት ጉዳትም እምብዛም የለም። እርግጥ የማምለኪያ ቦታዎች ተዘግተዋል፤ ንብረት ተወርሶአል፤ ተዘርፎአል፤ ጥቂት ያልሆኑ ታስረው ተጎሳቁለዋል። የቤተ ክርስቲያን ጉዳት ከተቆጠረ ግን ከዚህ ሌላ የለም። ያመጣላት ጥቅምም የለም። እርግጥ መጠነኛ ጥራት የጅምላ ጉዞን የለወጠ መስሎአል፤ እምነትም ዋጋ የሚጠይቅ መሆኑ ታይቶአል። እነዚህ ግን ስደትና አብዮት ቢኖሩም ባይኖሩም በዘመናትና በታሪክ ውስጥ እንደታየው የክርስትና መለዮ መሆን ያለባቸው ነገሮች ናቸው። አብዮቱ የገዛ ራሱን ሥራ ነው የሠራው። የወደቀውም የመውደቂያው

ጊዜ ስለደረሰና ከውስጡ ስለበሰበሰ ነው። ደግሞም ዓለም አቀፋዊው የሶሻሊዝም ርዕዮት ሚዛን ስላጋደለበት የፍልስፍናውን ማዝመምና ውድቀት ተከትሎ ነው የኢትዮጵያው አብዮትም የወደቀው። ይህ ክስተት አገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም ዓቀፋዊ ይዘት የታየበት ሁኔታም ነበር።

የደርግ መንግሥት በመጀመሪያዎቹ ዘመናቱ ከቻይና ተሞክሮ በመነሣት የባሕል አብዮት የተባለውን ዘመቻ በመጠኑ አካሂዶአል። የዘመቻው አንድ ገጽታ ቤተ ክርስቲያንን በስልታዊ መንገድ ጨርሶ ማጥፋት ነበር። ቢሆንለት ያ መንግሥት ተቃዋሚዎቹን የፖለቲካ ቡድኖች ምሳና እራት እንደዳደረገው ቤተ ክርስቲያንንም ሊውጥ ሞክሮ ነበር። ቤተ ክርስቲያን በምድር ብትኖርም ምድራዊት አይደለችምና ይህን ማድረግ አልቻለችም። ይህ ከቶም የማይቻል ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድራዊ መንግሥት ቸርነት የምትኖር ወይም በዚያ መንግሥት ስደት የምትጠፋ አካል አይደለችም። ከጌታ ዕርገት በኋላ የነበሩት ሦስት መቶ ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የዚህ ዐቢይ ምስክር ነው።

በአንጻሩ 1980ዎቹ የነጻነቱ ዓመታት ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ ለስደት ሳትሰናዳ እንደመሸባት አሁንም ለነፃነትና ለሰፋ ዕድል ሳትሰናዳ የነጋባት ይመስላል። ወዲያው መንደፋደፍ ተጀመረ። ጊዜውንና ሁኔታውን የተመለከቱ ጠሊቅ ቀርቶ፥ ጠቅላላ የግምገማና የስልት ጥናት ምክክሮችና ጸሎቶች እንኳ በወጉ አልተደረጉም። በወንጌል ስርጭት ላይ ብቻ በመጠኑ ሰፊ የሆነ ሩጫ ተደረገ። ስለዚህ የኮሚኒዝም ካድሬዎችንና የተፈናቀሉ የጦሩንና የምሑራኑን ክፍል ጨምሮ ብዙዎች ወደ ወንጌል እውነት መጡ፤ ወደ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ተደባለቁ። ይህ ትልቅ ዕድል ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከደርግ ዘመን ቀጥሎ በቁጥር ያደገችበት ዘመን እንደኛ አቆጣጠር የነጻነቱ ዓመታትወይም ከማጀት ወደ አደባባይ የሚባለው፥ 1984-85 ነው።

የ1987 የእስታቲስቲክስ ቢሮ ዘገባ በግርድፉ እንደሚያመለክተው ጠቅላላው የክርስቲያን አኀዝ 48.65% ሲሆን ሙስሊሙ 44.95% ነው። የቀረው 6.4% ሌሎችን በሙሉ ይይዛል። ከክርስቲያኑ ጎራም ተዋሕዶ 38.15%፤ ካቶሊክ 0.89%፤ ወንጌላዊው ክርስትና 9.61% አስመዝግቦአል። ዓለም አቀፍ እስታቲስቲክስ ደግሞ የወንጌላዊውን እምነት አኀዝ ከ12 እስከ 14% ከፍ ያደርገዋል። ይህ እሰይ የሚሰኝ መልካም ዜና ነው። ይሁን እንጂ፥ ዕድገቱ ጥሩ ሆኖ ሳለ 'ከወንጌል በኋላስ?' የተባለ አይመስልም። መጠነ-ሰፊ ዘመቻ ላይ እንጂ ስረ-ጥልቅ ክርስትና ላይ አልተተኮረም። ስለዚህ በአንድ በኩል ጥቂት ያልሆኑ ወደ ኋላ ተመልሰዋል። በሌላ በኩልም ከዚያ ካልበለጡ ያላነሱ ለተሳሳቱ ትምህርቶችና ልምምዶችም ተዳርገዋል።

በክፉው ቀን የነጎዱትም እንደ ድል ማግስት አርበኞች ከነአሜሪካዊ ልምምዳቸውና ግሳንግሳቸው መጡና በቀደሙት ዘመናት የቃረሙትን የተደበላለቀ ትምህርት ሳይመርጡ ለአገር ቤቱ ምዕመናን አጋቡት። ቤተ ክርስቲያንም ዘመኗን መምሰል ጀመረች። የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ዘመን አይደል? የውድድር? ቤተ ክርስቲያንም ውድድር ውስጥ ገባች። የዲሞክራሲ ዘመን አይደል? ማን ማንን ይነካል? ማንስ ማንን ይናገራል? ሕገ መንግሥታዊ ድጋፉም ሌላ ጉልበት ማበርከቱ አይረሳም። ስለዚህ ተንሳፋፊና ተለጣፊ አብያተ ክርስቲያናት በዙ። አንዳንዶቹም የአኩራፊዎች መሰብሰቢያ እየሆኑ ገና በሚከፈቱበት ዕለት ሺህ ሲደመር እየሆኑ መሰብሰብ ጀመሩ። በዚሁ ሁሉ ወንጌል ተሰራጭቶ ነፍሳት መዳናቸው ተአምር ሆኖ፥ሳለ የስሕተት አሠራሮችም መብዛታቸው አሌ የማይሉት እውነት ነው። የጠፉትን በማጥመድ ፈንታ የዳኑቱን ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የሚያንገዋለሉት አማኞችና አገልጋዮችም ሌላ በአጥቢያዎች መካከል የሚፈጠሩ የችግር አጀንዳ ሆኑ።

ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያትና ከኢትዮጵያውያኑ አሜሪካዊ ክርስትና ጋር የተያያዘው ሁኔታ ከምርቱ ይልቅ ግርዱ የበዛበት ነው። በሰሜን አሜሪካ የሚገኙት የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ክርስትና ከመጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይልቅ አሜሪካዊውን ካሪዝማዊነት ሙጥኝ ብሎ የከረመ ነው። ይህም፥ ጤንነትን፥ ብልጽግናን፥ ድሎትንና ምቾትን፥ ልምምዳዊነትን፥ ስሜታዊነትን፥ ከሞት መሸሽን፥ ከመስቀል ዋጋ የተለየ ክርስትናን ማስተዋወቅ መለያው ሆነ። ከላይ የተጠቀሰው ሰው ክርስትና በአሜሪካ ማትረፊያ ሆነ እንዳለው በኢየሱስ ስምም እየተነገደ መጣ። አንዳንዶች አገልጋዮች ደግሞ በቪዲዮ የሚያሳዩአቸውን ሰዎች ቃል በቃልና እርምጃ በእርምጃ እየኮረጁ እንደ በቀቀን መድገምን ሥራዬ ብለው ያዙት። ክርስትና የሚጠይቀውን ዋጋ መክፈል የማይወድ ሁሉ ደግሞ ተሻምቶ ተቀበላቸው። አንዳንዶች በየዋህነት አንድ ሰው ከዚያኛው የዓለም ክፍል፥ ከአሜሪካ ስለመጣ ብቻ የተማረና ለአገልግሎትም የበቃ አድርገው ይቀበሉታል። ይህ አደገኛ የዋህነት ነው።

አንድ እንዲህ ያለው አሜሪካዊ አበሻ ሰባኪ ከአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን አምልኮ ጋር በማነጻጸር የኢትዮጵያ ሕዝብ ገና አምልኮ አለማወቁን፥ አለመጀመሩን ተናግሮ ነበር። በነጻነት ስም አምልኮን በሚመስልና ነገር ግን ሥርዓት በለቀቀ ሁኔታ የፈለጉትን መሆን ለግንፍል ስሜታዊነት በር መክፈት ነው። መፈክራምነትና ‘ትቅደምና ይውደም’ ሲል የኖረ ማኅብረ ሰብ በበዛበት በዚህ ዘመን አምልኮ ያለ መፈክርና ያለ ጩኸት የሚደምቅ የማይመስላቸው ብዙዎች ተነሡ። በእውነቱ፥ አምልኮ በቅርጹ አንድ ዓይነት መሆን የግድ የለበትም። የአምልኮ ዓላማና ግብ የአምላኪ ከተመላኪው ጌታ ጋር መሆንና በዚያ መቆየት ነው። ሚዛኑም የተጠበቀ ሊሆን ይገባዋል። የማኅበር አምልኮም የጉባኤተኛው በጸሎትም በዝማሬም፥ ቃሉን በመማርም፥ ወይም የመሳሰሉትን ነገሮች በማድረግ አብሮ መቆየት ነው።

ከጩኸታም አምልኮ ልምምድ ወደ ጸጥተኛ ጉባኤ የሄደ ሰው የእንቅልፋሞችና የሙታን ጉባኤ እንደገባ ሊመስለው ወይም ከጸጥተኛ አምልኮ ጉባኤ ወደ ጩኸታሙ የገባው የቀውሶችና የዕብዶች አደባባይ የገባ ሊመስለው ይችላል። የጸጥታና የጩኸቱ ልዩነቱ አንጻራዊ ነው። የሁለቱም ይዘት ተመሳሳይ ከሆነ ቅርጻቸው ብቻ ነው ልዩነቱ። ይህ እንግዲህ ለአምላኪው ምዕመን ነው። አዲስ ለሚመጣውና ላላመነውስ? ይህም መታለፍ የለበትም። በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን ንድፍ ተከትሎ ሚዛናዊነትን ማስፈን የጉባኤ አምልኮ ጤናማ ግብ ነው። ክርስትናውና ትምህርቱ ጤናማ እስከሆነ ድረስ የአምልኮ ቅርጽ የጉባኤውን ሚዛንና ጣዕም እየተከተለ የሚቀረጽ ወይም የሚመቻች ነገር ነው። የሚቀረጽና የሚመቻችም ብቻ ሳይሆን የጉባኤው ዕድገትና ብስለት በራሱ የሚለውጠው ወይም የሚያመጣውም ሊሆን ይችላል። አንድ የአምልኮ ሥርዓት በሌላው ላይ ሊያይልና ሊልቅ የሚችልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም፤ ወይም አምልኮ በአዝጋሚ ለውጥ እያደገ የሚሄድ ነገር አይደለም። በዚህ ዘመን ያለን እኛ የዛሬ 20 ወይም 200 ዓመት በፊት ከነበሩት የተሻለ ልናመልክ አንችልም። ወይም እዚህ ያለን እኛ ቻይና ወይም ቻድ ካሉት ክርስቲያኖች የተሻለ ልናመልክ አንችልም። አምልኮ በጊዜና በቦታ ልቀቱ ሊበላለጥ አይችልምና።

ሌላው የዘመናዊው መነቃቃትና ተሐድሶ ንቅናቄዎች፥ በተለይም የአሜሪካዊው ክርስትና ገጽታ ንዋይና ብልጽግና ነው። ይህ ለሁሉም ዓለማዊ አእምሮና ለምዕራቡ አመለካከት፥ እንዲሁም ለሥጋዊ ክርስቲያን የሚመች ትምህርት ነው። የምዕራቡ ዓለም ሥርዓተ ማኅበር የሆነው ካፒታሊዝም በተፈጥሮው ሰዎችን መፍቀሬ ንዋይ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ክርስቲያኖችም ከዚህ ነጻ አይሆኑም። በምዕራቡ ካፒታላዊ ዓለም ለገንዘብ ፍቅር ብቻ ሳይሆን ለገንዘብ ማካበትም ጣሪያው ሰማይ ነው። ግን ልፋቱም የዚያን ያህል ነው። ስለዚህ ያለልፋት የሚገኝ ከሆነ፥ አቋራጭ መንገድ ከተገኘ ማለፊያ ነውና፥ ለምን ይህ መንፈሳዊነትን የተቀባ ትምህርት ሰዎችን አይስብም? የብልጽግና ወንጌል ስለሚባለው የስሕተት ትምህርት በመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፍ በቂ ተብሎአል። ከዚህኛው ርዕስ ጋር በተያያዘ ጥቂት መጨመር ያስፈልግ ይሆናል።

የሰዎችን የገንዘብ ምንጭ የሚመጥጡ ስግብግብ አስተማሪዎች የሚያስተምሩአቸው ጥራዝ ነጠቅ ጥቅሶች አሉ። እርግጥ ጌታ ስጡ ይሰጣችኋል ብሎአል። ጳውሎስም በጥቂት የሚዘራ በጥቂት እንደሚያጭድ፥ ከሚቀበልም የሚሰጥ የተባረከ እንደሆነ ጽፎአል። ግን ይህ ብቻ አይደለም። እነዚህ፥ ‘የማትረፊያው ኢየሱስ’ አስተማሪዎች የሆኑ የወንጌል ነጋዴዎች 2ቆሮ. 8 እና 9ን ቢያጠኑት በቂ ትምህርት ያገኙ ነበር። የቆሮንቶስ ሰዎች በድህነታቸው እንኳ በቸርነት ይለግሱና ይሰጡ የነበረው ለፈዋሹ፥ ለቀዳሹ፥ ለሰባኪው፥ ለአስተማሪው ጳውሎስ ሳይሆን ለተቸገሩት የኢየሩሳሌም

ምዕመናን ነበረ። የሰጡትም ቤተ ክርስቲያን መርጣ በሾመቻቸው ሰዎች እጅ ነበር፤ 1ቆሮ. 16፥1-4።

አሚጥጠው ሰጥተው ኋላ ጎድሎባቸው ራሳቸው የሚበሉትን አጥተው እንዳያማርሩ በደስታና በፈቃድ ካላቸው እንዲሰጡ ነው የተባሉት እንጂ፥ ከላይ ያየናት እጎት (ተመ) እንደተጭበረበረችበት ስብከት የውሸት ተስፋም ማስፈራሪያም አልተነገራቸውም። አንድ የብልጽግና ትምህርት ሰባኪ ያላቸውን አሚጥጠው መስጠት እንዳለባቸው ሲያስተምር እንደ ምሳሌ የጠቀሳት ሴት የሰራፕታዋ ሴት ነበረች። 'ይህች ሴት ያላትን አሚጥጣ መጋገርዋ ምን አሳጣት?' አለ። አንደኛ፥ ይህች ሴት ያላትን አሚጥጣ አልጋገረችም፤ ከቀራት ትንሽ ቀንሳ ጋገረች እንጂ። ሁለተኛም እንደ ኤልያስ ቃል ሴቲቱና ልጅዋ በረሃቡ ዘመን ሁሉ አልተራቡም። እነዚህ የዘመናችን አትራፊዎች ግን የባንክ ገንዘብ አሚጥጠው ወስደው ቤትና ንብረት ሲያስሸጡ፥ የታክሲ ሳንቲም ወስደው በእግር ሲያስኬዱ፥ ሌላው ቀርቶ ሰዎችን ሲያስርቡ ታይተዋል።

እርግጥ ለእግዚአብሔር ከሰጠን እርሱም እንዲባርከን ብንመኝ ወይም ብንጠብቅ ክፋት የለበትም። ግን እንዲህ ወይም እንዲያ እንዲያደርግልን ግዴታ አለበት ወይ? ወይስ እኛን እነርሱ እንደሚሉት ሊያበለጽገን ተስፋ ሰጥቶአል ወይ? የማትረፊያው ኢየሱስ አስተማሪዎች፥ 'አዎን ተስፋ ሰጥቶአል' ነው የሚሉት። መስጠትን በመዝራትና ማጨድ ሕግ አስደግፈው ብር ሰጥቶ ብሮች መቀበል እንደሆነ ያስተምራሉ። ክርስትና እንደምን ፈጥኖ ተለወጠ? ከዓመታት በፊት ብቻ እንኳ ይሰበክ የነበረው ስብከት ክርስትና ዋጋ ማስከፈሉ፥ የኛ የሆነው ሁሉ የክርስቶስ መሆኑ፥ ደቀ መዝሙርነት መሥዋዕትነት መጠየቁ፥ ወዘተ፥ ነበር። ዛሬስ? ዛሬ የሚሰበከው ክርስትና ዋጋ እንደሚያስገኝ፥ የክርስቶስ የሆነው ሁሉ (ምድራዊ ሀብትና የሰዎች ንብረቶችም ሁሉ) የኛ መሆኑ፥ ክርስትና ምንም መሥዋዕትነት ከቶም እንደሌለው ነው ለጆሮ ተጣፍጦ ተቀምሞ የሚነገረን። ወንጌሉ ነው የተለወጠው ወይስ ሰዎቹና ትምህርቱ?

ጌታ ሲጠራን ለክርስቲያኖች ሁሉ የብልጽግናን ተስፋ ሰጠ? አዎን፥ ሰማያዊና ዘላለማዊ ተስፋን ሰጥቶአል። ጊዜያዊና ምድራዊ ብልጽግናስ? የተስፋ ሻሞ የሚበትኑልን ብዙ ቢሉም የለም፤ አልሰጠም። ለምድሩማ ራሱም እንኳ ራሱን የሚያስጠጋበት እንዳልነበረው ነው የተናገረው። ደቀ መዛሙርቱስ? ጴጥሮስና እንድርያስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ዓሳቸውን መረባቸውንና ታንኳቸውን ትተው ሲከተሉት የትልልቅ መርከቦችና የሰርዲን ፋብሪካዎች ባለቤቶች መሆን ነበረባቸው። ግን በሐዋ. 3፥6 ላይ ጴጥሮስ ብርና ወርቅ እንደሌለው ነበር የተናገረው። ዮሐንስም የብር ከረጢቱን አልከፈተም፤ የለውማ። ጳውሎስ እስከዚያች ሰዓት ድረስ እንደሚራብ እንደሚጎሳቆል መከራውን ዘርዝሮ 'እኔን የምትመስሉ ሁኑ' ይላቸዋል፤ 1ቆሮ. 4፥11-16። ይህ ማለት ሁሉ ክርስቲያን ጎስቋላ ይሆናል ማለት አይደለም። የዚያኑ ያህልም ሁሉም ክርስቲያን

ስለሆነ ብቻ የተንደላቀቀ ባለ ጸጋ ይሆናል ማለትም አይደለም። በመጀመሪያ፥ ከደኅንነት፥ የዘላለምን ሕይወት ከማግኘት የበለጠ ምንም ብልጽግና የለም። ቀጥሎም ክርስቲያን እንደ እግዚአሔር ባለአደራ በተሰጠው ምድራዊ ጸጋ ታማኝና ትጉህ ከሆነ፥ ከአምላኩ በተቀበለው ጉልበት፥ አእምሮና ጥበብ በተግባሩ ከተሰማራ ፍሬያማ የማይሆንበት ምክንያት የለም። ብር ግን እንደቅጠል ከዛፍ ላይ አይቀነጠስም።

የብልጽግና ትምህርት ለስግብግብ አእምሮና ለሥጋዊ ክርስቲያን በጣም የሚጥም ትምህርት ነው። ከሁሉም የሚያሳፍረው ደግሞ ይህ ትምህት በአንዳንዶች ዘንድ ከደኅንነት ጋር መቆራኘቱ ነው። የዳነ ሁሉ መበልጸግ አለበት፤ ይህ ካልሆነ ደኅንነቱ አጠያያቂ ነው እስከ ማለት ይደርሳሉ። ለቤተ ክርስቲያንና ለጤናማ አገልግሎቶች መስጠት ተገቢ ቢሆንም መስጠትን የብልጽና መክፈቻ ያደርጉታል። በመስጠት ብቻ መበልጸግ ቢኖርማ ኖሮ ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ችግረኞች እርዳታን ከገላትያና ከመቄዶንያ ከቆሮንቶስም አብያተ ክርስቲያናት ከመሰብሰብ ይልቅ ለራሳቸው ለኢየሩሳሌም ችግረኛና እርዳታ ተቀባይ ክርስቲያኖች ይህን አቋራጭ መበልጸጊያ ለምን አላስተማራቸውም ነበር? ሰጥተው ራሳቸውን እንዲያበለጽጉ ማስተማር ሲችል ለምን ዙሪያ ጥምጥም በመሄድ እርዳታ ማሰባሰብ አስፈለገው? የብልጽግና አራማጆች ትምህርትና ባሕርይ የሚጋጭበት ትልቅ ነጥብ እነዚህ ሰዎች በአብዛኛው መቀበል እንጂ መስጠትን የማያውቁ ሰዎች መሆናቸው ነው። አድማጮቻቸው እንዲሰጡ ያስተምራሉ እነርሱ ግን አይሰጡም። ሲሰጡም በትልቅ ማስታወቂያና ለሚድያ ፍጆታ እንዲውል በማሰብና በማስላት ነው። በዚህ ነገር ከልብ የሚያምኑ ቢሆኑ ኖሮ ለችግረኛ ፈጥኖ ደራሽ እነርሱ በሆኑ ነበር። ግን በዚህ ምግባረ ሠናይ የሚታወቁ አይደሉም። ይህ የሚያሳየው ትምህርቱን ራሳቸውም እንደማያምኑበትና ለማትረፊያነት ግን እንደሚገለገሉበት ነው።

ሌላው አሳሳቢ ነጥብ ደግሞ ይህን የሚሰብኩላቸው ወይም አድማጮቻቸው አድርገው የሚመርጡአቸው ሰዎች በመጠኑም ቢሆን ያላቸውና ሊሰጡ የሚችሉ መሆናቸው ነው። እንዲህ ያለ ትምህርት የሚሰብኩ ሰዎች ወደ ድሆች ወይም ወደ ችግረኛ ቤተ ክርስቲያን ወይም ችግረኞች አማኞች ዘንድ ሲሄዱና ይህን ሲናገሩ አይታዩም። ቢሆንማ ለማበልጸግና ድኅነትም ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ወደ ድሆቹ መሄድ ነበረባቸው፤ ግን የሚተላለፍባቸው ይመስል ድህነትን ይፈሩታል፤ እንደማይሰምርላቸውም ጠንቅቀው፥ ስብከታቸው እንደማይሠራም አሳምረው ያውቁታል። መቀማጠል የእግዚአብሔር ልጅነት ምልክትና መታወቂያ ቢሆንማ ኖሮ በርካታ አማኞች የጌታ ልጆች ሆነው ሳሉ ከእምነታቸው ብቻ የተነሣ በመከራና በስደት ስለ ምን ይኖራሉ? የለም፤ የብልጽግና ወንጌል ልዩ ወንጌል ነው። የብልጽግና ወንጌል የስግብግብነት ወንጌል ነው። የብልጽግና ትምህርት ነገሮችና በአጠቃላይ የካሪዝማውያን ሌላ ጉልህ ችግር ለእግዚአብሔር ያላቸው ግምት ትንሽ መሆኑ ነው።

እግዚአብሔርን የተጠየቀውን ሁሉ የሚያቀርብ ሸቀጥ አራጋፊ፥ ፈቃድ የሌለው የፍጡራት አገልጋይ አስመሰሉት። እኛ የእርሱ አገልጋዮች ልንሆን ሲገባ እርሱን የኛ አገልጋይ አድርገው ሳሉት።

እግዚአብሔርን አገልጋይ የሚያስመስለው ሌላ ትምህርት የጸሎት አመላለሱ ነው። እግዚአብሔር ጸሎትን ይመልሳል? አዎን፥ በእርግጥ ይመልሳል። ግን እኛ እንደፈለግን ይመልሳል? አይደለም። በኛ ምኞትና በእግዚአብሔር ፈቃድ፥ ወይም በምንፈልገውና በሚያስፈልገን ነገር መካከል ያለውን ልዩነት እንዲህ በቀላል መመልከት የለብንም። ከእነዚህ አንዳንዶች እግዚአብሔር የልባችንን መሻት እንደሚሰጠን በመናገር መዝ. 37፥4ን ጎምደው ይጠቅሱታል። ከጥቅሱ ብቻ እንኳ ስንመለከተው እግዚአብሔር የልባችንን መሻት የሚሰጠን ልባችን ስለተመኘው ብቻ አይደለም። በእርሱ ደስ መሰኘት አብሮ ተጠቅሶአል። በእርሱ ደስ መሰኘት ለፈቃዱ መገዛትን የያዘ እውነትን ነው። እንዲያም ሆኖ በእርሱ ደስ የተሰኙትም እንኳ ለምነው የልባቸውን መሻት ያጡባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው።

ከላይ በትንሹ እንደተጠቀሰው እዚህ ላይ እንደገና ሊጤን የሚገባው የሰሜን አሜሪካ ክርስትና ወይም አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ እንዲህ ናቸው ማለት ያለመሆኑ ነው። የጅምላ አባባል ሁልጊዜም ስሕተት አይጠፋውም። ተፈትኖ ያለፈ ፍሬያማ ክርስትና እና አገልግሎት ያለባት አገርም ናት አሜሪካ። በሀብትና በምቾት ተከብበው ያንን የመንደላቀቅ ፈተና ገፍተውና ወደ ጎን ብለው የሚኖሩ ምዕመናንና የሚያገለግሉ ታማኝ አገልጋዮች አገርም ናት አሜሪካ። በድኅነት ጌታን ከማመንና ከማገልገል ይልቅ ምናልባት በድሎት ታማኝ መሆን ይበልጥ ፈታኝ ሳይሆን አይቀርም። አሜሪካ ጠንካራ ወንጌላዊ እንቅስቃሴና ወንጌል ወዳልደረሰባቸው የሕዝብ ክፍሎች ወንጌልን ለማድረስ ዋጋ እየተከፈለ የሚደረግ ብርቱ ትግል የሚታይባት አገርም ናት። ኢትዮጵያም የዚህ የወንጌል ገድል በረከት ተካፋይ ናት። በኢትዮጵያ ወንጌላዊ ክርስትና ታሪክ ውስጥ እንደሚታወቀውም እንኳ ከ1910ራዎቹና 20ዎቹ ጀምሮ ብዙ የወንጌል መልእክተኞች ከዚህ ክልል መጥተዋል። አሜሪካዊ ዜግነታቸውን ለአገልግሎት አመቺነት ሲሉ በኢትዮጵያዊ ዜግነት የለወጡ እንደ ዶክተር ቶማስ ላምቤን የመሳሰሉ ዋጋ ከፋይ ሚስዮናውያን ወደ አገራችን መጥተው አገልግለዋል። ምቾትና አካላቸውን ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውንም መሥዋዕት ያደረጉ ጥቂት አይደሉም። አሁንም ቢሆን በዚህ ረገድ ብዙ ነገሮች እየተደረጉ ናቸው። ለቃሉና ለአባቶች እምነት የሚጠየቀውን ሁሉ ዋጋ ከፍለው ጤናማ የክርስትና ትምህርት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የጣሩና የሚጥሩ ውብ አገልጋዮች ያሉበት አገር ናት አሜሪካ፥ በሌላ ገጽታዋ።

እንግዲህ ክርስትና ዓመታትና ዘመናት ሲያልፉና ሲለወጡ እንደየዘመኑ ፋሽን የሚለዋወጥ ከሆነ፥ ከየዘመናቱ ብቻ ሳይሆን ከየአህጉራቱ የሚመጡ ነገሮች ቅይጥም

ከሆነ በአዲስ ኪዳን የሚታየው ትክክለኛ መልኩ መልክ ብቻ ሆኖ ሊቀር ነውና መጠንቀቅ ያሻል። የአዲስ ኪዳንን መሠረት የለቀቀና የሚያስለቅቅ ወንጌልን ከአሜሪካ ብቻ ሳይሆን ከሰማይ መላእክትም መጥተው ቢሰብኩልን የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ደግመን ልናጤን ይገባል፤ *የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።* 2ቆሮ. 11፥4። *ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።* ገላ. 1፥8-9፤

(*መጽሐፍ ቅዱስ እና የአፈታት ስሕተቶች፤ ሁለተኛ እትም፥ ገጽ* 253-265።)

# የልሳኖች ቀውስ

(ከመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች የመጀመሪያ እትም ገጽ 198-211፤ ለሁለተኛ እትም በመጠኑ የዳበረ።)

ለካሪዝማዊ ቀውሶች መነሻው ጴንጤቆስጣዊ ልምምዳዊነት ሲሆን የልሳኖች ቀውስ ጉልህ ስፍራ ያለው ነው። እግዚአብሔር ከምህረቱ የተነሣ አድኖን የአካሉ ብልት ሲያደርገን ከጸጋው የተነሣም ስጦታዎችን ሰጥቶናል። ከነዚህ ስጦታዎች መካከል አንዱ በሌላ ልሳን ወይም ቋንቋ የመናገር ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ በዘመናችን ልክ እንደ ባቢሎን ግንብ ዘመን መለያየትንና መደናገርን የፈጠረ ስጦታ ሆኗል። በሚያስገርም መልኩ፥ ይህ ስጦታ በተሰጠበት ቀን የሆነው የዚህ የባቢሎን ታሪክ ግልባጭ ነበር። ማለትም፥ አንድ ቋንቋ ይናገሩ የነበሩ ሰዎች ቋንቋቸው ተደበላልቆ መበታተናቸው ሳይሆን የብዙዎች አገሮች ሰዎች በየቋንቋቸው አንድ መልእክት መስማታቸውና የእግዚአብሔርን ድንቅ ነገር መናገራቸው ነበር የሆነው፤ ሐዋ. 2፥1-11። ከዚህ ከሐዋ. 2 ክፍለ ምንባብ የምንረዳቸው ሁለት ነገሮች አንደኛው ጉዳዩ አይሁድን የሚመለከት መሆኑንና፥ ሁለተኛ፥ ቋንቋዎቹ የሚታወቁ ቋንቋዎች መሆናቸውን ነው። ይህ ነገር በዚያ ዕለት ያከተመ ሳይሆን እንደ ገንቢ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ በመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ ስጦታው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መሆን እንደሚገባው የሰጠውን መመሪያ በ1 ቆሮ. 14 እናገኛለን።

ልሳን ወይም በግሪክ ቋንቋ 'ግሎሳ' የተባለው ቃል በአዲስ ኪዳን አምሳ ጊዜያት ተጽፏል። ከእነዚህ ውስጥ ከፊል ያህሉ 'ልሳን' ሲሰኙ የቀሩት ደግሞ 'መላስ' (ለምሳሌ፥ ማር. 7፥33 እና 35፥ ሉቃ. 1፥64፥ 1ጴጥ. 3፥10፤ ወዘተ፥) 'ቋንቋ' (ለምሳሌ፥ ማር. 16፥17 እና ራዕይ 5፥9 ወዘተ፥) 'አንደበት' (1ቆሮ. 14፥9 ያዕ. 1፥26 እና 3፥5-8፤ 1ዮሐ. 3፥18 ወዘተ፥) ተብለው ተተርጉመዋል። ስለዚህ ልሳን በአንደበት የሚነገር፥ የቋንቋ መስፈርቶችን ሁሉ የሚያሟላ ቋንቋ ነው።

ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ ቋንቋዎች የተናገሩባቸው ቦታዎች ማለትም በሐዋ. 2፥4፥ ሐዋ. 10፥46 እና ሐዋ. 19፥6 'ልሳን' ተብለው ተጠቅሰዋል። በተረፈ ልሳን የሚለውን ቃል ከምችት የምናገኘው በ1ኛ ቆሮ. 12-14 ነው። እነዚህም እንደ ጸጋ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው የሚያመለክቱ የትምህርትና የሥርዓቱም ክፍሎች ናቸው። ቦታዎቹ፥

1ቆሮ. 12፥10፤ እና 28-30፤

1ቆሮ. 13፥1 እና 8

1ቆሮ. 14፥2-6፤ 13-19፤ 22-27 እና 39 ናቸው።

ልሳናት በቤተ ክርስቲያን የጉባኤ መታነጫ ስጦታዎች ናቸው እንጂ የግል አይደሉም። በእርግጥ፥ ተናጋሪው ሊታነጽበት የሚችልበት አንድ ገጽታ አለ። 1ቆሮ. 14፥4 *በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።* ይላል። ጠቅላላ መልኩ ግን፥ እንደ ሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ ልሳን ለቤተ ክርስቲያን መታነጫ የተሰጠ መሆኑ ነው። ልሳን ችግርና ሁከትም እንዳይፈጠር በስነ ሥርዓት መነገር እንዳለበትና፥ ማኅበሩ ይታነጽ ዘንድም የሚተረጉም ሰው በእርግጥ መኖር እንዳለበት የተነገረ ስጦታ ነው።

በጉባኤ ውስጥ ብዙዎች በልሳናት የሚጮኹበትን ሁኔታስ ከቃሉ አንጻር እንዴት እናየዋለን? አንዳንድ ጴንጤቆስጣውያንና ካሪዝማውያን አስተማሪዎች ልሳናትን ሁለት ቦታ ይከፍሏቸዋል፤ የግልና የጉባኤ ብለው። 'የጉባኤው የሚተረጎመው ሲሆን የግሉ ደግሞ ተናጋሪው የሚታነጽበት ነው፤' ይላሉ። እንዲያውም ከዚህ ራቅ የሚሉቱ፥ በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ወይም/እና የመጠመቅ ምልክት ስለሆነ በልሳን የማይናገር አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ገና አልተሞላም ወይም አልተጠመቀምና መጠመቅና መሞላት፥ ከዚያም በልሳኖች የመናገርን ስጦታ ሊቀበል ያስፈልገዋል ይላሉ።

ይህንን እና ሌሎቹንም የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ በዝርዝር በተመለከትንበት በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጠው፥ ምንም የግል ስጦታ የሚባል ነገር የለም። ልሳን ብቻ ግን ራስን እንደሚያንጽ ተገልጧል። ይህም በልሳን የሚናገረው ራሱን የሚያንጸው ምናልባት መተርጎም ባለመቻሉ ወይም ባለመተርጎሙ ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር በመጸለይ በውስጡ የመንፈስ ቅድስን ኀልውና ከመረዳቱ ወይም ከመሰማቱ እንጂ ሌላ መታነጽ አይደለም።

ሁሉ በልሳኖች መናገር እንዳለባቸው የሚያስተምሩ አስተማሪዎች የመጀመሪያ ጥቅስ ማር. 16፥17-18 ነው። በነዚህ ጥቅሶች ያመኑትን የሚከተሉ አምስት ምልክቶች ተጠቅሰዋል። ጥቅሱ የሚለው፤ *ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።* ከአምስቱም ግን ሁሉም ያለ ችግር ሊለማመዱት የተመረጠው በአዲስ ቋንቋ መናገር ነው። ቋንቋ እንደ ፈውስ በቀላሉ ሊረጋገጥ አይችልም። ይህ ጥቅስ ኮስተር ተብሎ ከተወሰደ የሁሉም ስጦታዎች ሚዛናዊነት፥ የመርዙና የእባቦቹም ጭምር መታለፍ የለባቸውም። በርግጥ ይህን እያደረጉ ችግር የደረሰባቸው እንዳሉም፥ 'እባብ ያዦቹና መርዝ ጠጪዎቹ' በሚለው ክፍል ተመልክተናል።

በቁጥር 16 ላይ ደኅንነትንና ፍርድን ሲገልጥ በነጠላ 'ያመነ የተጠመቀ፤ ያላመነ' ብሎ፥ ምልክቶችን ሲናገር ግን በወል፥ 'ያመኑትንም' ይላል። ከዚህ የምንረዳው አንድ ትልቅና

ግልጽ እውነት አለ፤ ይኸውም ያመነ የተጠመቀ ሁሉ እያንዳንዱ በነጠላ ይድናል። ያላመነም ሁሉ እያንዳንዱ በነጠላ አይድንም፤ ይፈረድበታል። ወደ ምልክቶቹ ስንመጣ ግን ሁለት ነገሮችን ልንመለከት ያስፈልገናል። የመጀመሪያው፥ (ሀ) በጅምላ ከመናገሩ የተነሣና (ለ) ከሌሎችም የአዲስ ኪዳን ምንባቦች እንደምንረዳው፥ ባመኑት ሁሉ ምልክቶቹ ሁሉ እንደማይከሰቱ እንገነዘባለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ማብራሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ሁለተኛው ነጥብ እነዚህ ምልክቶች ያመኑትን የሚከተሉ ናቸው እንጂ ያመኑት እነዚህን ምልክቶች የሚከተሉ አይደሉም። የምልክቶች ፈላጊና ተከታዮች መሆን እንደሌለባቸው መስተዋል ያለበት ነገር ነው።

ሌላው ልሳንን ያለ አግባብ የሚያቆራኙበት ጥቅስ በሮሜ. 8፥26-27 የተጻፈው የመንፈስ ማገዝና የመቃተት ነገር ነው። ቃሉ የሚለው መንፈስ ድካማችንን እንደሚያግዝና የመንፈስን አሳብ ስለሚያውቅ በማይነገር መቃተት እንደሚማልድልን ነው። *እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና።* ይላል። አንዳንድ ጴንጤቆስጣውያንና ካሪዝማውያን በዚህ ቃል ላይ በመመርኮዝ አንድ ሰው በልሳን ሲጸልይ በመንፈስ እየጸለየ እንደሆነ ያስተምራሉ።

በመንፈስ ስለመጸለይ ቀደም ሲል በአምልኮ ቀውስ ክፍል የተመለከትነው ነው። ይህ ክፍለ ምንባብ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ ድካማችንን ሊያግዝ ወይም ሊሸከምልን እና በውስጣችን ሆኖ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊጸልይ እንደሚወድ ነው። ጳውሎስ ከሮሜ. 6 እስከ 8 ባሉት ምዕራፎች ስለ ክርስትና ሕይወት ሲናገር በምዕ. 6 ለኃጢአት መሞትን ያብራራል። በምዕ. 7 ደግሞም ምንም እንኳ አንድ ሰው ለኃጢአት ቢሞትም፥ ነገር ግን በውስጡ የሚሠራ ሌላ ሕግ፥ ይኸውም የኃጢአት ሕግ የሚባል እንዳለ ይገልጣል። በምዕ. 7 የምንመለከተው የነዚህን ሁለት ሕጎች ጦርነት ነው። በዚህ ምዕራፍ የምናየው ሕይወቱ የእርስ በርስ ጦርነት ሜዳ የሆነ ጎስቋላ ሰው ጩኸት ሲሆን፥ ወደ ምዕ. 8. ስንመጣ ግን ሌላ ታሪክ ነው የምናነብበው። ለጦርነቱ አሸናፊነት፥ ለክርስትና ሕይወትም ስምረት የሚሆነው የሕይወት መንፈስ ሕግ የተባለው ሕግ በዚያ ሰው ሲሰለጥን ያ ሰው በአሸናፊነትና በጽናት ሲመላለስ ይታያል። የአሸናፊነቱም ምሥጢር መንፈስ ቅዱስ ነው። በጠቅላላው በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ 'መንፈስ' የሚለውና መንፈስ ቅዱስን የሚያመለክተው ቃል 26 ጊዜያት ሲጻፍ፥ ከ26ቱ ውስጥ 18ቱ በዚህ በአንዱ ምዕራፍ ማለትም በሮሜ. 8 ተከማችተው ይገኛሉ። በጠቅላላው በዚህ ምዕራፍ 'መንፈስ' 21 ጊዜ የተጻፈ ሲሆን ከእነዚህ 18ቱ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩት ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ መንፈስ ቅዱስ ከሚያደርጋቸው ነገሮች አንዱ የአማኙን የጸሎት ሕይወት መደገፍ ነው። ይህንም ጸሎት፥ 'የማይነገር መቃተት' ይለዋል። በልሳን መናገርና የመንፈስ ወይም የመንፈስ ቅዱስ መቃተት አንድ አይደሉም። ቃሉም አሳቡም አንድ አይደሉም። ይህ ጸሎት የልሳን ጸሎት እንደሆነ ማሳየት ቢወድስ ኖሮ ጳውሎስ በግልጽ፥ 'ልሳን' የሚል ቃልን በተጠቀመ ነበር። ነገር ግን በአማኙ ውስጥ ያደረው መንፈስ ቅዱስ ቃላት ሊገልጡት በማይችሉት መንገድ ይማልዳል። በምናውቀው ቋንቋ ብንጸልይ ያ ጸሎት በቃላት ይገለጣል፤ አንድ ሰው በልሳንም ቢናገር ወይም ቢጸልይ ቢያውቀውም ባያውቀውም ያ ቋንቋ ወይም ልሳን ቋንቋ ነውና የሚነገርና በቃላትም የሚገለጥ ነው። በዚህ ክፍል የምናየው ግን መንፈስ ቅዱስ የሚማልደው በማይነገር መቃተት ከአንደበት ተገልጦ በማይወጣ የውስጥ 'መናገር' ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሌላ አንድ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ያም፥ ሐዋ. 7፥34 ነው። የሕዝቡ የግብጽ ስቃይ መቃተት ተብሎአል። መቃተት አንደበታዊ ቋንቋ አይደለም። ለምሳሌ፥ ማቃሰትም ቋንቋ አይደለም ግን የሚያስተላልፈው መልእክት አለ። በማይነገር መቃተት ቃላት የማይገልጡት ጸሎት ነው። ስለዚህ የመንፈስ መቃተትና ልሳን አንድ አይደሉም። ልሳንን ከመቃተት ጋር ሊያመሳስሉት የሚሞክሩ ሰዎች ለልምምዱ ከተጻፈለት በላይ ሕጋዊነት ለማቀዳጀት የሚጥሩ ሰዎች ናቸው።

ከ1ቆሮ. 12፥10 በልሳኖች መናገር ከጸጋ ስጦታዎች መካከል አንዱ መሆኑን ከዚሁ ምዕራፍ ከጠቅላላው አሳብና በተለይም ከቁጥር 30 ደግሞ ሁሉ በልሳኖች እንደማይናገሩ በግልጽ እናገኛለን። ጥቅሱ፥ ቁጥር 30 የሚለው *ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን?* ነው። መልሱ ግልጽ የሆነ፥ 'የለም አይናገሩም።' የሚል ነው። ይህ የአጻጻፍ ዘይቤ ነው። በስነ ጽሑፍ፥ rhetorical question ይባላል። ጳውሎስ እንዲህ ያለውን የአጻጻፍና የማስተማር ስልት በብዙ ቦታዎች ያዘወትራቸዋል፤ ለምሳሌ፥ ሮሜ 6፥1። እንግዲህ የቃሉ ትክክለኛ ተርጓሚ ቃሉ ከሆነ፥ ቃሉ ደግሞ በማር. 16 እና በ1ቆሮ. 12-14 ባሉት ምዕራፎች ልሳኖችን በተመለከተ የተጠቀመው ቃል ተመሳሳይ ከሆነ፥ የግልና የጉባኤ ልሳናት የሚባሉት ከየት መጡ? እግዚአብሔርስ እንዲህ ነገሮችን አሻሚ አድርጎ በኛ መጫወትን ይፈልጋል? 'የግል' የሚባለው የማይተረጎመው ቋንቋ ከሆነ የማይተረጉመው ሰውየው መተርጎም ስላልቻለ መሆኑም መታለፍ የለበትም። ይህ ሰው ጉባኤው ይታነጽበት ዘንድ እንዲተረጉም መጸለይ እንዳለበትና መተርጎም ካልቻለ ደግሞ በጉባኤ ውስጥ ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር መናገር እንዳለበትም በግልጽ ተጽፏል።

በጴንጤቆስጣውያንና ካሪዝማውያን ዘንድ በጉባኤ ልሳን ሲነገር አነጋገሩ አንድ ዓይነት ነው። ብዙዎቹ ልሳኖችም አንድ ዓይነት ናቸው፤ ወደዚያ እመጣለሁ፤ እዚህ ግን አነጋገሮቹ አንድ ዓይነት መሆናቸውን ነው ያልኩት። ይህም በራሱ ከአንድ ምንጭ የተኮረጀ መሆኑ ይታያል። የተለመደው አነጋገር አንድ ሰው በልሳን ይናገርና ከዚያ

ራሱ ያንን የተናገረውን ነገር በሰሚዎቹ ቋንቋ ይተረጉመዋል። ልሳኑ ወይም ቋንቋው የሰሚዎቹ አይደለም። ያንን ልሳን ወይም ቋንቋ ሳይናገር ለምን በቀጥታ ትርጉሙን አልተናገረም? ተናጋሪውም ተርጓሚውም እራሱ ከሆነ ነገሩን ያውቀዋል። ግን እንዲያ ካደረገ ከተለመደው አደራረግ፥ ወይም ልምምድ፥ ወይም ኩረጃ መውጣት ይሆናል። ስለዚህ ሰሚዎቹ ባያውቁትም፥ ነገሩ ቋንቋ ይሁን አይሁንም ባይታወቅም ብቻ ይነገርና ይተረጎማል። ቢሆንማ፥ እንደ ቃሉ ቢደረግማ ትርጉምም ባላስፈለገ ነበር።

በልሳኖች መናገር ከሌሎቹ ስጦታዎች ተለይቶ ልዩ ቦታ ስለሚሰጠው የጉባኤ መገንቢያ በመሆን ፈንታ በብዙ ቦታዎች መለያያ ማፍረሻ፥ ያልዳኑትን ማስበርገጊያ፥ የሚናገሩትን ማስታበያ፥ የማይናገሩትን ማንኳሰሻ እየተደረገ ይታያል። አንዴ ልሳን ሁለት ዓይነት ተደርጎ ከተስተማረ የትኛው የትኛው መሆኑን ለመለየትም ሆነ ለመቀበል ያዳግታል። ይህን የሚያውቀው ተናጋሪው ብቻ ሊሆን ነው ማለት ነው። ሰዎች ግራ መጋባታቸው ይበዛል። በጉባኤ ሥርዓት አልባነት የሥርዓትን ቦታ ይይዝና እዚህ አንዱ፥ እዚያ ሌላዋ ያሻቸውን ይላሉ። በ1ቆሮ. 14፥22 *እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።* ተብሎ እንደተጻፈው ልሳን ወይም ቋንቋ ለማያምኑ ምልክት መሆን ሲገባው፥ ማለትም ያ ሰው ልክ እንደ ሐዋ. 2 የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ድንቅ ነገር በገዛ ቋንቋው መስማት ሲገባው፥ ቀጥሎ ባለው ጥቅስ፥ 1ቆሮ. 14፥23 እንደተጻፈው፥ *እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ፦ አብደዋል አይሉምን?* የሚያሰኝ ዓይነት ነገር እየተደረገ ይታያል።

አልፍሬድ ኤች ፖል የተባለ ሰው ለብዙ ዓመታት በልሳኖች መናገርን በመንፈስ ቅዱስ እንደ መጠመቅና መሞላት ዋና ምልክት አድርጋ በምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ሲያስተምርና ሲያገለግል ከኖረ በኋላ የማይዋጡለት ነገሮች ሲበዙና እነዚህንም ከቃሉ አንጻር ሲመረምር ያፈነገጡ ሆነውበት ሊወጣ ችሏል። ከዚህ በኋላ በጻፈው 'የልሳናትን ንቅናቄ የተውኩባቸው አስራ ሰባት ምክንያቶች' (17 Reasons Why I Left the Tongues Movement) በተባለው መጽሐፉ የወጣበትን ምክንቶች በሰፊው ጻፈ። ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም ከምክንያቶቹ ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው፤

- ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጤንነቱ ሙሉ ያለመሆኑ፤
- ከመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ውስጥ አንዱ ብቻ ማለትም ልሳን መጉላትና መታየቱ፤
- በግላዊ 'ልምምድ' ማለትም በሰብዓዊ ልምምዶች መደገፍ፤

- የመንፈስ ቅዱስ አካልነት ወይም አምላክነት ዝቅ ማለቱ፤
- በልሳኖች መናገር የመንፈሳዊነትና እንዲያውም የደኅንነት ምልክት ተደርጎ መታየቱ፤
- 'የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ናቸው' የሚባሉትን ነገሮች ያለ ምንም ጥርጣሬና ጥያቄ ለመቀበል መገደድ፤
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ መገለጦች መኖራቸው፤
- መሪዎችን ልክ ዕውር መሪውን ያለ ምንም ጥያቄ እንደሚከተል መከተል፤
- እውነተኛው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የሚለው አሳብ መዛባቱ።[27]

የልሳኖች ስጦታ አንድ ብቻ ነው ያም ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት መንፈስ ቅዱስ የሰጠው በሌላ ቋንቋ የመናገር ስጦታ ነው። ይህ ስጦታ በጉባኤ በሚነገርበት ጊዜ ተናጋሪው ወይም ሌላ ሰው መተርጎም አለበት። የግል ልሳን የተሰጠው የሚመስለው ማንም ቢኖር ይህ ነገር በእውነት ችግር አይፈጥርም ምክንያቱም ይህ ሰው ስጦታው እንዳለው ከራሱና ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለም። በጉባኤ ከተናገረው መተርጎም እንደሚጠበቅበት ያውቃል በእልፍኙ ለሚናገረው ግን የሚባረከውም ተጠያቂውም ራሱ ነው።

አሁንም አንዳንድ አስተማሪዎች የሁለቱን ልዩነት ለመግለጥ የጉባኤ ቋንቋን የሚታወቅ ወይም የሚተረጉም ልሳን ሌላኛውን ደግሞ ሌላ የማይታወቅ ምንም ሰሚውም ሆኑ ተናጋሪውም የማያውቀውና ሊተረጉመውም የማያስፈልገው ቋንቋ አድርገው ያስተምራሉ። ይህንንም 'በእንግዳ ወይም በማይታወቅ ቋንቋ መናገር' (Xenoglossolalia) ይሉታል። በ1ቆሮ. 13፥1 የሰዎችና የመላእክት ቋንቋ መኖሩን፥ በ1ቆሮ. 14፥10 ደግሞ የሰዎች ቋንቋ ብዛቱ እጅግ እንደሆነ እናገኛለን። እርግጥም የቋንቋ ብዙነትና ዓይነት አሌ የማንለው እውነት ነው፤ ነገር ግን በልሳኖች የመናገር ስጦታ ሲሰጥ በልሳኖች የተነገረውን የመተርጎም ስጦታም የተሰጠበት ምክንያት ለዚህ መሆኑ መታለፍ የለበትም። መላእክትም ቢሆኑ ለሰው ሲናገሩ በሰው ቋንቋ መሆኑ የታወቀ ነው። መላእክት ተገልጠው ለሰዎች በተናገሩባቸው ጊዜያት ሁሉ የሰዎቹን ቋንቋ ነው የተናገሩት።

ልሳንን እንደስጦታ ማለትም ከጸጋ ስጦታዎች እንደ አንዱ ሳይሆን እንደ ምልክት ማለትም እንደ መንፈሳዊነት ማረጋገጫ ምልክት ማየት የዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊና ካሪዝማዊ ንቅናቄ አንዱ የተሳሳተ አዝማሚያ ነው። ልሳን የመንፈሳዊነት ማረጋገጫ አይደለም። ማንም በቅርብ የሚያየውና እንደሚረዳው በልሳኖች የሚናገሩት አማኞች

እንደ ስጦታነቱ በመረዳት ጉባኤውን ከሚያንጹበት ይልቅ እንደ መንፈሳዊነት የመታወቂያ ምልክት ማውለብለቡን ነው የሚመርጡት። በልሳን መናገር ልዩ መንፈሳዊነት፥ እርከንን የመሻገርና ከሌሎች የተሻሉ የመሆን ምልክትስ ቢሆን ኖሮ እንዲህ የሚያደርጉት ሲዝሉ፥ ሲንሸራተቱና ሲወድቁ መታየት አልነበረበትም ነበር። እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስጦታዎች አሉ። ምንም አልጎደሉባቸውም፤ 1ቆሮ. 1፥7። በልሳኖች መናገር እንዲያውም ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን ይህ ርዕስ ሦስት ምዕራፎች ላይ ከመጻፉ እንረዳለን። ነገር ግን የቆሮንቶስ ምዕመናን 'ሥጋውያን' ተብለው የተወቀሱ ምዕመናን ነበሩ። ከ1ኛ ቆሮንቶስ እንደምንረዳው ሦስት ዓይነት ሰዎችና ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች አሉ። ሁለቱ ዓይነት ክርስቲያኖች በልሳን የሚናገሩና የማይናገሩ ሳይሆኑ ሥጋውያንና መንፈሳውያን ተብለው የሚታወቁት ክርስቲያኖች ናቸው። በየትኛዋም ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓይነት ሰዎች አናገኝም። በቆሮንቶስም እንዲሁ። የቆሮንቶስ ምዕመናን ግን በግልጽ ሥጋውያን ተብለው ተወቅሰዋል።

የአንድ ሰው የመንፈሳዊነቱ መለኪያው የጸጋው ስጦታ ሳይሆን፥ መንፈሳዊ ሕይወቱና መንፈሳዊ ፍሬው ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው በምልክት መታወቅ ካለበት እንደ ምልክት ተደርገው የሚወሰዱ ነጥቦች ሊኖሩ ይችላል። ስለዚህ አሳብ ከላይ የተጠቀሰው ሲናገር፥

> ምንም እንኳ በአንድ ወቅት በልሳናት መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላትና የመንፈሳዊነት ምልክት እንደሆኑ ባምንና ባስተምርም በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን አማካኝነት አመለካከቴን መለወጥ ነበረብኝ። . . . አሁን በእውነት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ወይም የመንፈሳዊ ክርስቲያን ምልክት ወይም ባሕርያት ናቸው ብዬ የማምናቸው፤
>
> 1. የተሰቀለ፥ ራስን የካደ ሕይወት (ይህ የአንድ ጊዜ ልምምድ ሳይሆን ሕይወት ነው።) ገላ. 2፥20፤ 6፥14።
>
> 2. የተማረከ ሕይወት የተገዛና ለጌታ የተሰጠ ሕይወት። የሰው ፈቃድ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሲገዛ። ሮሜ 6፥13-19፤ 12፥1-2
>
> 3. ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት። ገላ.2፥20፤ ሮሜ 8፥29
>
> 4. ፍሬያማ ሕይወት የመንፈስ ፍሬ ሲገለጥ። ዮሐ. 15፥፥8፤ ገላ. 5፥22-23
>
> 5. በክርስቶስ አገልግሎትና ምስክርነት ውጤታማ ሕይወት፤ ሐዋ. 1፥8፤ 4፥31
>
> 6. እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት። 1ኛ ቆሮ. 6፥20። ናቸው።[28]

አንዳንድ ሰዎች ልሳንን ከመፈለጋቸው የተነሣ ለማግኘት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ይህ ከልሳን ቀውሶች መገለጫዎች አንዱ ነው። ይህን ለማግኘት አንዳንዴ

ምንም መንፈሳዊነት ያልተደባለቀባቸው ሰው ሰራሽ ቴክኒኮች ይደረጋሉ። እነዚህ ነገሮች በሚደረጉበት ወቅት ለሚሆነው ሁሉ ኃላፊነቱ የፈላጊውም የጸላዩም ነው። ከሚደረጉት ነገሮች መካከል ለምሳሌ፥ የሚጸለይለት ሰው ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲጸልይ ይነገረውና የሚጸልይለት ሰው (ሰዎችም ሊሆኑ ይችላሉ) ደግሞ እጆቹን በማንቀጥቀጥ ሰውነቱን በግድ ያንዘፈዝፈዋል። በዚህ ጊዜ እጆች የተጫኑበትና የሚጸለይለት ሰው ድምጽ መንዘርና መንቀጥቀጥ ሲጀምር በዚያ መልክ እንዲቀጥል ያደፋፍሩታል። አንዳንድ የተመረጡ ቃላትንም በተለይም 'ሃሌሉያ' የሚለውን ቃል እንዲደጋግማቸውና በፍጥነት እንዲላቸው በማድረግ እነርሱ ወደሚሉትና ወደሚፈልጉት ልምምድ እንዲጠጋ ይነገረዋል ይደረጋልም።

አንዳንዶች ጸላዮችማ በጣም ከመጓጓታቸው የተነሣ የሚጸልዩላቸውን ሰዎች ጉንጭና መንጋጭላ፥ አገጭና ምላስ ሁሉ ሳይቀር በመነካካት ልዩ ድምጽ ለመፍጠርና ለማስፈጠር ይጥራሉ፤ ይተጋሉ። አንዳንዶችም በግልጽ አንዳንድ የተመረጡ ሐረጎችን እንዲሉ ያስተምራሉ፤ ሲያስተምሩም አንዳንዶቹን ቃላትና ሐረጎች ቋንቋነታቸው ቀርቶ ድምጽ ብቻ እስኪሆኑ ድረስ በፍጥነት እንዲነገሩ ያደርጋሉ። እነዚያም ያንን እየኮረጁ ይሉታል። ይህ ዘመናዊና ሰው ሰራሽ ስልት እንጂ በአዲስ ኪዳን እንዲህ ያለ ታሪክ ሲደረግ አልታየም። የብዙዎች ልሳኖች ተመሳሳይ የሆኑ መስሎን ያውቃል? ከሆነ ሊደንቀን አያስፈልግም። በእርግጥም ተመሳሳይ ነው። ከተመሳሳይነቱ ምክንያቶች አንዱ ይህ እንዲሉ የሚለማመዱት ነገር ነው። ሌላው የተመሳሳይነት ምክንያት ደግሞ፥ የአንድን ሰው በልሳን መናገር ብዙ ጊዜ ደጋግሞ መስማት ነው። ያንን ሲሰሙና ሲሸመድዱ የኖሩት አንድ ቀን ገንፍሎ ይወጣል። ከዚያ መቀጠሉ ቀላል ነው።

በአዲስ ኪዳን ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዎች በልሳኖች በተናገሩባቸው ሦስት ምዕራፎች (ሐዋ. 2፤ ሐዋ. 10 እና ሐዋ. 19) ውስጥ ይህንን መሳይ ነገር አናይም። በሁሉም ምዕራፎች በልሳኖች ለመናገር ሲጠብቁ ወይም እንናገራለን ብለው ሲጠባበቁም አናይም። በመጀመሪያውም እንኳ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት እንጂ፥ እንዴት እንደሚመጣና ከመጣም በኋላ ምን እንደሚፈጽም አያውቁም ነበር። በልሳን እንዲናገሩ የሚደረጉ ሰዎቸ በሚጸለይላቸው ጊዜ በአዕምሮአቸው እንዲጸልዩና የሚጸልዩትንም ነገር በሚያውቁት ቋንቋ እንዲናገሩት አይፈቀድላቸውም ወይም አይበረታቱም። ይህን ማድረግ 'አሸንዳውን እንደ መዝጋት' ነው የሚቆጠረው። ቃላትን አብዝቶ ከመደጋገምና አፍጥኖ ከመናገር የተነሣ የሚነገረውን ያንን ነገር ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ስጦታ ነው? ወይስ ሰው ሠራሽ ልሳን ነው የምንለው? በሐዋ. 2፥4 እንደምናነብበው እነዚያ የተናገሩት 'መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው' ነበር እንጂ ተምረውና ተለማምደውና ሰልጥነውበት፥ ወይም ተገፋፍተውና ተደፋፍረው ከቶም አልነበረም።

በልሳናት መናገር በማርቆስ ወንጌል ምዕ. 16 በሐዋርያት ሥራ ሦስት ምዕራፎች፥ 2፤ 10 እና 19፤ እንዲሁም በ1ኛ ቆሮንቶስ ሦስት ምዕራፎች፥ 12፤ 13 እና 14 ተጽፈዋል። በሐዋ. 8 እንዳለ ይመስላል እንጂ በግልጽ አልተጻፈም። ሐዋ. 8 ዋናውና ከሌሎቹም ይልቅ የሚመረጠው የካሪዝማዊ ንቅናቄ እንዲሁም የልሳኖች ንቅናቄ መነሻ አሳብ ነው። በዚህ ክፍል ብቻ አስቀድመው በዳኑት ላይ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ ወይም ሲቀበሉ እናያለን። ይህም የሆነው ሐዋርያት ከሄዱና እጃቸውንም ከጫኑባቸው በኋላ ነበር። በሰማርያ ወንጌልን የሰበከው ፊልጶስ ሲሆን ፊልጶስ ወንጌላዊ እንጂ ሐዋርያ አልነበረም። እግዚአብሔር የሐዋርያትን እጅ መጫን ለሥልጣናቸው ምልክትም፥ ለአንድነታቸው መሠረትም ይሆን ዘንደ ነው የተጠቀመው። በአይሁድና በሳምራውያን መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳም ማፍረሱ ነው። ከሐዋ. 8 በቀር በቀሩት በሦስቱ የሐዋርያት ሥራ ቦታዎች ሰዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈስ ቅዱስንም በልሳኖች የመናገር ስጦታንም ሲቀበሉ እናያለን። ከእነዚህ ክፍሎች ሁሉ እንደምንረዳው፥ ልሳን ማለት ሰዎች ያልተማሩት መንፈስ ቅዱስ የኀልውናው ምልክት አድርጎ ከገለጣቸው ስጦታዎች አንዱ ሲሆን የጉባኤ ሰሚዎች ቋንቋውን ካወቁት ጥሩ፤ ካላወቁት ግን ሊተረጎምላቸው የተገባው ቋንቋ ነው። ልሳን ቋንቋ ነው። ከነዚህ ሦስት ጸሐፊዎች (ማርቆስ፥ ሉቃስ፥ ጳውሎስ) እና ሰባት ያህል ምዕራፎች እንደምንረዳው በልሳን መናገር የሚያንጽ ስጦታ እንጂ፥ መናገር የመንፈሳዊ ብስለት፥ ያለመናገር ደግሞ ያለመብሰል ምልክት መሆናቸውን አይደለም።

ከ3ኛው ሞገድ ንቅናቄ መሪዎች መካከል የሆነው ጆን ዊምበር የተባለው ሰው መንፈስ ቅዱስ በሰው ላይ ሲወርድ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚፈጥር ሲናገር እንዲህ ብሏል። 'መንቀጥቀጥን፥ መራድን፥ መውደቅንና መገንደስን፥ እንደሰከረ ሰው መንገድገድንና ወደ ላይና ወደ ታች መዝለልን፥ የእጅ መኮማተርንና የጣቶች መዘረጋጋትን፥ የሰውነት መድረቅንና የፊት መኮማተርን፥ የዓይን መርገብገብንና ቁና ቁና መተንፈስን፥ ሙቀትንና በላብ መስጠምን፥ ሁሉ ያጠቃልላል።'[29] እነዚህ ነገሮች የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል ነገር ነው። የአንድ መንፈሳዊ ትምህርት ማረጋገጫ ደግሞ የሰዎች ልምምድ በሚሆንበት ጊዜ በተመሳሳይ ሰዓት ሁለት ስሕተቶች ይፈጸማሉ፤ እነዚህም፥ አንደኛው፥ የሰዎችን ነገር ማጉላት ሲሆን፥ ሌላው፥ የቃሉን ክብደት መቀነስ ነው። ነባራዊ የሆነውን ቃል ተለዋዋጭ የሆነውና ጥልቀት የሌለው የሰው ልምምድ ከሸፈነው አደገኛ ችግር ይፈጠራል። የሰውን ልምምድ የመጽሐፍ ቅዱስ መደገፊያ ምርኩዝ ማድረግና ልምምዱ በቃሉ ውስጥ ካልተገኘ ቃሉን እንደሚመች አደርጎ ወደ ልምምዱ እንዲጠጋ መተርጎም ወደ ማጥ የሚከት መንገድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ድጋፍና ያለ ልምምዳዊ ማስረጃ በራሱ ችሎ መቆም የሚችል መለኮታዊ ቃል ነው። ዝኆንን በሰንበሌጥ አይደግፉም።

በሁለመናው ሙሉ የሆነውን መለኮታዊ ቃል በሰዎች ልምምድ ለማቅናት የሚደረግ ጥረት ሁሉ ረብ የለውም፤ ፍጻሜው አያምርም።

የሃይማኖት ምሁራን እንደሚናገሩት በተለያዩ ኃይማኖቶች አንዳንድ የተመሳሰሉ ሥርዓቶች አሉ። ከነዚህም መካከል መቅቀየር ወይም መልለወጥ (conversion)፥ መሥዋዕት ማቅረብ፥ የአምልኮ ሥርዓተ-ቅዳሴ፥ ጸሎት፥ በአምልኮ ወቅት በደስታ መጨፈርና በሌሎች ቋንቋዎች መናገርም ይገኙባቸዋል። በተለይ በኋለኛው ዓይነት ልምምድ፥ ማለትም በሌሎች ቋንቋዎች መናገር በሚከሰትበት ጊዜያት፥ ማጓራት፥ ማቃሰት፥ መጮህ፥ መግዘፍ፥ መንቀጥቀጥ፥ መውደቅ፥ መዝለል፥ መደነስና የመሳሰሉት አካላዊ እንቅስቃሴዎች እንደሚታዩ ይናገራሉ። ኩንዳሊኒ የተባለው ሃይማኖት የዚህ አንድ ምሳሌ ነው። ብዙዎችም በእንዲህ ያለው ኢጋጣሚ የታመቀ ስሜታቸውን ሊያፈስሱትና ሊቀንሱት ምቹ ይሆንላቸዋል። ኃይማኖቶችን በእንዲህ ያሉ መለኪያዎች የሚመዝኑ ምሑራን ክርስትናንም ከብዙዎቹ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች እንደ አንዱ ብቻ አድርገው ይወስዱታልና የምናደርገውን ሁሉ በማስተዋል ማድረግ አለብን።

በልሳኖች መናገር በዚህ ዘመን እንደሌለ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች (ወይም ሴሴሽኒስቶች) 1ቆሮ. 13፥8ን በማብራራት ይጠቅሳሉ። በዚህ ክፍል ትንቢትና ዕውቀት እንደሚሻሩ፥ ልሳኖች ደግሞ እንደሚቀሩ ይናገራሉ። ‘ይቀራሉ’ የሚለው አሳብ ያበቃሉ፥ ሥራቸውን ያቆማሉ፥ ወይም በራሳቸው ይቆማሉ የሚል አሳብን የያዘ ነው። ከሐዋርያት ዘመን በኋላም ስለ ብዙ ነገሮች በጻፉልን በአብያተ ክርስቲያናት አባቶች በነአውጉስጢኖስ፥ ሰማዕቱ ኢዮስጢን፥ አርጌንስ፥ ዮሐንስ ክሪሶስተም ወይም አፈወርቅ ይህ ነገር፥ ማለትም፥ ልሳን አለመጠቀሱን እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ። በዚህ ዘመን የሚሰሙትም ልሳኖች ምንጭ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ሌላ እንደሚሆን ያስተምራሉ።

ከሐዋርያት ታሪክ በኋላ ልሳን የተጠቀሰው በሞንታኖሳዊው እንቅስቃሴና ለተወሰነ ጊዜ ከዚህ ትምህርት ጋራ ከተቆራኘው ከጠርጡልያኖስ ጽሑፎች ነው። ከዚህ በኋላ በመጠኑም ቢሆን ሰፋ እየተደረጉ የተነገረላቸው በልሳን የመናገር ልምምዶች በ1730ዎቹ በሮም ካቶሊክ ውስጥ የሚገኙ ጃንሰናውያን የሚባል ቡድን ነው። ከነዚህ ጥቂት ቀደም ብሎ ደግሞ በፈረንሳይ አገር የሚገኙ ጥቂት ቄሶች ስለ ልሳን ያውቁ ነበር። ክርስቲያን ባልሆኑ ሃይማኖቶችም ልሳኖች ቢገኙም፥ ልሳንን በመጥፎ መልኩ እንዲታወቅ ያደረጉ ክርስትናን የተላበሱ የስሕተት ትምህርቶችም ነበሩ። ‘ሼከርስ’ ወይም ተንቀጥቃጮቹ በመባል የሚታወቁት ሰዎች እምነት ማዘር አን ሊ በምትባል በ18ኛው መቶ ምዕት ዓመት በኒውዮርክ በነበረች ሴት የተመሠረተ ሲሆን ይህች ሴት እርሷ የክርስቶስ እንስት እኩያው ወይም ሴት ክርስቶስ እንደሆነች በማስረዳት አዲስ መገለጥን እንደተቀበለች ማስተማር ጀመረች። ይህች ሴት ማናቸውም ዓይነት ወሲባዊ

ግንኙነትን፥ በጋብቻ ውስጥም የሚገኝን ጭምር ታጥላላ ነበር። ሥጋን ማለትም አሮጌውን ባሕርይ ለመግደል ተከታዮችዋ ዕርቃናቸውን በመሆንና በልሳን እየተናገሩ እንዲደንሱ ታደርግ ነበር፤ በዚህም ፍትወታዊ አምሮት ሊሸነፍ እንደሚችል ታስተምር ነበር። ተንቀጥቃጮቹ የሚለው ስያሜ ከዳንሳቸው ጋርም የተያያዘ ነው።[30]

የልሳኖችን ምንጭ ስንመረምር እንግዲህ ሁሌም መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንዳልሆነ መመልከት አያዳግትም። መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ ከሚያድለው በልሳኖች የመናገር ስጦታ ባሻገር ሰዎች ከሌላ ምንጭም ሊቀዱ ይችላሉ። በእርግጥም ይህንን ማድረግ እንደሚችሉ ጆን ኤፍ ማካርተር ሲጽፍ ሰይጣናዊ ስነ-ልቡናዊና በልምምድ ማለትም በመኮረጅ የሚገኝም ሊሆን እንደሚችል አብራርቷል።[31] ሥስነ-ልቡናዊ ሲል በፈቃድ መቆጣጠር የምንችላቸውን የሰውነታችንን ክፍሎች ለምሳሌ፥ ጡንቻዎቻችንን፥ ድምጻችንን፥ ሌሎችም ነገሮቻችንን በአዕምሯችን መቆጣጠር በማቆም ራሳቸው በራሳቸው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ በመጀመር የሚገቡበት ልምምድ ነው። ልክ ፓይለት አውሮፕላንን በራሱ እንዲሄድ የሚያደርግበትን ጥበብ የሚመስል ነው። በስነ-ልቡና ተመራማሪዎች ዘንድ ይህ 'ሞተር-አውቶማቲዝም' ይባላል። እንዲህ ያለ ነገር ውስጥ የሚገቡ ሰዎች ፈቃዳቸው ወይም አዕምሯቸውን ቢያስሩት ሊያደርጉ የማይችሏቸውን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ። ሰዎች ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሲጸልዩ 'አዕምሯችሁን ክፍት አድርጉ፥ ራሳችሁን ባዶ አድርጉ፥ ብዙ ነገር ላለማሰብ ሞክሩ' ወዘተ፥ የሚባሉት ዓይነት ነገሮች አደገኛ የሚሆኑት ለዚህ ነው። እኛ ሳናቋርጥ የተሞላን እንድንሆን እንጂ ባዶ እንድንሆን አልተነገረንም።

በመኮረጅ የሚገኘው ልሳን ደግሞ ግልጽ ነው። ክርስቲያኖች ከሌሎች ክርስቲያኖች መኮረጅ ያለባቸው ብዙ የኑሮና የክርስቲያናዊ ሕይወት ዘይቤዎችና ልምምዶች አሉ። የጸጋ ስጦታን መኮረጅ ግን መደረግ የሌለበት ነገር ነው። ምክንያቱም ይህን የሚሰጠው መንፈስ ቅደስ እንጂ ሌላ ማንም መሆን የለበትም። በዘመናችን ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ሰዎች የጸጋን ስጦታ በተለይም በልሳኖች መናገርን ይኮርጁታል። ትንቢትን መናገርንና ፈውስንም በመኮረጅ እየቀዱ ሊያገለግሉ የሚሞክሩ ጥቂቶች አይደሉም። ለዚህም ነው ብዙ ሐሰተኛ ትንቢቶችና፥ ስሜታዊና ውሸታም ፈውሶች የሚሰሙት። ልሳን ግን እንደ ሕመም ለመለየት ስለሚያስቸግርና የተደፋፈነም ስለሚሆን የተኮረጀ መሆኑን ማንም ላያስተውለው ይችላል። ነገር ግን በልሳኖች መናገር ከሌሎቹ ሁሉ ስጦታዎች ይበልጥ ይኮረጃል፤ ለዚህም ነው የብዙዎቹ ተናጋሪዎች ቃላትና ሐረጎች አስከሚያስገርም ድረስ ተመሳሳይ የሚሆኑት። የብዙ ሰዎች ልሳናት ተመሳሳይ ሆነውብን ያውቃሉ? መገረም የለብንም። ብዙዎች ለሚናገሩት ልሳን ተመሳሳይነት አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች የሚሰጡት ምላሽ ይህ በግድና በኩረጃ የሚገኝ ልምምድ መሆኑን ነው።

በልሳኖች መናገር በሌሎችም ኃይማኖቶች ዘንድ በሚገባ የታወቀ ነገር ነው። ለምሳሌ፥ በምሥራቃውያን ኃይማኖቶች፥ በሱፊ እስልምና፥ ክርስትናን በሚመስሉ የስሕተት ትምህርቶች (ለምሳሌ፥ ከላይ የጠቀስኩት የሼከርስ ልምምድ)፥ በአምልኮተ ሰይጣን (ለምሳሌ፥ በአገራችን የቃልቻና የውቃቢ የአምልኮ ሥርዓቶች) እንዲሁም በመሳሰሉት ይገኛሉ። ኩንዳሊኒ ቀደም ሲል ስሙን ብቻ የጠቀስኩት የሂንዱ ሃይማኖት አንድ ገጽታ ነው። የቃሉ ትርጉም የተጠቀለለ እባብ ማለት ሆኖ የእንስታዊ አምላክ ኃይል እና መንፈሳዊ አርነት የመጎናጸፍ መንገድ ተብሎ ይታወቃል። በኩንዳሊኒ አምልኮ ወቅት መግዘፍ፥ መንቀጥቀጥ፥ ራስን አለመቆጣጠርና በልሳኖች መናገር የተለመዱ ናቸው። እነማን መሆናቸውን የማያውቅ ሰው እነዚህንና ጴንጤቆስጣውያንን ለመለየት ይቸገራል። ለነዚህ ሰዎች በልሳኖች ወይም በሌላ ቋንቋዎች መናገርን መንፈስ ቅዱስ እንዳልሰጣቸው በማያወላዳ መንገድ እጅግ በጣም ግልጽ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ካልሰጣቸው ታድያ ማን ሰጣቸው? አሁንም ምንጩ ግልጽ ነው። ሰይጣን አስመሳይ ሠራተኛ መሆኑን አንዘነጋውም። አስመሳይነቱም በግልጽ ተጽፎልናል። ራሱን ሲለውጥ የብርሃን መልአክ እንኳ ሊመስል እንደሚችልና በመጨረሻውም ዘመን ደግሞ የሚያምኑትን እንኳ ሊያስት እንደሚሞክር ተጽፎልናል፤ 2ቆሮ. 11፥15፤ ማቴ. 24፥24። ሰይጣን ማፍራት የማይችለው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን ነው እንጂ ስጦታዎቹንስ መሥራት ይችልበታል። ሰይጣን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን አስመስሎ ቢያመርት ሊያስደንቀን አይገባም። አስመስለው የሚሠሩት ነገር ድሮም የከበረ ነገርን ነው። ርካሹንማ ማን አስመስሎ ይሰራዋል? ለምሳሌ፥ ሐሰተኛ የገንዘብ ኖቶችን የሚሠሩት ባለ ኀምሳ ባለ መቶ እና ከዚያም በላይ የሆኑትን እንጂ ባለ አንድ ብር ገንዘቦች እየሠሩ ጊዜያቸውን እውቀታቸውንም ሆነ ጉልበታቸውን አያባክኑም። አምስት ብርና አንድ ሺ ብር ለመሥራት እኩል ከጠየቀ ለምን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ይከሰር? የውሸት ማኅተም የሚሠሩ ሰዎች የትንሽ ኪዮስክ ማኅተም ከሚሠሩ ይልቅ የትልቅ አገር ማኅተም ቢሠሩ ይመርጣሉ። በሥልጣን ማጭበርበር ይችላሏ! የጸጋ ስጦታዎች የከበሩ ናቸውና ተምሳሌታቸውን ሰይጣን ከቶም እንዲህ በቀላል በማያስታውቅ ሁኔታ እንደሠራና ወደ ፊትም ይበልጥ እያሻሻለ እንደሚሠራ ቅዱስ ቃሉም፥ ታሪክም፥ ዘመናችንም ይነግሩናል።

አዲሱ ጴንጤቆስጣዊነት በተጀመረበት የቶፒካው እንቅስቃሴ ጊዜ ልሳን የሚስዮናዊነት ቋንቋ ነው ተብሎም ተነግሮ ነበር። በዚያ ንቅናቄ በመጀመሪያ በልሳን የተናገረችው አግነስ ኦዝማን ኋላ፥ በልሳን መናገር ብቻ ሳይሆን በልሳን መጻፍም ጀምራ ነበር። ይህኛው አስቂኝ ታሪክ ነው። ስጦታዎች እንዴት በሰዎች እንደሚሻሻሉ ሲታሰብ ያስገርማል። እነዚያ ቋንቋዎች መጻጻፊያና መጽሐፍ ቅዱስ የሚተረጎምባቸው፥ እንዲሁም ሰዎች ወደ ሚስዮናዊነት ሲላኩ የሚናገሯቸው ቋንቋዎች መሆናቸውንና

ሚስዮናውያን በሚሄዱባቸው አገራት በቀጥታ ከሰዎቹ ጋር ይግባባሉ እንጂ ቋንቋ በመማር ዓመታት መቆየት የለባቸውም የሚል እምነት ላይም ደርሰው ነበር።



Agnes Ozman writes in tongues. 1901

ቤተ ክርስቲያን የተሰጧት ስጦታዎች ሽንቁርና ቀዳዳ ኖሮባቸውና ከመንፈስ ቅዱስ ሌላ የሆነ መንፈስ ገብቶ እንዳያወናብዳት እጅግ ልትጠነቀቅ ይገባታል። ሐሰተኛው መሢሕ የሚያምኑትን ሊያስት የሚሞክረው በአንዳንድ ሥዕሎች እንደምናየው ቀንዳምና ጥፍራም፥ ጅራታምና ኮቴያም ሆኖ በመምጣት አይደለም።

ቶኒ ካምፖሎ የተባለው የማኅበራዊ ጉዳዮች ምሑርና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መንፈስ ቅዱስ በአብያተ ክርስቲያናት ስለሚሠራቸው ግሩም ሥራዎች ከተናገረ በኋላ በአንጻሩ ደግሞ ስላለው በሰዎች አማካይነት የሚደረግ መጥፎ ገጽታ ሲገልጽ፤

> በሌላ በኩል ደግሞ የሚያሰድቡና እንግዳ ነገሮች በጴንጤቆስጣዊነት ስም እንደተደረጉ አልክድም። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚደረጉትን ነገሮች መመርመር እንደሚገባን ይነግረናል፤ እንዲህ ሲል፥ 'ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ። ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።' (1ዮሐ. 4፥1) በእምነት እድገት ውስጥ የሚከሰቱ ማናቸውንም ነገሮች መመርመር የክርስቲያን ኃላፊነት ነው። ይህ ነገር በተለይ በጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ብዙ የተጭበረበሩ ነገሮችና ስሕተቶች እየተፈጸሙ ባሉበት እንደ አሁኑ ባለው ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ነው።[32]

በልሳናት መናገርና ትንቢትን መናገር ከሌሎቹ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ይልቅ ሰፋ ያለ ትንታኔ ተሰጥቶአቸዋል። ይህን በ1ቆሮ. 14 እናገኛለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ትንቢትን መናገር በልሳኖች ከመናገር ይልቅ ጉባኤውን ያንጻልና የቆሮንቶስ ምዕመናን ከልሳኖች ይልቅ ትንቢትን እንዲፈልጉና እንዲናገሩ ያበረታታቸዋል።

ትንቢት ከልሳኖች እንደሚሻልና ይበልጥም ጠቀሜታ እንዳለው ሐዋርያው ይህን የተናገረበትን፥ በተለይ በ1ቆሮ. 14፥15 እና 19 እናገኛለን።

በልሳኖች መናገርን በተመለከተ በዚህ ምዕራፍ (1ቆሮ. 14) ያሰፈራቸው መሠረታዊ መመሪያዎች አሉ። እነዚህም ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት የልሳን የጸጋ ስጦታን ስንመለከት ያየናቸው ናቸው፤

ሀ. በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ (14፥2) (ትንቢት የሚናገር ግን ለሰው ይናገራል።) ለእግዚአብሔር የሚናገር በግሉ ይናገር ዘንድ ተጽፎአል።

ለ. ልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ (14፥4) (ትንቢት የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል)

ሐ. በልሳን የተነገረ ነገር ካልተተረጎመ ከንቱ ነው፤ (14፥5-12)

መ. በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ፤ (14፥13)

ሠ. ለሌሎች ትምህርት ይሆን ዘንድ በልሳን 10 ሺህ ቃላት ከመናገር ይልቅ የሚታወቁ አምስት ቃላት መናገር ይበልጣል፤ (14፥19)

ረ. በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው፤ (14፥22) ትንቢት ግን ለሚያምኑ ነው። (በልሳኖች መናገር ለማያምኑ እንዴት ምልክት እንደሚሆን በተለይ በሐዋ. 2 ከተጻፈው እንማራለን ወይም መረዳት እንችላለን።)

ሰ. ሁሉ በልሳኖች በሚናገሩበት ያልተማሩ ወይም ያላመኑ ቢገቡ ነገሩ እብደት ሊመስል ይችላል፤ (14፥23) (ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን ውጤቱ መወቀስና ስግደት ነው።)

ሸ. በልሳን የሚናገሩ ከኖሩ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም፤ (14፥27) በጉባኤ ሁሉ በልሳን እንዲናገሩ ማበረታታት የቃሉ ትምህርት አይደለም።

ቀ. የሚተረጉም ከሌለ ተናጋሪው በማኅበር መካከል ዝም ብሎ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር፤ (14፥28)

በ. በልሳኖች መናገር መከልከል የለበትም፤ (14፥39)

ከላይ የተዘረዘሩት እስከተፈጸሙ ድረስ በልሳን መናገር መከልከል የለበትም። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በልሳኖች መናገርን ሙሉ በሙሉና በጥብቅ ይከለክላሉ። ይህን መሳይ ውሳኔያቸው ትክክል ካለመሆኑም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚደግፋቸው በቂ ድጋፍ ማቅረብ አይችሉም።

ይህን ርዕስ ለማጠቃለል ሁለት ዋና የሚሆኑ አሳቦችን እንውሰድ። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ በተለይም አዲስ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳንም ውስጥ የሐዋርያት ሥራና መልእክቶች ስለ ሁለት ዓይነት ልሳኖች አይናገሩም። ልሳን ልሳን ነው። ልሳን ቋንቋ ነው። የቋንቋ መስፈርትን እንዲያሟላ መጠበቅ ትክክል ነው። ልሳን ምልክትነት ያለው በመለኮታዊ መንገድ ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ የተሰጠ የሚታወቅ ቋንቋ ነው። የሚታወቅ ካልሆነም የሚተረጎም ቋንቋ ነው። የማይተረጎም ከሆነ ግን በጉባኤ የማይናገሩት ቋንቋ ነው። ግን ቋንቋ ነው። ቋንቋ በመሆኑም የቋንቋ ባሕርያትን ሁሉ የተላበሰ ነው። በተወሰኑ ከአስር በማይበልጡ ድምጾች የተቀመረ ነገርን ቋንቋ ብሎ መቀበል ቢያስቸግር፥ 'ለምን አስቸገረ?' ብሎ መጠየቅ ማስገረም የለበትም። ይሁን እንጂ የመግባቢያና የመነጋገሪያ ቋንቋ ግን አይደለም። አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆች ፈጽሞ የተለዩ መሆናቸውን ለማሳየት በልሳኖች መግባባት የሚችሉ እስኪመስሉ እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩበትም ሁኔታ አልፎ አልፎ ታይቶአል፤ ይታያልም። ልሳን የመነጋገሪያና የመግባቢያ ቋንቋ አይደለም። የዋሆቹም ክርስቲያኖች እነዚህን ልሳን ተናጋሪ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል በመመርመር ፈንታ እንደ ልዩ የክርስቲያን ዝርያዎች በመመልከት ያደንቋቸዋል።

አንዳንዶች የማይተረጎመው የመላእክት ልሳን ሊሆን ይችላል ይላሉ። ስለ መላእክት ልሳን ጉዳይ ሦስት ነጥቦችን ልበል፤

1. መላእክት ቋንቋ ያላቸው ይመስለኛል። መላእክትኛ የሚባል ቋንቋ ስለመኖሩ የተጻፈ ነገር ባይኖርም፥ መላእክት አንዱ ለአንዱ እንደሚናገሩ ተጽፎአል። ግን በ1ቆሮ. 13 የተጻፈው፥ የፍቅርን በላጭነት በመግለጥ በንጽጽር እና በግነት መልክ የተጻፈ ምንባብ ነው።

Ἐὰν ταῖς γλώσσαις τῶν ἀνθρώπων λαλῶ καὶ τῶν ἀγγέλων በሰዎች ልሳን ብናገር፥ በመላእክትም እንኳ ጭምር . . . ሲል፥ አይደለም በሰዎች፥ በመላእክትም ልሳን ተናግሬ ማለቱ ነው፤ 'ይህን ተናግሬ ፍቅር ግን ቢጎድለኝ' እያለ ነው። ንጽጽራዊ ቋንቋን ወይም ኢጋኖን በመጠቀም መግለጡ ነው።

2. ይህ ቢሆንና ለአንድ ልሳን ተናጋሪ የመላእክት ቋንቋ ተሰጠው ብንል እንኳ ከሌላ የማናውቀው የሰው ቋንቋ የተለየ መሆኑን በምንም መስፈርት አናውቅም። መላእክት ሲነጋገሩ በመካከላቸው ተገኝተን ካልሰማንና ያንን ቋንቋ ካላወቅን በቀር ያ ቋንቋ የመላእክት ቋንቋ መሆኑን አናውቅም። የምናውቀው ከቋንቋዎች ሁሉ አንዱ ብቻ መሆኑን ነው። ከዚህ በፊት ከቶም ሰምተን የማናውቀውን ቋንቋ፥ 'ይህ ጉራግኛ ወይም ሽናሽኛ ነው።' ማለት እንደማንችል። ይህ መላእክትኛ ነው ማለትም አንችልም።

3. ይህ ቢሆንና አንድ ሰው የመላእክት ልሳን ተናገረ ብንልና ልሳኑ የመላእክት መሆኑን ብናውቅ እንኳ (አናውቅም እንጂ) እኛ ሰዎች ስለሆንን በትግርኛ ወይ ሶማልኛ ወይ

ሌላ የምናውቀው ልሳን ካልተነገረን፥ መላእክትኛን አናውቅምና፥ የማይታወቅ ልሳንም ነውና፥ ልሳኑ ካልተተረጐመ ጉባኤው ይታነጻል? አይታነጽም። ስለዚህ አሁንም የሰውኛም ሆነ የመላእክትኛ ልሳን ቢነገር ከተተረጐመ ደግሞ ምንም አያጣላንም። የማይታወቅ ከሆነና የማይተረጐም ከሆነ ደግሞ ተናጋሪው ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር። ይህ የቃሉ ትምህርት ነው።

ልሳን እንግዲህ ካልተተረጎመና ለራስ ብቻ ከተነገረ አማኙን ሊያንጽ ቢችልም ቅሉ እንደ ሌሎቹ ስጦታዎች ሁሉ፥ ለክርስቶስ አካል ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ የተሰጠ ስጦታ ነው። የሚናገረውም አማኝ በጉባኤ ካልተተረጎመ እንዳይናገር፥ እንዲሁም መተርጎም እንዲችል እንዲጸልይ የተነገረው ለዚህ ዓላማ ነው።

የመጨረሻው ነጥብ የስጦታውን ባሕርይ መመልከት ማስፈለጉ ነው። ይህን ስጦታ ስናስብ እነዚህን ጥያቄዎች እንጠይቅ፤

- የስጦታው ምንጭ ማነው? ወይም ምንድር ነው?
- የስጦታው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ትክክለኛ ነው?
- ጉባኤውን የሚያንጽ ነው? ተተርጉሞ ተጨምቆ ማኅበሩን የሚያንጽ ነገር ይወጣዋል?
- በስነ ሥርዓትና በአግባብ ነው የሚነገረው? ወይስ በግብታዊነት በሥርዓት አልባነትና ከቁጥጥር ውጪ በመሆን?
- እግዚአብሔርስ በነገሩ ይከብራል?
- የተናጋሪውስ ሕይወት ሲታይ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚታይበት ነው?

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ጴንጤቆስጣዊ ነገረ ልሳን

ቀጥሎ ያለው ቀደም ሲል ከጻፍኩት ጴንጤ አይደለሁም እና የልሳን ጉዳይ በኋላ በተከታታይ የጻፍኩት ምላሽ ነው። በአሥር ተከታታይ አጫጭር ጽሑፎች ያካፈልኩት ሲሆን እዚህ በጥቂት ርእሶች ለያይቼ አቀርበዋለሁ።

## ልሳኖች እና ጴንጤቆስጣዊነት

ይህንን ጉዳይ (99.9ን ሳይሆን ዋናውን የጴንጤቆስጣዊነት ጉዳይ) ከዚህ በፊት በሰፊው ከ30 ያህል ዓመታት *በፊት በመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች* መጽሐፌ የጻፍኩት ጉዳይ ነው። በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ የሚጠየቅ ሁሉን አቀፍ የሆነና የተለመደ አንድ ጥያቄ አለ። ያም፥ 'በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃል? መቼ?' አንዳንዶቹ 'ተሞልተሃል?' የሚለውን፥ 'ተጠምቀሃል?' ይሉታል። ይዘቱ ግን ያው ነው። የመሞላት ወይም የመጠመቅ ምልክቱ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ ያም፥ በልሳን መናገር።

ልሳን የጴንጤቆስጣዊነት ዋና እና ብቸኛ መታወቂያ ነው። ልሳን የጴንጤቆስጣውያን የቀበሌ መታወቂያ ነው፤ የመንጃ ፈቃድና የክልል መታወቂያ ነው፤ ብሔራዊና ዲጂታል መታወቂያ ነው፤ ፓስፖርት ነው። ልሳን ከሌለ፥ ጴንጤቆስጣዊነት መታወቂያ አሳይቶ ኬላ መሻገር አይችልም። ልሳንን መንካት መታወቂያን መንጠቅ ነው። መታወቂያ ብቻ ሳይሆን በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና እና በአንድ ሰው ውስጥ የመገኘቱና የመኖሩ ብቸኛ ምስክር ተደርጎ ይወሰዳል። የሰሞኑ ትኩሳት ያንን ያሳያል። ልሳንን መንካት መታወቂያን መንጠቅ ስለሆነ፥ ልሳን በጥንቃቄ የሚጠበቅ ሰነድ ነው። መታወቂያው ፎርጅድ ከሆነ ምን እንደሚከተል ይታወቃል።

ልሳን የጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ልብና ሳንባ ነው። ያለነዚህ ሁለት ነገሮች የደም ዝውውርና መተንፈስ አይችልም። ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ የተጀመረው እኤአ በ1901 የዓመቱ የመጀመሪያ ቀን በካንዛስ ግዛት በቶፒካ ከተማ በቤቴል መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ነው። ከጥቂት ወራት በፊት በከተማዋ ሳልፍ ቦታውን ለመጎብኘት ፈልጌ ነበር ግን የለም። ኮሌጁ በዚያው ዓመት ከጥቂት ወራት በኋላ ነበር የተዘጋውና፥ እንኳን አሁን ያኔም አልነበረም። እዚያ ምን ተከሰተ? ይህንን ዘመንና ጴንጤቆስጣዊውን እንቅስቃሴ ቀደም ሲል በጠቀስኩት መንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፌ ምዕራፍ 3 ውስጥ በሰፊው ጽፌበታለሁ።

## ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ

ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ የተጀመረው እኤአ በ1901 የዓመቱ የመጀመሪያ ቀን በካንዛስ ግዛት በቶፒካ ከተማ በቤቴል መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ነው። ኮሌጁን የመሠረተው ቻርልስ ፎክስ ፓርሃም የተባለ ሰው ነው። ፓርሃም ከዚህ ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ በ1898 ቤቴል የፈውስ ቤት የሚባል ከፍቶ የፈውስ ጸሎት ሥርዓት ያደርግ ነበር። ከዚያ በፊት እርሱና አንድ ልጁ በጠና ታምመው ድነው ነበርና ያንን መዳን መለኮታዊ ፈውስ አድርጎ በመውሰድ፥ ሰዎች መድኃኒት መውሰድ ሳይኖርባቸው በጸሎት ብቻ መፈወስ አለባቸው ብሎ በማመን የጀመረው የፈውስ ቤት ነበረ። እንደ አገራችን የሐሰተኞቹ ገስት ሀውስ ዓይነት ነገር ሆኖ ልዩነቱ የነዚህ በዋናነት እና በብቸኝነት የገንዘብ መሰብሰቢያ መሆኑ ነው።

በ1900 ይህንን የፈውስ ቤት ለጥቂት ሰዎች ትቶ የወራት ዕረፍት ወስዶ በጊዜው የታወቁትን የቅድስና እንቅስቃሴ አብያተ ክርስቲያናትን እየዞረ ይጎበኝና ያጠናቸው ጀመር። በተለይ ፍራንክ ሳንድፈርድ የተባለ ሰውን አገልግሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱን ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ሞዴሉን ወይም አደራረጋቸውን ሲያጠና ቆየ። ስለ ልሳን የሰማውም እዚያ ሳለ ነው።

ወደ ከተማው ሲመለስ የፈውስ ቤቱን በአደራ የሰጣቸው ሰዎች ወስደውት የራሳቸው አድርገውት ነበር። ከነሱ ጋር ላለመጨቃጨቅ ያንን ለነሱ ትቶ ቤቴል የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የስነ መለኮት ኮሌጅ ብሎ ከፈተ። ጥቂት አሥር ተማሪዎች ተቀብሎ ማስተማርም ጀመረ። በኮሌጁ የትምህርት መጽሐፍ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሲሆን አስተማሪውም መንፈስ ቅዱስ በፓርሃም አንደበት በመሆን ነበር።

ዓመቱ (1900) ሊያልቅ ሲል ትምህርት ቤቱ ለገና በዓል ስለሚዘጋ ለተማሪዎቹ የቤት ሥራ ይሰጣቸዋል። ያም የቤት ሥራ፥ 'በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ሕልውና አብሯት የመሆኑ ምልክት ምን ነበር?' የሚል ነው። ተማሪዎቹ ያንን ሲያጠኑም ሲወያዩም ቆይተው ዓመቱ ሲያልቅ በዓመቱ መጨረሻው ቀን የመዝጊያ አምልኮ አደረጉ። በቀጣዩ አዲስ ዓመትም ጃንዋሪ 1 ቀን 1901 ሌላ አምልኮ ኖራቸው። በዚያ የጃንዋሪ 1 ቀን 1901 አምልኮ ጊዜ ከተማሪዎቹ አንዷ አግነስ ኦዝመን የተባለች ተማሪ በልሳን ተናገረች። ለቤት ሥራቸው ሲያጠኑት እንደቆዩት ልክ በሐዋ. 2 እንደተጻፈው እነሱ ባያውቁትም ያንን ንግግር የሚታወቅ ቋንቋ ነው ብለው ተቀበሉት። ይህ ነገርም በአግነስ አልቆመም። ነገሩ እየተበረታታ ሌሎችም ተናገሩት። ኋላማ አግነስ በልሳን መናገር ብቻ ሳይሆን በልሳን መጻፍም ችላለች ልሳኑን ጻፈች ከተባለ።

ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ ስር ሰደደና 'የልሳኖች እንቅስቃሴ' The Tongues Movement' በተባለባቸው በቀጣዮቹ ዓመታት ያ የተናገሩት ቋንቋ የቻይና ቋንቋ ነው ተብሎ፥ ልሳነኞቹ ወደ ቻይና ሚስዮናውያን ተደርገውም ተልከው ነበር። ውጤቱ ምን ነበር? ቅሌት! ሄደው አፍረው ነበር የተመለሱት። በአገራችንም በልሳን ልክ እንደሚግባቡ እርስ በርስ የሚነጋገሩ ወፈፌዎች ኖረው ያውቃሉ። ሁለቱ እንዲያውም ካፌ ገብተው አንዱ አስተናጋጇን ግራ እስኪያጋባ የሚጠጣውን በልሳን አዝዞ ነበር። ደግነቱ አብሮት የነበረው ጓደኛው ተረጎመላት።

የቻርልስ ፓርሃም አካሄድና አሠራር ያላማራቸው የቀድሞ ተማሪዎቹ፥ 'አስመሳይ እና ውሸታም' ብለውት ተለዩት። የከተማዋ ጋዜጦችም ኮሌጁን፥ 'የባቢሎን ግንብ' ብለው ጠሩት። የቋንቋ ድብልቅልቁን ነው ከባቢሎን ጋር ያመሳሰሉት። ፓርሃም ድጋፍ ሲያጣ ኮሌጁን በዚያው ዓመት ከጥቂት ወራት በኋላ ዘግቶ ሌላ ከተማ ሄዶ አገልግሎት ጀመረ። ጥቂት ከበርቴ ደጋፊዎችንም አገኘ። ወጣት አገልጋዮችን በጊዜው የታወቀውን የቅድስና ትምህርት ሳይሆን 'ሐዋርያዊ መልእክት' የሚባል አዲስ ትምህርት እንዲሰብኩ ወደ ሌሎች ከተሞች ይልክ ጀመር። ወጣቶቹ ዘንጠውና ሽቅርቅር ብለው የሚለብሱ መሆናቸው ሆን ብሎ ያደረገው አዲስ ባህል ነው።

የፓርሃም አገልግሎት ሰፍቶ ከካንዛስ በመውጣት ወደ ኦክላሆማና ቴክሳስ ደረሰ። በቴክሳስ ሳለ ብዙ ጥቁሮች ወደ አገልግሎቱ ተሳቡ። ሆኖም ጥቁሮች ከነጮች እኩል ተቀምጠው የሚያመልኩበት ጊዜ አልነበረም ጊዜው። እዚያ ነበር ዊልያም ጄ ሲሞር ወደ ፓርሃም ትምህርት የተሳበው። ኋላ ከፓርሃም ቀጥሎ የዘመነኛው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ መታወቂያ የሆነውም ይህ ሰው ነበር።

## ከካንዛስ ቴክሳስ ከዚያ አዙሳ።

ቶፒካ ብዙም ሳይሄድ ቀዝቅዞ ከሰመ። ፓርሃም ከካንዛስ ወደ ቴክሳስ ሄዶ በቴክሳስ ኦርቻርድ በሚባል ከተማ Apostolic Faith Movement የሚለውን አገልግሎቱን በ1905 ጀምሮ በዚያው ዓመት ወሰ ሂዩስተን አዞረው። Apostolic Faith Bible School የሚባልም ትምህርት ቤት ከፈተ።

በትምህርት ቤቱ የምግብ ቤት የምትሠራ በመንፈስ ተጠማቂ በልሳን ተናጋሪ ጥቁር አሜሪካዊት ለሎስ አንጀለስ አካባቢ ሸከም እንዳላት ሲያውቅ ከገንዘብ ድጋፍ ጋር እዚያ ሄዳ አገልግሎቱን እንድትጀምር ከገንዘብ ድጋፍ ጋር ላካት። ስምዋ Lucy Farrow ይባላል።

ዊልያም ሲሞር ቀድሞም የቅድስና ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ የነበረ ሰው ቢሆንም፥ በፓርሃም ትምህርት ተስቦ እንደነበር ቀደም ሲል አይተናል። ስለዚህም የፓርሃም

ትምህርት ቤት ገብቶ መማማር ጀመረ። ይማር ወይም ያዳምጥ የነበረው ግን ጥቁር ስለሆነ ከነጮች ጋር መቀመጥ ስለማይችል ኮሪደር ላይ ተቀምጦ ነበር። ሲሞር በጣም የተመሰጠባቸው ትምህርቶች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በልሳን መናገር፡ እና የሐዋርያዊ ክርስትና ዳግም ለቤተ ክርስቲያን መመለስ የሚሉት ነበሩ። ከጥቂት ወራት በኋላ ፓርሃም ሲሞርንም ቀድሞ ሉሲ ወደ ሄደችበት ወደ ሎስ አንጀለስ አብረው እንዲያገለግሉ ከገንዘብ ድጋፍ ጋር ላከው። ሉሲ የጀመረችውን ሲሞር አጠናክሮ አሰፋው።

ቀድሞ የአፍሪቃውያን ሜተዲስት ኤጲስቆጶሳዊ ቤተ ክርስቲያን የነበረ ኋላ አገልግሎቱን ትቶ መጋዘን ተደርጎ የነበረ በ312 አዙሳ ጎዳና የሚገኝ ቤት ተከራይተው በ1906 በፓርሃም አገልግሎት ስም Apostolic Faith Mission ተብሎ ተመዘገበ። ይህ ኋላ በጎዳናው ስም የታወቀው የአዙሳው ጎዳና መነቃቃት (The Azusa Street Revival) የተባለው እንቅስቃሴ ነው። የአዙሳ ጎዳናው ንቅናቄ 'የባቢሎን ግንብ' ከተባለው ከቶፒካው የባሰው የልሳኖች፥ የጩኸትና ሁከት ስሜታዊ ልምምድም የበዛበት ነበረ። ራሱ ሲሞርም ሲጀመር በልሳን ባይናገርም ኋላ በልሳን ተናጋሪ ሰው ሆነ። ጥቂት ያልሆኑ ነጮችም ተካፋዮች ሆኑ። ጥቁሮች የሚያገለግሉበት ጉባኤ ታዳሚዎች ስለሆኑ ጥቁር በዚህ ነጭ በወዲያ ብለው መለየት አይችሉምና አብረው ተቀምጠው ያመልኩ ነበር።

በ1906 ፓርሃም ይህንን አገልግሎት ለመጎብኘትና ለማገልገል ወደ ሎስ አንጀለስ በመጣ ጊዜ ሦስት ነገሮች በጣም አስቆጡት። አንዱ፥ ነጮችና ጥቁሮች አብረው ማምለካቸው ነበር። ጊዜው የቀለም ልዩነት በጉልበቱ የነበረበት ጊዜ ነው። ሁለተኛው፥ ያስቆጣውና ነገሩን፥ 'እብደት' ያለው በጉባኤው የሚታየው ድብልቅልቅ የልሳን፥ የጩኸት፥ እና ሌሎች ስሜታውያን ልምምዶች መብዛት ናቸው። ሦስተኛው፥ ሲሞር ከቴክሳስ የላከው ፓርሃም ስለሆነና የአዙሳው አገልግሎት የተመዘገበውም የፓርሃም አገልግሎት በሆነው Apostolic Faith Mission ስለሆነ ሥልጣንና ኃላፊነቱ የኔ ነው ሲል፥ ሲሞር ደግሞ ፈጽሞ አልፈቀደለትም። በነዚህ ምክንያቶች በግልጽ ተለያዩ።

የቶፒካው ንቅናቄ፥ 'የባቢሎን ግንብ' ከተባለ፥ የአዙሳ ጎዳናውን ንቅናቄ ራሱ ፓርሃም፥ 'እብደት' ብሎ ከጠራው፥ ምን እንደሚስል መገመት ይቻላል። ፓርሃምና ሲሞር በዚህ ጉዳይ መግባባት አልቻሉምና ተለያዩ። ሲሞር የአዙሳውን ጉባኤ ቀጠለ። ትልቅ ትኩረት የሳበውን ትምህርቱንና ልምምዱን የተቀበሉ በመጡ በሌሎች ቦታዎች አሰራጩት።

የቶፒካው ንቅናቄ ከ3 ወራት በኋላ እንደከሰመው፥ የአዙሳው ጎዳና ንቅናቄ ከ3 ዓመታት በኋላ እየቀዘቀዘ ሄደ። ጉባኤውም ተመናመነ። አንዳንድ መሪዎች ወጥተው

የራሳቸውን ማኅበሮች ጀመሩ። አንዳንዶቹ ጭራሽ በሥላሴም የማያምኑ አሐዳዊ ጴንጤቆስጤዎች ወይም 'ኢየሱስ ብቻዎች' ሆኑ። ሲሞር በ1922 በ52 ዓመቱ ሲሞት በአብዛኛው የተረሳ ሰው ነበረ።

የፓርሃም ፍጻሜም እንደ አጀማመሩ አልነበረም። ከሎስ አንጀለስ እንደተመለሰ በ1906 የተከሰሰበት ወሲባዊ (አንዳንዶች ግብረ ሰዶማዊም ይሉታል።) ክስ ክፉኛ ስሙንና አገልግሎቱን አደበዘዘው፤ እንዲያውም፥ ጎዳው። በ1929 በ55 ዓመቱ ሲሞት ቀድሞውኑ ደብዛዛ የሆነ ሰው ነበረ።

የ1901ዱ እና የ1906ቱ ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴና ሁለቱ አንቀሳቃሾች እነዚህ ሲሆኑ፥ ሁለቱም በነበሩበት ዘመን ደብዝዘው ቢከስሙም ታሪካቸው የጎላው ከዕልፈታቸው በኋላ ከዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ጋር ተቋጥሮ ነው። ፓርሃም የጴንጤቆስጣዊነት ስነ መለኮት መሠረት ጣይ እና ለኳሽ፥ ሲሞር ደግሞ አቀጣጣይና አራማጅ በመሆን ነው።

ሰዎቹ ቢደበዝዙና ቢያልፉም፥ ኋላ በጴንጤቆስጣዊ ትርክት ድርሳናቸው የተጻፈ ሰዎች ናቸው። ከሁሉም በላይ በጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ራሱ ጀማሪውና መሠረት ጣዩ ፓርሃም፥ 'እብደት' ያለው ልሳን ዛሬም አነጋጋሪያችን ርእስ ነው።

## ልሳን የዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊነት እንብርት

ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ በካንዛስ ተወልዶ፥ በቴክሳስ አድርጎ ወደ ሎስ አንጀለስ አዙሳ ጎዳና ደርሶ አይተናል። በሁለቱም ቦታዎች፥ በአንደኛው 3 ወራት ብቻ፥ በሁለተኛው 3 ዓመታት ብቻ ቆይቶ መክሰሙንም አይተናል። የዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ ስነ መለኮታዊ መሥራች ቻርልስ ፓርሃም እና ልምምዱን አቀጣጣዩ ዊልያም ሲሞርም የደበዘዙና የተዘነጉ ሆነው በ50ዎቹ ዕድሜያቸው ምድራዊ ኑሮአቸው ማክተሙንም ተመልክተናል። እነዚህ ሁለት ሰዎች ከብዙ ዓመታት በኋላ በጴንጤቆስጣዊ ትርክት ድርሳናቸው የተጻፈ ሰዎች ናቸው። ከሁሉም በላይ በጴንጤቆስጣዊው የልሳን እንቅስቃሴ ራሱ ጀማሪውና መሠረት ጣዩ ፓርሃም እብደት ያለው፥ ዛሬም አነጋጋሪያችን ርእስ ነው።

ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ ግን 10 ዓመትም ሳይቆይ በሁለቱም ቦታዎች ቢከስምም ልምምዱ፥ በተለይም ልሳን ቀጠለ። በ1910ራዎቹና 20ዎቹ የልሳን ንቅናቄ እየተባለም ይጠራ ጀመር። የትኞቹም ልምምዳዊ እንቅስቃሴዎች ቅርጻቸው ይቀያየራል እንጂ አይጠፉም። ልምምዶች ተሰልቺ ስለሚሆኑ በሌላ አዲስ እየተተኩ ይቀጥላሉ። ባለፉት ብዙ አሥሮች የክርስትና ዕድሜዬ ውስጥ ብዙ ልሳኖች የተባሉ ድምጾችን

ሰምቻለሁ። አንድም የታወቀ ቋንቋ ግን ሰምቼ አላውቅም። 'አንተ ባታውቅ የለም ማለት ነው?' ልባል እችላለሁ። ያንን አላልኩም። ብዙ መቶዎች የማውቃቸውና ስለ ልሳናቸው የጠየቅኋቸው ሰዎች አሉ። አንዳንዶቹን በአካል በቃል፥ ሌሎቹን በስልክ፥ ሌሎቹን በጽሑፍ ነው የጠየቅኋቸው።

ከምጠይቃቸው ጥያቄዎች መካከል፥ ይህንን ስጦታ መቼና እንዴት ተቀበልክ? ተቀበልክ ወይስ ተለማመድክ? ከዚያ በፊት ይህንን ነገር ለስንት ወራት ወይም ዓመታት ስትሰማ ኖረሃል? ይህንን ነገር እንድታገኝ ሰዎች ነግረውሃል? ገፋፍተውሃል? አደፋፍረውሃል? አለማምደውሃል? እጃቸውን ጭነው እያንዘፈዘፉህ በፍጥነት እንድትናገር፥ ድምጽህ እንዲንቀጠቀጥና እንዲነዝር አድርገውሃል? አውጣው! በለው! አፍጥነው! ወዘተ፥ ብለውሃል? ሌሎችም ጥያቄዎች አሉ። ብዙዎቹ መልሳቸው አዎንታዊ ነው። ይህንን ከመለሱልኝ በኋላ፥ 'ታዲያ ይህ ነገር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ይመስልሃል? ደግሞስ እውነተኛ ቋንቋ ይመስልሃል?' እላቸዋለሁ። የብዙዎቹ መልስ ከልባቸው የሆነ መልስ ነው። ያንን ተጠይቀውም አያውቁም።

ብዙ መቶዎች ብያለሁ። አንድ መቶ ብቻ ብጠይቅ ወይም ብፈትሽና ከዚያ ውስጥ 1 ብቻ ቋንቋ ባገኝ፥ 99% ቋንቋ አይደለም ማለት ነው። እኔ ያልኩት ደግሞ 99.9% ነው። ይህንን ለማለት አንድ ሺህ መሙላትና ከአንድ ሺህ ውስጥ 1 እውነተኛ ቋንቋ መስማት አለብኝ። መጠየቄ ቀጥሏል። አሁንም እንኳ እጠይቃለሁ። ከትናንት ወዲያ አንድ ጓደኛዬን በዝርዝር ጠይቄዋለሁ። ከ1 ሺህ አንድ እውነተኛ ቋንቋ አገኝ ይሆናል። ምናልባት ከ10 ሺህ ወይም መቶ ሺህ አንድ ይገኝ ይሆናል። እስካሁን ግን አላገኘሁም። አንድም።

ምናልባት ሌሎች 0.01% ወይም 1% ወይም 10% ወይም 100% አግኝተው ይሆናል። ታዲያ እነርሱ ምስክርነታቸውንና ማስረጃቸውን ማቅረብ ይችላሉ። አንድም ማቅረብ ካልቻሉ ደግሞ፥ 'አንተ የመንፈስ ቅዱስ ተቃዋሚና ተሳዳቢ ነህ!' በማለት ሊቀጥሉ ይችላሉ። ያ ታዲያ ድምጻቸውን ቋንቋ አያደርገውም።

ቋንቋ ስንሰማ እናውቃለን። ቋንቋውን ባናውቅም እንኳ፥ ልክ ሙዚቃ ስንሰማ ሙዚቃ እንደሆነ እንደምናውቀው ቋንቋ ስንሰማ ቋንቋ መሆኑን እናውቃለን። ባለ አንድ ድምጽ መሣሪያ ሙዚቃ አያወጣም። በጡሩምባ ሙዚቃ መጫወት አይቻልም። አንድ ድምጽ ብቻ ነው ያለው። የአዲሱ ጴንጤቆስጣዊ ልሳንም ልክ እንደ ጡሩምባ ነው። ድምጽ ነው፤ ቋንቋ አይደለም።

በ1901 ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ ሲጀመር ቻርልስ ፓርሃም ለተማሪዎቹ የሰጣቸው የቤት ሥራ ጥያቄ ትዝ ይላችኋል? 'በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ምልክት ምን ነበር?' የሚል ነበር። መልሱ ልሳን ሆነ። መልሱ ስብከት ቢሆን ኖሮ ሰባኪዎች ይበዙ ነበር። መልሱ ፈውስ ቢሆን ኖሮ በልሳን ፈንታ ፈውስ ይሆን

ነበር። ግን ልሳን ሆነና ልሳን እስከዛሬ የጴንጤቆስጣዊነት መታወቂያና ፓስፖርት ሆኖ ቀጠለ። ይህ ነገር ደግሞ ለመፈብረክና ለመለማመድ በጣም ቀላሉ ነው። ፈውስ ቢሆን ኖሮ ሸውዶ ማለፍ አይቻልም። ይህ ግን ተመኝተውት፥ ብዙ ሰምተውት፥ ተለማምደውት፥ ተገፋፍተውትና ተጎትጉተውት ይነገራል።

ውጤቱ ምንድር ነው? ቋንቋ ካልሆነና ቋንቋ ሆኖ ካልተተረጎመ ለጉባኤ ውጤቱ ምንድር ነው? ምንም! በጣም የተሻለው መልስ፥ 'ራስን ማነጽ' ነው። ማንን ማነጽ? ራስን። ግን ይህ ራስን ማነጽም አይደለም። ምክንያቱም ራሳቸውን ቢያንጹ በግልና በጓዳና በእልፍኝ ነው የሚናገሩታ! በጉባኤ አይናገሩትማ! ራስን ማነጽ ቢሆን በጉባኤ ማን ይሰማው ነበር? ያውም ማይክሮፎን ላይ ተደርጎ! ያውም እያስተማሩትና እያለማመዱት! ይህማ ራስን ማነጽ ሳይሆን ጉባኤን ማወክ ነው።

በጉባኤ ከተነገረ ያ ቋንቋ በእርግጥ ቋንቋ ነው። ለዚህ ነው ለማያምኑት ምልክት ነው የተባለው። 'እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም።' 1ቆሮ. 14፥22። የግል መታነጫ ከሆነም በጉባኤና ለጉባኤ ስለማይነገር አያጣላንም። አንሰማውማ! 'የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር።' 1ቆሮ. 14፥28። ባለ ልሳን ጴንጤቆስጣውያን ይህንን ክፍል አያነብቡትም ወይስ በልሳን ነው የሚያነብቡት?

## በስሕተትነት የቀጠለ ታሪካዊ ስሕተት

ዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ የተጀመረው ስነ መለኮታዊና ልምምዳዊ ስሕተት ላይ ተመስርቶ መሆኑን ከአጀማመሩ ታሪክ ተመልክተናል። ያ ታሪካዊ ስህተት በስህተት ታሪክነት ቀጥሏል። የቀጠለበት ታሪክ በመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፌ ምዕራፍ ሶስት መመልከት ይቻላል። ይህ እስካሁን የጻፍኩትም ሰፋ አደረኩት እንጂ አንኳሩ ከዚያ የተወሰደ ነው።

ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ ከቶፒካና ከአዙሳው ቀጥሎ ባሉት ቀጣይ ዓመታት ከቃሉ የተፋቱ ምልክታዊና ትንግርታዊ ልምምዶችን እያዘለ ቀጠለ። የልሳናት ንቅናቄ ይባል ነበር። የድንቅና ምልክቶች ንቅናቄም ተብሏል፤ እባብ ያዢዎችና መርዝ ጠጪዎችም ተነሥተው ነበር (እየሞቱም እየተነደፉም)። እንቅስቃሴው ደከም ሲል፥ 'ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ' ተብሎ እንደ አዲስ ንቅናቄ ሆኖ ተጀመረ። የኋለኛው ዝናብ፥ ሦስተኛው ሞገድ፥ የሐዋርያትና ነቢያት አምስቱ ቢሮዎች፥ የብልጽግናና የጤንነት ወንጌል፥ ቃለ እምነት፥ ወዘተ፥ እየተባለ ቀጠለ። በነዚህ ሁሉ ዋናው አጫዋች ልሳን ነው።

በሁሉም ንዑሳን ንቅናቄዎች ዘንድ ልሳን እንደ መንፈስ ቅዱስ መገኘት ምልክት ተደርጎ ነው የሚታየው። ልብን እንበል፤ ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ ሲጀመር ፓርሃም የጠየቀው ጥያቄ፥ 'በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ምልክት ምን ነበር?' የሚል ነው። ባለፈው ክፍል እንዳልኩት መልሱ ልሳን ሆነና ልሳን መድረኩን ያዘ። በመቶ ዓመታት የጴንጤቆስጣዊነት እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ያ ጥያቄና መልሱ አልተለወጡም። ሌላ ጉዳይም ልብ እንበል፤ የሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሀዋርያት ምንጭ ይህ እንቅስቃሴ ነው።

ከዚህ ተከታታይ ጽሑፍ ግቦች አንዱ ጥበበኛ መልስ ከማግኘት ይልቅ ትክክለኛ ጥያቄ መጠየቅ ነው። መልስ ትክክለኛ ላልሆነ ጥያቄም ይገኛል። ትክክለኛ ያልሆነ ጥያቄ ጠይቆ መልስ ከማግኘት ትክክለኛ ጥያቄ ጠይቆ መልስ ማጣት ይሻላል። ቃሉ ደግሞ የሚያጠግብ መልስ አለው።

የጴንጤቆስጣዊነትን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እና በልሳን መናገር ስናስብ መጠየቅ ያለብን፥ 'እውነት ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ነው? በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች ሁሉ ልሳን ተናግረዋል?' ብለን ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአዲስ ኪዳን 14 ቦታዎች ተጠቅሶ፥ አንድ ቦታ ብቻ ነው በልሳን የተነገረው። ያም ልሳን እውነተኛ ቋንቋ ነው። ይህንን ጉዳይ በመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማሪዎች ምዕራፍ ሁለት እና የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በልሳን መናገር ይገናኛሉ? በሚለው የቪድዮ ትምህርት አካፍያለሁ።

ከቃሉ ጋር የተፋቱ ልምምዶች ባሉበት በዚያ፥ ልምምዶቹን የተመረኮዙ የስህተት ትምህርቶች ይበዛሉ። ሙላትና ልሳንን ቃሉ በትክክል እንደሚያስተምረው ብንማራቸው ኖሮ የልምምድ ሰው-ሠራሽ ልሳኖች ቦታ አይኖራቸውም ነበር። ከጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙት የስህተት ትምህርቶችና ልምምዶች ዋና አጫዋች ልሳን ነው ብያለሁ። ልሳን ከሌለ ጴንጤቆስጣዊነት የለም።

የምንሰማቸው ልሳኖች እውነት ልሳኖች ወይም ቋንቋዎች ናቸው? ወይስ ስሜት-ወለድ ድምጾች (ecstatic utterance የሚባሉት) ናቸው? ይህንን ማወቅስ ይቻላል? በእውነቱ፥ በጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ማመናፈስ የገዘፈ ሚና ቢኖረውም፥ አንዳንድ ነገሮችም ምንም መንፈሳዊ ልባስ ቢላበሱም፥ ምንነታቸውን ለማወቅ የግድ መንፈሳዊ መሆን የለብንም። በአእምሮም እናውቃለን። ሐሰተኞች ሲያጭበረብሩ አጭበርባሪ እንደሆኑ ለማወቅ ክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ መሆን የለብንም። ያልተፈወሰ ሰው አለመፈወሱን ለማወቅ መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ መሆን የለብንም። ዓለማዊ ጋዜጠኞች ሐሰተኞችን የገለጡት እኮ ክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ ሆነው አይደለም። የልሳንንም ምንነቱን ለማወቅ የግድ ማመናፈስ የለብንም።

## የልሳን ሁለት ሳይንሳዊ ፍተሻዎች

ልሳን በሁለት ሳይንሳዊ መስኮች ተፈትሿል። 'መንፈሳዊ ልምምድ እንዴት በሳይንሳዊ መስክ ይፈተሻል?!' ተብሎ ጢስ እና አቧራ መነሣት ይችላል። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሥራ መሪ ይህንን አሳብ ካነበበ በኋ፥ 'ልሳን ላቡራትሪ ገብቷል' ብሎ አንጓጣጭ ጽሑፍም ጽፎአል። ጢስ እና አቧራውን ለመከልከል ባልችልም ለመቀነስ፥ ወደ መስኮቹ ከማለፌ በፊት ስለ ፍተሻው መቻቻል እና አለመቻቻል ሁለት ነገሮች ልናገር።

1ኛ፥ እርግጥ ነው፤ መንፈሳዊ ነገር በሳይንሳዊ ጥናት ሊፈተሽና ሊረጋገጥ አይቻልም። መዳኔንና አለመዳኔን ሳይንስ ማረጋገጥ አይችልም። ሳይንስ ማረጋገጥ የሚችለው ተጨባጭና ተዳሳሽ፥ ታዪ እና ተረዓዪ (የሚታይ ለማለት ነው)፥ ተቀማሽና ተሸታች፥ ተደማጭና ተሰሚ የሆኑትን በስሜት ሕዋሳት የሚፈተሹትን ነገሮች ብቻ ነው። አንደ መታደል ይሁን ወይም አለመታደል አላውቅም፥ ልሳን ደግሞ ከነዚህ ውስጥ ነው። ልሳን ማለት ደግሞ ቋንቋ ማለት ነው። ቋንቋ ሊፈተሽ ይችላል። ቋንቋ አካላዊ ክስተት ነው፤ የአካል ክፍሎችን ያካትታል፤ ስለዚህ ፍተሻን ማስተናገድ ይችላል።

2ኛ፥ እውነተኛ ያልሆነ የተጭበረበረ ነገር ሊታይበት ይችላል። ማናቸውም የተጭበረበረ ነገር ሊፈተሽ ይችላል ብቻ ሳይሆን መፈተ አለበት። ከዚህ በፊት ደጋግሜ ከተጋፈጥኳቸው ጉዳዮች አንድ ምሳሌ ልስጥ። ለምሳሌ፥ አንድ ፈውሰኛ አንድን ሕመምተኛ፥ 'ከዚህ ደዌ ተፈውሰሃል!' ይለዋል። ሕመምተኛው ወይም የዋሁ አማኝ አሜን ይላል። ጠርጣሪ ሰው ቢጠይቅስ? ይህ ፈውስ መረጋገጥ ይችላል? ወይስ ነገሩ መንፈሳዊ ጉዳይ ስለሆነና በሥጋና በሳይንስ መረጋገጥ ስለማይታሰብ አይቻልም? መልሱ ግልጽ ነው። ይቻላል። ሕመሙ መጥፋቱ በዓይን የሚታይ ከነበረ በዓይን ታይቶና በእጅ ተዳስሶም መረጋገጥ ይችላል። የውስጥ ደዌ ከሆነስ? ያኔ ደግሞ ሰውየው መስክሮ ይረጋገጣል። ሰውየው የቃለ እምነት ሰለባ ከሆነና ሳይፈውውስ ተፈውሻለሁ ቢልስ? በሐኪም ተፈትሾ መረጋገጥ ይችላል።

መፍፈተሹና መረጋገጡ ለምን አስፈለገ? ከላይ ባልኳቸው ሁለት ምክንያቶች። አንደኛ፥ ነገሩ አካላዊ በመሆኑ፤ እና ሁለተኛ፥ እውነተኛ ያልሆነ ተጠርጣሪና አጠራጣሪ ወይም እውተኛ ነገር በመኖሩ። አካላዊ ያልሆኑ መንፈሳዊ ነገሮችም እንኳ ይፈተሻሉ። ለምሳሌ፥ ትምህርት ትክክልና ስሕተት መሆኑ በቃሉ ይፈተሻል። ትንቢት መፍፈጸሙና አለመፍፈጸሙ ሊረጋገጥ ይችላል። ለዚህ ሳይንስ አይረዳንም፤ አያስፈልገንምም።

ልሳን በሁለት ሳይንሳዊ መስኮች ተፈትሿል ብያለሁ። እነዚህ ሁለቱ እኔ የማውቃቸው ናቸው እንጂ የፍተሻ መስኮቹ ከዚህም ሊበልጡ ይችላሉ። ምንድር ናቸው? እነዚህ ሁለቱ እኔ የማውቃቸው ናቸው እንጂ የፍተሻ መስኮቹ ከዚህም ሊበልጡ ይችላሉ። ምንድር ናቸው? ሁለቱ መስኮች ስነ ቋንቋዊ (Linguistic) እና የአንጎል ነርቮች ሳይንስ (Neuro-science) ናቸው። ሁለቱንም እንመልከት።

## ልሳንና ስነ ቋንቋ

ስለ ስነ ቋንቋዊው ሳይንሳዊ ፍተሻ ያነበብኩት ከ30 ዓመታት በፊት መንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶችን ስጽፍ ነበር። ያኔ ካነበብኳቸው ሥራዎች መካከል በመጽሐፎቹ የውስጥ ሽፋን ድምጽም የያዙ ሲዲዎችም ተያይዘው ነበሩባቸው። ያኔ ሲዲ ገና መጀመሩ ነበር። እኔ የቋንቋና ስነ ጽሑፍ ተማሪ እንደመሆኔና ጥቂት የLinguistics ኮርሶችም ስለወሰድኩ ጥናቱና መጽሐፎቹ ስበውኛል።

Linguistics ቋንቋ ምን መሆኑን፥ ፍጥረትና አሠራሩን፥ ድርና ማጉን፥ በምንና ምን እንደሚሸመንና እንደሚጠፈር የሚነግረን የትምህርት ዘርፍና ሙያ ነው።

ቀደም ባሉት ክፍሎች በተደጋጋሚ ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው ብያለሁ። አዲስ ኪዳን በተፃፈበት በግሪክ ቋንቋ ልሳን የተባለው ቃል ግሎሳ ነው የሚባለው ትርጉሙም ቋንቋ ማለት ነው። ሌላ ትርጉምም አለው፤ ምላስ ማለት ነው በአፋችን ውስጥ የሚገኘው የአንደበታችን ክፍል ማለት ነው። ሌላም ትርጉም አለው፤ የባህር ልሳን የምድር ልሳን እንደሚባለው የምላስ ቅርጽ ያለው መልክዓ ምድርም ነው። በአጠቃላይ ግን ግሎሳ ማለት ቋንቋ ማለት ሲሆን፥ glossolia ማለትም በልሳን መናገር ማለት ነው። የቋንቋ ትምህርት በመማርበት ጊዜ ከወሰድኳቸው ኮርሶች መካከል አንዱ ልሳነ ግእዝ ይባላል፤ የግዕዝ ቋንቋ ማለት ነው። ልሳን ማለት በአጭርና ግልጽ ቃል ቋንቋ ማለት ነው።

ቀደም ሲል እንዳልኩት የውሸት ፈውስ፥ ጸጋ ያልሆነ የልምድ ፈውስ ሊኖር እንደሚችል እና እንደሚፈተሽ፥ የውሸት ትንቢት ሊኖር እንደሚችል እና እንደሚፈተሽ ሁሉ፥ ውሸታም ልሳን ሊኖር ይችላል ብለን መጠርጠር ለምን አይታሰብም? ለምን ይከለከላል? ይህንን መጠርጠርና ፍተሻ የሚከለክሉ አሉ። የሚከለክሉበት ምክንያትም ቀደም ሲል ይህን ክፍል ስጀምር እንዳልኩት ልሳን የጴንጤቆስጣውያን የቀበሌ መታወቂያና የመንጃ ፈቃድ፥ የክልል መታወቂያና ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ እንዲሁም ፓስፖርት ስለሆነ ነው። ልሳን የጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ልብና ሳምባ ስለሆነ ነው። ልሳን ከሌለ ጴንጤቆስጣዊነት የለም። ስለዚህ ልሳን መነካትና መፈተሽ የለበትም።

ወደ ልሳን ስነ ቋንቋዊ ፍተሻ (linguistical analysis of glossolia) ጴንጤቆስጣዊው glossolia ወይም በልሳን መናገር ሃይማኖታዊ ልምምድ ሆኖ ቋንቋ የሚመስሉ፥ ቃል ያልሆኑ ቅጥልጥል ድምጾች የሚፈጠሩበት፥ ወጥነት ያለው ሰዋስዋዊ ሕግ ወይም መልእክትን እና ይዘትን (ቋንቋዊ መልእክት ማለቴ ነው) ያልጨበጡ ድምፆች ስብስብ ነው ማለት ነው። ቋንቋ፥ የትኛውም ቋንቋ የሚከተለው ሕግ አለው። ልሳን ግን የለውም።

የመጽሐፍ ቅዱሱ ልሳን ቋንቋ ነው። ሰዎች ሳይማሩት ሳይለምዱት ሳያውቁት የሚናገሩት፥ ሌሎች ደግሞ የሚሰሙት የሚረዱት ቋንቋ ነው። ልሳን በመጀመሪያ በተከሰተበት የሆነው ያ ነው።

በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ የሚባሉት ልሳኖች ቅርጽ ስላላቸው ንግግር ይመስላሉ። እነዚህ ልሳኖች የሚሠሩበት ምንጭ ድምጾቹ የሚገኙት ልሳን ተናጋሪው ሰው ከሚናገርበት ከራሱ ቋንቋ ነው። በዚያ ቋንቋ ውስጥ የሌሉ ድምጾችን አይጠቀምም። ለምሳሌ፥ ቻይናዊ ጴንጤ በልሳን ቢናገር፥ የአማርኛ ተናጋሪዎችን እንደ ጩ ወይም ቀ ያሉትን ድምጾች አይጠቀምም ማለት ነው አያውቃቸውም። ወይም የኦሮምኛን ዷ አያውቅምና አይናገርም። እውነተኛ ልሳን ከሆነና ቻይናዊው መንዝ ወይም ነጆ ቢገኝና ጥርት ባለው ዘዬአቸው ቢናገር ያ ልሳን ነው።

ስለዚህ አንድ የልሳን ተናጋሪ የልሳኑ ድምጾች ከገዛ ቋንቋው ውስጥ የወጡ ድምፆች ናቸው። ድምጾቹ ብቻ ሳይሆን አጣጣሉ፥ ዘዬው፥ ጠበቅ ላላ፥ ከፍ ዝቅ ማድረጉ (በስነ ቋንቋ prosody ይባላል) የራሱ ቋንቋ አነጋገር እና ዘዬ ነው። በአማርኛ ተናጋሪ ባለ ልሳኖች ዘንድ የባንቱዎችን ድምጸት አናገኝም።

ከስነ ቋንቋ እየታ አንጻር በልሳን መናገር ወይም glossolia ተናጋሪው ከገዛ ቋንቋው በወሰዳቸው ጥቂት ድምጾች የተሠሩ፥ ቃል የሚመስሉ እና የሚደጋገሙ፥ አንጓ ድምጾቹ (syllables) በጣም ቀላል፥ ብዙዎቹ አንድ ተነባቢና አንድ አናባቢ የያዙት ድምፆች ናቸው። ለምሳሌ፥ ሽ-አ፥ ር-አ፥ ግ-አ፥ ብ-አ፥ ር-አ ወዘተ፥ የያዙ በፍጥነት ሲደጋገሙ (ሻራጋባራ) ቃል የሚመስሉ ድምጾች ናቸው። ድግግሞሽ (repetition) ተመሳሳይ ድምፆችን ጫን ማለት (alliteration) ድምጹን ቅላጼ ወይም ዜማ ማስመሰል (intonation) የመጨረሻ ድምፆችን ማመሳሰል (rhyme) የሚቆራረጡበት ቦታ የተለካ መምሰሉ (staccato)፥ የድምጽ ግነት ወይም (pitch and loudness) ፍጥነትና ርገጥ ማድረግ ወይም (tempo and intensity) እንደ ተናጋሪው የስሜት ሁኔታ ሊለዋወጥ ይችላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ተደማምረው ለሰሚዎች እንደ ንግግር ያለ ቋንቋ ሊመስላቸው ይችላል እንጂ በልምምድ የሚነገሩ ልሳኖች ቋንቋዊ መዋቅርን አይከተሉም። እንደ ስነ ቋንቋዊ ፍተሻው ልሳን እንደ ቋንቋ ወጥ የሆነ ቅርጽ

(morphology) የለውም። ለምሳሌ፥ ነጠላና ብዙ፥ የጊዜ፥ የግስ፥ የባለቤት ወዘተ፥ ቅርጽ የለውም። በተከታታይ የሚተኮሱ ድምጾች ብቻ ናቸው ያሉት። ልሳንን ወደ ዐረፍተ ነገር መልክ አስቀምጦ መከፋፈል ቢሞከር ድምፃዊ ክፍፍል (phonological patterning) ብቻ እንጂ እንደ ቋንቋ ትርጉም ሰጪ ደንብን የተከተለ አከፋፈል ማድረግ የማይሞከር ነው።

ይህ የልሳን ስነ ቋንቋዊ ፍተሻ ወይም ሳይንሳዊ ፍተሻ ነው። ይህንን ጨብጠን የሚናገሩ ሰዎችን ልሳን ብንፈትሽ ምንም የቋንቋ ይዘት የሌላቸው የተደጋገሙ ቃላት መሳይ ድምጾች ሆነው እናገኛቸዋለን። የተበላሹ የፈውስ ቃላት ወይም የፈውስ አዋጆች እንደሚፈተሹት (አካላዊ ናቸዋ!) ወይም የተሳሳቱ ትንቢቶች እንደሚፈተሹት፥ ሰው-ሠራሽ የልምምድ ፈውስ፥ ሰው-ሠራሽ የልምምድ ትንቢት እንደሚፈተሹት፥ ሰው-ሠራሽ እና በልምምድ ተገኘ የተገኘ ልሳንስ በዚያ መልኩ መፈተሽ አይችልም? ይችላል።

እንኳን በቃሉ በመመርኮዝና መናፍስትን በመለየት፥ እንኳን እንደ ባለ አእምሮ በማሰብና በመጠየቅ፥ እንዲህ በስነ ቋንቋ ጠቢባንም ሳይቀር ልሳን ይፈተሻል። ልሳን ይፈተሻል። አንደኛውን የልሳን ሳይንሳዊ ፍተሻ ወይም ምርምር፥ ማለትም፥ ስነ ቋንቋዊ ይዘቱን ፍተሻ ተመለከትን። ወደ ሁለተኛው እንለፍ።

## የNeuro-science ወይም Neuro-theology ፍተሻ

ሁለተኛው የNeuro-science ፍተሻ ወይም ምርምር ነው። አንዳንዶች Neuro-theologyም ይሉታል። ለስነ ቋንቋ ጥናት የልሳን ተናጋሪዎችን ድምጽ መስማት፥ ወይም የተቀረጹ የልሳን ድምጾችን መስማት ብቻውን ለጥናቱ በቂ ግብዓት ነው። ወደ የNeuro-science ወይም Neuro-theology ስንመጣ ግን ይህኛው ጥናት የአንጎል ነርቮች ጥናት ነውና፥ ደግሞም አካላዊ እና ስሜታዊ (motor and sensory) ሕዋሳት መስተጋብር ያለበት ነውና በሕያዋን ሰዎች ላይ መካሄድ አለበት።

ይህ ስለሆነ፥ ጥናቶቹ የተካሄዱት በፈቃደኛ ሰዎች ላይ ነው። ባለፈው ክፍል እንዳየነው ልሳንን እንደ ቋንቋ መመርመር ሳይሆን፥ ይህኛው በዚያ ጊዜ፥ ሰዎቹ በልሳን ሲናገሩ ጸሎት እየተካሄደ ነው ወይ? የሚል ነው ጥናቱ። ቀደም ሲል እንዳልኩት መንፈሳዊ ነገር በሳይንሳዊ መንገድ ሊረጋገጥ አይችልም ወይም ላይረጋገጥ ይችላል። ግን ያ ነገር አካላዊ ክስተት ከሆነ ሊረጋገጥም ይችላል።

ቀደም ሲል የተጠቀምኩትን ምሳሌ ልድገመው። አንድ ፈውሰኛ አንድን ሕመምተኛ፥ 'ከዚህ ደዌ ተፈውሰሃል!' ቢለው፥ የዋሁ አማኝ አሜን ይላል። ጠርጣሪ ሰው ይጠይቃል። ይህ ፈውስ መረጋገጥ ይችላል? አዎን ይችላል። ለምን? አካላዊ ስለሆነ።

ሕመሙ መጥፋቱ በዓይን ታይቶና በእጅ ተዳስሶም መረጋገጥ ይችላል። የውስጥ ደዌ ከሆነ ደግሞ፥ ወይ ሰውየው መስክሮና በሐኪምም ተፈትሾ መረጋገጥ ይችላል። መንፈሳዊ ነገሮች በሳይንስ አይረጋገጡም። ለምሳሌ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ትክክልና ስሕተት መሆኑ ወይም ትንቢት መፍፈጸሙና አለመፍፈጸሙን፥ ወይም አንድ ሰው መዳንና አለመዳኑን ለማረጋገጥ ሳይንስ አይረዳንም፤ አያስፈልገንምም።

ልሳን እንደ ፈውስ አካላዊ ክስተት ነው። ይነገራል፤ ይደመጣል። ሲነገር የሞተር ሕዋሳት፥ ሲደመጥ የስሜት ሕዋሳት ተግባር ላይ ናቸው። ይህንን ጉዳይ የNeuro-science ጠበብቱ እንደ ስነ ቋንቋ ጠበብቱ የልሳንን ቋንቋነት አይደለም ያጠኑት። ነገር ግን በፈቃደኛ ጸሎተኞች እና በልሳን ተናጋሪዎች ላይ በጸሎት ሂደት ውስጥ የሚከናወኑ የአንጎል ነርቭ እንቅስቃሴዎች እና ሞገዶችን ነው ያጠኑት። ይህንን ያደረጉት በንጽጽር በማየት ሲሆን ጥናቱ በካቶሊካውያን መነኮሳት ጸሎት፥ በምሥራቅ ሃይማኖቶች ጥሞና (meditation)፥ እና በልሳን ተናጋሪዎች ንግግር ላይ ነው። የግኝታቸው ውጤት ይህ ነው፤

ጸሎት የሚያደርግ ሰው ጸሎት በሚያደርግበት ጊዜ በአንጎሉ የተወሰነ ክፍል (lobe) የድርጊታዊ ምልክት እንቅስቃሴ ይነበባል። ተግባር በክንዋኔ ላይ መሆኑን አመልካች የእንቅስቃሴ ምልክት በአንጎል ነርቮች ይመዘገባል። ይህ ሳይንሳዊ ፍተሻ ወይም ምርምር በተደረገባቸው በካቶሊካውያን መነኮሳቱ ጸሎት ውስጥም፥ በምሥራቃውያኑ ጥሞና ውስጥም ይህ የአእምሮ እንቅስቃሴ መኖሩ ተረጋግጦአል። ይህ ማለት እየታሰበ የሚደረግ ጸሎት መኖሩን ያመለክታል። እየታሰበ፥ በእውቀት የሚደረግ ጸሎት።

በአንጻሩ ደግሞ፥ በምርምሩ ሂደት በልሳን ተናጋሪዎች ዘንድ አንዳች ነገር እየተደረገ ወይም እየሆነ እንዳለ የሚያስመዘግብ ምንም ምልክት የለም፤ ምንም የአንጎል ነርቮች ሥራና እንቅስቃሴ የለም። የተመዘገበው፥ '0 activity' ነው። ከጥናቶቹ መካከል የዛሬ 11 ዓመት ተደርጎ የተዘገበውን አንዱን ሊንክ አስተያየት መስጫው ውስጥ አስቀምጣለሁ።

ምናልባት ይህንን በ1ቆሮ. 14፥14-19 ካለው 'በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ጸልያል አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።' ከሚለው ጋር ማገናኘት ይቻል ይሆናል። የዚያ ክፍል ዋናው አሳብ ልሳን ስለሆነ በመንፈስ የሚለው በልሳን ማለት ነው ብለን ብንወስድ ከአሳቡ ፍሰት አያርቀንምና አፈታታችንም ስሑት አይሆንም። ያንን ክፍል ሲደመድም ግን ጳውሎስ፥ በማኅበር እልፍ ቃላት (10 ሺህ ማለት ነው) በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮ መናገር እንደሚወድድ መናገሩን፥ እንዲሁም በአእምሮ በማሰብ የሚናገረው ወይም የሚጸልየው ጉባኤውን እንደሚባርክና ጉባኤውም ለዚያ ብቻ አሜን ማለት እንደሚችል ተናግሮአል።

በመንፈስ መጸለይ እና የመንፈስ መቃተት በሌሎች መልእክቶች ውስጥም ስለተጻፈ ያንን ልሳን አንለውም፤ ነገሩ ራሱም ልሳን የተባለው ቃል ቢኖርም፥ ልሳን አልተባለም። ይህ የምርምሩ ልሳን ዓይነቱ ግን ምንም የአእምሮ ጸሎታዊ ተሳትፎ የሌለበት መሆኑን ራሳቸው የልሳን ተናጋሪዎቹም ይናገሩታል። ምርምሩም ያንኑ ያረጋግጣል። አእምሮአቸው disengaged ነው፤ ልክ እንደ መኪና ዜሮ ማርሽ። በልሳን መናገርም በልሳን መፀለይም ሁለቱም አዕምሮን ያካትታሉ። 'የለም እኔ ሸንበቆ ወይም መተላለፊያ ቧንቧ ብቻ ነኝ!' ካልተባለ በቀር።

ይህ ባዶነት በልሳን ልምምዶች ዘንድ ወይም በልሳን መናገርን በማግኘት ሂደት የሚለማመዱትና የሚያስደርጉት ነገር መሆኑን በተለይ የሚናገሩት ያውቁታል። በአንዳንድ የልሳን ልምምዶች በሚለማመዱባቸው ቦታዎች ላይ፥ በተለይም ልሳንን ስለመቀበል ከሆነ የሚጸለየው አዕምሮህን ዝጋ፤ ምንም አታስብ፤ በቋንቋህ አታስብ፤ በልሳን አስብ፤ አእምሮህን ባዶ አድርገው፤ ራስህን ልቀቀው፥ ለቅቀነው ተነዳን ተብሏልና ለቀኸው ተነዳ፥ ወዘተ፥ ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ አእምሮአችን እንዲያስብ፥ እንዲሁም እንደ ባለ አእምሮ እንድናስብ እንጂ ባዶ ስለማድረግ ፈጽሞም አያስተምረንም። ስናምን ወደ ውስጣችን ገብቶ ማደሪያው ባደረገን መንፈስ ቅዱስ የተሞላን፥ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሁሌ የምንኖር እንድንሆን እንጂ ባዶ ልንሆን ቃሉ አያስተምረንም።

ይህንን ጉዳይ ከሳይንስ አንጻር ማየቱ ፌዝ የሚመስላቸው አመናፋሾች መኖራቸው እሙን ነው። ራሴን ካነጸ ሌላው ትርፍ ነው የሚሉም አሉ። ግን ራስን ማነጽ ምንድር ነው? ልሳን ራስን የሚያንጸውስ እንዴት ነው?

## በልሳን መናገር ራስን ያንጻል? እንዴት?

ይህን ተከታታይ ጽሑፍ ስጀምር፥ 'እኔ ጴንጤ አይደለሁም!' በማለት እና ከዚያ ውስጥ ደግሞ ብዙዎችን ያስቆጣውና አብሮ አነጋጋሪ የሆነው ከሦስቱ ነጥቦች አንዱ የሆነው የልሳን ጉዳይ ነው። ሦስቱ ያልኳቸው ነጥቦች አንደኛው፡ ጴንጤ የሚለው ቃል ወይም ጴንጤቆስጣዊነት፥ ሁለተኛው፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚባለው ነገር፥ ሦስተኛው ከዚህ ከሁለተኛው ጋር የሚያያዘው ልሳን የሚባለው ነገር ናቸው።

ስጀምር ያልኩትን በማለት ልቀጥል። ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው። በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ የሚነገሩት እኔ የሰማኋቸው ልሳኖች ግን 99.9% ቋንቋ አይደሉም። ታዲያ ምንድር ናቸው?

1ኛ፥ ቋንቋ ሳይሆን በጥቂት ከራሳቸው ከተናጋሪዎቹ ቋንቋ በተውጣጡ ድምፆች የተሠራና ቃላት የሚመስሉ ድምጾች ስብስብ ነው። ድምጽ ነው ድምጽና ቋንቋ ይለያያሉ።

2ኛ፥ ልሳኑ የተገኘበትን መንገድ ስንፈትሸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጸጋ ሳይሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ሳይሆን፥ በሰዎች ግፊት፥ በጥበቃ፥ በልምምድ፥ በኩረጃ፥ በቡድን ስሜት ተሁኖ የሚናገሩት ነገር ነው።

3ኛ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ልሳን ጉባኤ ወይም ማህበር የሚታነጽበት ለማኅበር ግንባታ የሚውል ነገር ነው። ጴንጤቆስጣውያን የሚናገሩት ልሳን የሚባለው ነገር ግን ለማኅበር ግንባታ የማይውልና ለግል ፍጆታ ወይም መታነጽ የሚነገር ነገር ነው።

እነዚህን 3 ነጥቦች ይዘን ወደ ራስን ማነጽ ምንነት እንለፍ። በልሳን የሚናገር እራሱን እንደሚያነጽ ተጽፏል። አንዳንድ ስነ መለኮታውያን ራስን ማነጽ ጉባኤን ከማነጽ ጋር በንጽጽር የተፃፈ አሉታዊ አሳብ ነው የተላለፈው ይላሉ። 'ጉባኤ እንዲታነጽ የተሰጠውን ራሳችሁን አነጻችሁበት እኮ!' ማለቱ ነው ይላሉ። እነርሱ ራሳቸውም፥ 'ጉባኤን ለማነጽ የተሰጠውን የግል ማነጫ አደረጉት።' ይላሉ። ስጦታ ሁሉ የተሰጠው ጉባኤን ወይም ማኅበሩን ለማነጽ ነው። ይህ በግልጽ ተጽፎአል።

ጳውሎስ፥ 'በልሳን የሚናገር እራሱን ያንጻል' ብሏል። ይህ የተፃፈ እውነት ነው። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ተናጋሪው ራሱን የሚያንጸው እንዴት እንደሆነ አልተናገረም፤ አልጻፈም። ታዲያ ምን ማለት ነው ራስን ማነጽ?

ስጦታ ሁሉ ለአካል እነጻ ከተሰጠ፥ ትክክለኛው የራስ ማነጽ ነጥብ በእኔ መረዳት አንድ ሰው በልሳን በሚናገርበት ጊዜ፥ ያ ልሳን እውነተኛ ከሆነ የሚሰማና የሚደመጥ ነውና፥ የማይታወቅ ቋንቋ ከሆነ ደግሞ ከተረጎመ፥ እና ማህበሩ ከታነጸ፥ ተናጋሪውም ከማህበሩ ጋር አብሮ እንደ አካሉ ብልት መታነጹ ነው። አካሉን በማነጹ አብሮ ይታነጻል።

ልብ እንበል፤ ራስን ለማነጽ በመጀመሪያ፥ ያ ልሳን በእርግጥ ልሳን መሆን አለበት። ቋንቋ መሆን አለበት። ሰምተው የኮረጁትና የተለማመዱት ልሳን የልምምድና የኩረጃ ሰው ሠራሽ ልሳን እንጂ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ አይደለም። ይህንን ደጋግሜ ብዬዋለሁ። ስለዚህ ራስን ለማነጽ ማነጫው ራሱ ሲጀመርም እውነተኛ መሆን አለበት።

ይሁን እንጂ ጴንጤቆስጣውያን የልሳን ተናጋሪዎች ይህንን የጳውሎስን ቃል በመውሰድ ልሳናቸው በግል የሚታነጹበት መሆናቸውን በጥብቅ ይናገራሉ። መልሶቻቸውም እንደ ተለማማጆቹ ብዙ ናቸው። እነዚህን የራስ ማነጽ ልምምዶቻቸውን ቀጥሎ አስቀምጣቸዋለሁ፤ እንመልከታቸውና እንመዘናቸው።

ቀደም ሲል 99.9% የጴንጤቆስጣውያን ልሳኖች የልምምድ ናቸው ያልኩትን አሳብ፥ 'እንዴት ሪሰርች አደረግህ?' ያሉኝ አሉ። ባለፉት 40 ያህል ዓመታት የብዙዎችን ምስክርነቶች ሰምቻለሁ፤ አንብቤአለሁ፤ ራሴም ጠይቄአለሁ። የሁሉም አንድ ዓይነት ነው። ከአምስት ያነሱ በግላቸው ሲጸልዩ በልሳን እንደተናገሩ ቢሉም፥ ቀድሞ ሲሰሙና ሲጸለይላቸው በመቆየታቸው ያመሳስላቸዋል። እስካሁን ብዙ መቶዎችን ብሰማና ባናግርም አንድም በሚታወቅ ቋንቋ ወንጌልን ላላመኑ የተናገረ የለም።

ከብዙ መጽሐፎች መካከል Dr. Bill Hamon የሚባል ሰው የጻፈው Seventy Reasons For Speaking In Tongues የሚባል መጽሐፍም አንብቤአለሁ። ይህ ሰው 15 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብሎ፥ 30 የግል ጥቅሞች ብሎ፥ 25 የመንፈሳዊ አገልግሎት ብሎ ከፋፍሎ አስቀምጧል። መጽሐፉን ለብቻው ባሔስ ደስ ይለኝ ነበር፤ ግን በአጭር ቃል የዚህ ሰው ሥራ መጽሐፍ ቅዱስን መፍታት ሳይሆን ስነ መለኮታዊ ልጠጣ ወይም theological extrapolation ነው። ለምሳሌ፥ በልሳን መጸለይ የፈውስ ኃይል እንዲለቀቅ፥ የጸጋ ስጦታዎች እንዲጀመሩ (activate እንዲደረጉ)፥ ሪቫይቫል እንዲመጣ፥ መለኮታዊ ስልቶች እንዲከሰቱ ያደርጋል ይላል።

ቀጥሎ የማስቀምጣቸው 'መታነጫዎች' 99.9% ወደ ማለት ያመጣኝን ጴንጤቆስጣውያኑን እኔ ራሴ ስጠይቃቸው የመለሱልኝ ነው። እነዚህን ሰባት ወይም ስምንት ነጥቦች አስቀምጣቸዋለሁ።

አንደኛ፥ 'በልሳን በምናገርበት ጊዜ ረጅም ሰዓት እየተናገርኩ እየጸለይኩ መቆየት እችላለሁ።' የሚል ነው። ምን እንደሆነ የማያውቁት ጸሎት ይሁን ንግግር ወይም ሌላ ነገር ብዙ ሰዓት እየተናገሩ ረጅም ሰዓት መቆየት በረከት ተደርጎአል። ታሳቢ ማድረግ ያለብን ልሳኑ የልምምድና የኩረጃ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውም ነው። ስለ ምን ጉዳይ ጸለያችሁ? ሲባል ስለ ምን መሆኑ አይታወቅም።

በአዕምሯቸው በመጸለይ የማይቆዩትን መጠየቅ ያለብን አንድ ሰው በአእምሮ በፀሎት እየተጋደለ መቆየት መቻሉ ያ ዕድገት ነው ወይስ አይደለም? እየጸለየ እየጾመ፥ ስለ ማን ወይም ስለ ምን ጉዳይ እንደሚፀልይ እያወቀ በመጋደል መቆየቱ ያ ብስለት ነው? ወይ አይደለም? የትኛው ነው የጸሎት ትጋትና ተጋድሎ? ይህኛው ከባዱ መሆኑን ይናገራሉ። ረጅም ሰዓት መጸለይ የማይችሉት ለዚያ ነው። ከባዱ ለምን በአቋራጩ ተተካ? ቀላል ስለሆነ?

ሁለተኛው ራስን ያንፃል ብለው የሚሰጡት ምክንያት ስሜት ወለድ ንግግር ወይም ecstatic utterance ስለሆነ ደስታ ሊፈጥርላቸው መቻሉ ነው። ስሜት ወለድ ንግግር ብቻ ሳይሆን እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን፥ ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ከስሜታዊ ልምምዶች ጋር አብሮ የተሠራና የተቆራኘ መሆኑን ነው። ልምምዶቹ አንዳንዶቹ አርጅተው ሲከስሙ ሌሎች አዳዲሶች በቦታቸው ይወለዳሉ።

በስሜት ወለድ ልምምዶች ውስጥ ስሜታዊ ነገሮች መንፈሳዊ እየመሰሉና መንፈሳዊውን እየሸፈኑ ይኖራሉ፤ መንፈሳዊ ብስለትና እድገት ሳይኖር ይቀጥላል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከስሜት ወለድ ነገሮች ጋር ብዙ የስሕተት ትምህርቶችም ይመነጫሉ።

ሦስተኛው ልሳንና መንፈስ ቅዱስ በመቆራኘታቸው በልሳን ሲናገሩ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ወይም አብሮአቸው እንዳለ ስለሚመስላቸው ማረጋገጫ ስለሚሆንላቸው ነው ይላሉ።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን መገኘቱ የሚሰማቸው በልሳን ሲናገሩ ከሆነ ካልተናገሩት አይሰማቸውም ማለት ነው። አብሮን መሆኑ የተፃፈልንና ያነበብነው አይደለም፤ ወይም ያንን ማወቃችን ብቻውን በቂ አይደለምና ድጋፍ በቃሉ ላይ መጨመር አለብን ወይም ቃሉን በስሜታዊ ነገር ወይም ልምምድ መደገፍ አለብን ማለት ነው።

አራተኛው፥ በልሳን መናገር ራስን ማነጽ ነው የሚሉት በልሳን ሲናገሩ ሰይጣንን እያደናገሩት እንደሆነ ስለተነገራቸው ነው። 'በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል፤' (1ቆሮ. 14፥2) የሚለውን በልሳን ሲናገሩ ምስጢር እየተናገሩ ሰይጣንን እያደናገሩት እንደሆነና ምስጢር መናገር ማለት ሰይጣንን ማደናገር ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን ሰይጣንን እያደናገሩት ከሆኑ በልሳን የማይናገር ሰው የሰይጣንን አሰራር መቃወም አይችልም የሰይጣን አሰራር ሰለባ ሆኖ ይኖራል ማለት ነውና፥ ሁሉም ደግሞ በልሳን እንደማይናገሩም ተጽፎአልና፥ ሁለት ዓይነት የክርስትና መደብ ሊኖር ነው። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አይደለም።

የልሳን ተናጋሪው የሚናገረው ለእግዚአብሔር ከሆነና፥ ያውም ደግሞ የሚናገረው ምስጢር ከሆነ ጉባኤው መስማት አለበት ወይ? ምስጢር ከሆነ የጉባኤ አይደለም ማለት ነው። የጉባኤ ካልሆነም የማይተረጎም ነው፤ ካልተተረጎመ ወይም የሚተረጎም ካልሆነና የጉባኤ ቢመስላቸው እንኳ፥ 'የሚተረጉም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር።' 1ቆሮ. 14፥28 አይደለም ወይ የተባለው? ምስጢር ነው ማለት እና አሰምቶ ለጉባኤ መናገር እርስ በርስ ተፈራራሽ ድርጊቶች አይደሉም ወይ? ናቸው እኮ!

አምስተኛው፥ በሮሜ 8፥26 የተጻፈውን በመንፈስ መቃተት የሚለውን ከልሳን ጋር አመሳስለው መንፈስ ቅዱስ በልሳናቸው እየማለደ')፥ እየለመነ፥ ለሌሎች እየጸለየ እንደሆነ ስለሚመስላቸው ነው። ቃሉ የሚለው ይህ ነው፤ 'እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤' ይህንን የማይነገር መቃተት ነው በልሳን ከመናገር ጋር የሚያመሳስሉት።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን ሦስት ነገሮች አሉ። አንዱ፥ ቃታቹና በልሳን ተናጋሪው የተለያዩ ባለቤቶች መሆናቸው ነው። ቃታቹ መንፈስ ነው፤ ሮሜ 8 የመንፈስ ቅዱስ ምዕራፍ መባል የሚችል ምዕራፍ ነው። በልሳን ተናጋሪው ደግሞ ተናጋሪው ሰው ነው። ሁለተኛው ልብ ማለት ያለብን፥ ይህ መቃተት መቃተት ነው፤ በቃላት የተሠራ ነገር አይደለም። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን አንድ ሌላ ቦታ ተጠቅሶአል፤ ያ ጥቅስ ምንነቱን ይበልጥ ይነግረናል፤ ያ ቃል በሐዋ. 7፥34 የሚገኘው የእስራኤል በግብጽ መቃተት ነው። ሦስተኛው ልብ ማለት ያለብን፥ መቃተት የሚለውን ቃል ጳውሎስ የተጠቀመው በልሳን መናገር የሚለው ቃል ጠፍቶት ወይም ያንን ቃል ረስቶት አይደለም። ሁለቱንም መልእክቶች የጻፈው ጳውሎስ በዚያው መንፈስ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ መሆኑን ለአፍታም መርሳት የለብንም። ቃሉ መቃተት ነው። ስለዚህ የመንፈስ መቃተት በልሳን መናገር አይደለም።

ስድስተኛው፥ በልሳን መናገራቸው የመንፈሳዊ ልምምድ ጣራ ተደርጎ ስለሚቆጠር ያንን መለማመዳቸዉ የመንፈሳዊነት ማረጋገጫ ስለሚመስላቸው ነው። በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ በመንፈስ የመጠመቅ ወይም የመሞላት ብቸኛ ምልክት ልሳን ነው ተብሎ ስለተማሩ፥ ያ ልሳን እስኪገኝ ድረስ ብዙ ይጠበቃል፤ ሳምንታትም ወራትም ዓመታት ይጠበቃል። ያ ሲገኝ የመጨረሻው ጣራ እንደተነካ ይቆጠራል። ከዚያ በላይ ያለ እስከማይመስል ድረስ እዚያ መቸከል ይሆናል። ስለዚህ ልሳን የዚያ ብቃት ባንዲራ ሆኖ ይውለበለባል። ይህ በተለይ በይፋ ጴንጤቆስጣውያን ባልሆኑት እንደ ቃለ ሕይወት ወይም ሌሎች አብያተ እምነቶች ውስጥ የእዩልኝ ስሙልኝ መታወቂያ ተደርጎ መመጻደቂያ መሆኑ ከታየ ከርሟል።

ልሳን በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ የመስፈሪያው ጣራ ብቻ ሳይሆን፥ የሁሉም ነገር አንድና ብቸኛ ፍቱን መፍትሔ ሆኖ ይታያል። ልክ የአገራችን የባሕል መድኃኒተኞች፥ 'ለቋቁቻና ለጋብቻ፥ ለራስ ምታትና ለቁርጥማት፥ ለስጋትና ለውጋት፥ . . .' እያሉ እንደሚሸጧት የቀበሪቾና የአዝሙድ ድብልቅ አንዲት ብልቃጥ፥ ልሳንም ለሁሉም 'ሁሉም በአንድ all-in-one' መፍትሔ ሆኖ ተወስዶአል።

ሰባተኛው፥ ራስን ማነጽ ነው የሚሉት በሚመሳሰሏቸው ወይም በሚመስሏቸው ሰዎች መካከል መገኘት እና የልምድ መመሳሰል ነው። ይህ በብጤዎቻቸው መካከል መገኘት ብጤያዊ እቅፍ ውስጥ የመገኘት ስሜት (sense of belonging) ይሰጣቸዋል። ይህ የስነ ልቡና እና የመንፈሳዊ ዕድገት ጉዳይ ነው። መሳሰል ጥሩ ቢሆንም መመሳሰል በራሱ ብቻውን ውበትም ማደጊያም አይደለም። እንዲያውም በተቃራኒው፥ ሙሉ በሙሉ ከማንመሳሰላቸው ሰዎች ጋር መዋል ማደር ይሞርደናል፤ ስለታም ያደርገናል። ይህንን ሰሞኑን የምንነጋገርበትን ጉዳይ ሳነሣ በብዙዎች ዘንድ ድንጋጤያዊ አጸፋ የፈጠረው ከዚህ የተነሣም ነው።

ስምንተኛው የመታነጫ መንገድ የሚሉት አንዳንዶቹ ልሳናቸው በእርግጥ ቋንቋ መሆኑን ከልብ ስለሚያምኑ ነው። እንዴት ባለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ እንዳገኙት እያወቁም እንኳ፥ ከልብ አምነው ተቀብለውታል። ካነጋገርኳቸው ወንድሞች መካከል አንዱ የእርሱ ቋንቋ ስፓኒሽ እንደሆነ፥ ሌላው የሩስኪ የገጠሬ ዘዬ ወይም ቀበሊኛ እንደሆነ፥ ሌላው በእብራይስጥ እንደሚናገር ነግረውኛል። ሌሎችም ብዙ አሉ። ሲጸልዩ ቀርጸው እንዲልኩልኝ ስጠይቅ እንደ ድፍረት ይቆጥሩታል። ያ ብቻም አይደለም በአካባቢያቸው አማርኛ የማያውቁ ላቲኖች ወይም ሩስኪዎች ወይም አይሁድ አሉ ወይ? የሉም።

ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ የዛሬ 125 ዓመት ሲጀመር የተናገሩት ቋንቋ ቻይንኛ ነው ብለውና ተብለው ወደ ሩቅ ምሥራቅ ስለሄዱት ሰዎች አይተናል። መቼም፥ 'ማየት ወይም መስማት ማመን ነው' ቢባልም፥ እኔ አልልም፥ በዚህ የሚድያ ዘመን፥ በተለይም ባለፉት 20 ያህል የማኅበራዊ ሚድያ ዓመታት የተቀረጸ እውነተኛ ቋንቋ ግን እንዴት ይታጣል?

የመላእክት ቋንቋ ጉዳይስ? መላእክት ቋንቋ ሳይኖራቸው አይቀርም፤ ልክ አዳም ከቋንቋ ጋር እንደተፈጠረ። የተጻፈልን ግን መላእክት በሰዎች ቋንቋ ሲናገሩ ነው። ጌዴዎንን ወይም ዳንኤልን፥ ማርያምን ወይም ዮሐንስን በመልአክኛ አላናገሯቸውም። ጳውሎስ፥ 'በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።' 1ቆሮ. 13፥1 ሲል ጳውሎስ በመላእክት ቋንቋ ማለቱ በዐውዱ ካየነው እና ብዙ ስነ መለኮታውያን እንደሚያስተምሩት አጋኖአዊ ወይም ግነታዊ ቋንቋ መጠቀሙ መሆኑን ያሰምሩበታል። ፍቅር ከሌለኝ እንኳን በሰው በመላእክትም ቋንቋ ብናገር ከንቱ ነኝ ለማለት። ጴንጤቆስጣውያን ከሆኑት መካከል የሚናገሩት ቋንቋ የመላእክት ነው ብለው እርግጠኛ መሆን ባይችሉም፥ እርግጠኛ ቢሆኑ እንኳ፥ ጉባኤው የመላእክት ሳይሆን የሰዎች ነውና ይህ ቋንቋ የማኅበሩ ሳይሆን የመላእክት መሆኑ የግዴታ መስፈርትን ያልፋል?

እንግዲህ፥ 'በልሳን የሚናገር እራሱን ያንጻል' የሚለው ራስን ማነጹ ጉባኤውን ከማነጹ ጋር በጋራ መታነጹ ካልሆነ፥ ከነዚህ ከዘረዘርኳቸው ሰባት ነጥቦች በጥቂቱ፥ ወይም በሁሉም፥ ወይም እዚህ ባልተጠቀሱ የግል ልምምዶቻቸው ሊሆን ይችላል። ባለፈው ክፍል ቢል ሐመን 70 ምክንያቶችን እንደዘረዘረው ማለት ነው። ግን ትልቅ ጥያቄ አለ፤ ጥያቄው ችግሩም ነው፤ ማንን ማነጽ?

'ራስን ማነጽ' ትልቁና ዋናው ጉዳይ ጉባኤን ሳይሆን ራስን ማነጽ መሆኑን ማወቅ ነው። ልሳን ለጉባኤ የማይጠቅም ወይም የማይተረጎም ከሆነ በግልጽ እንደተጻፈው፥ 'በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር' ነው የተባለው። ይህ

የተጻፈው መከበር የለበትም? አለበት። በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ ግን ይህ ትእዛዝ ወይ መኖሩም አይታወቅም፤ ወይም ታውቆም ይናቃል።

እንግዲህ ራስን ለማነጽ በመጀመሪያ ስጦታው ስጦታ መሆን አለበት። የልምምድ እና የኩረጃ ሰው-ሠራሽ ልሳን ሳይሆን እውነተኛው የጸጋ ስጦታ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው ራስንም ሆነ አካሉን የሚያንጸው። ተለማምደውና ኮርጀው የሚናገሩት ልሳን ጉባኤውንም ሆነ ራስን አያንጽም፤ ሲጀመርም የጸጋ ስጦታ አይደለማ! እውነተኛ ከሆነ ላላመኑ ምልክት ነውና፥ 'እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም።' እንደሚል 1ቆሮ. 14፥22 የማያምኑት የሚሰሙት ቋንቋ መሆን አለበት። ካልሆነ ደግሞ በቁጥር 27 እንደተጻፈው፥ ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም። ያ ከልሆነ ጉባኤ አይታነጽም።

የጸጋ ስጦታ የተሰጠው ከሁሉ በፊት ለእግዚአብሔር ክብር ነው። ቀጥሎም ለአካል እነጻ ነው። በየትኛውም ስጦታ ተግባራዊነት መጠየቅ ያለብን፥ 'እኔ ተጠቀምኩ ታነጽኩ ወይ?' ሳይሆን፥ 'አካሉ ተገነባ ወይ?' ብለን ነው። አንተ ብልት ብቻ ነህ፤ አካል ሲታነጽ ትታነጻለህ፤ አንተ ብቻህን ስትታነጽ ግን አካል ታነጸ ማለት አይደለም።

## መደምደሚያ

በዚህ ጉዳይ፥ 'እኔ ጴንጤ አይደለሁም' የሚለውንና በተለይም ስለ ልሳን መጻፍ ከጀመርኩ በኋላ ጤናማ ሙግት የጻፉ አሉ። በውስጥ መስመር የተጻጻፍን እና ደውለው ጊዜ ወስደን ያወራን አሉ። ልዩ ልዩ ዓይነት ሰዎችም እየተቃወሙኝ ጽፈዋል፤ ተናግረዋል፤ በግልጽ የተቃወሙኝን አድናቂ ነኝ፤ ግልጽ ስለሆኑ። ያላልኩትን ብለው ወይም ያልኩትን ቆልምመው የተናገሩና ስም ሳይጠቅሱ አሁንም ድረስ የሚጽፉ አሽሙረኞችም አሉ። እነዚህ የተናቀ ሥራ ሠሪዎች ናቸው። እኔ በጣም ግልጽ ነኝ። የጻፍኩትም ግልጽ ነው።

ከተቃወሙኝ አንዳንዶቹ የምካቴ ጴንጤቆስጣዊነት ሰዎች ናቸው። ከቃሉ ይልቅ ከታሪክም ከልምድም እያዋጡ ጴንጤቆስጣዊነትን ከኖረው በላይ ሊያኖሩት ታትረዋል። አንዳንዶቹ ከልባቸው ልሳን ተናጋሪ ጴንጤቆስጣውያን ናቸው። ይህን ልምምዳቸውን ግን ከምንጬ እንዳልሆነ እያወቁም፥ ወይም የሚያውቁ ሲነግሯቸው ራሳቸውን በመደለል መካድም መቀበልም፥ ልምምዱንም መዋጥም መትፋትም ያልቻሉ ናቸው። ምንጬንም እያወቁ።

ምንጭ ስል አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ። እኤአ በ1903 ዐፄ ምኒልክ ከአሜሪካው መልእክተኛ Robert Peet Skinner ጋር ሲያወጉ፥ 'እናንተ አገር ሞት የተበየነበት ወንጀለኛ እንዴት ነው የሚገደለው?' ይሉታል። Skinnerም ስለ ኤሌክትሪክ ወንበርና የቅጣቱ መንገድ ያስረዳቸዋል። 'አይይይይ! እኛ'ኮ ገልቱዎች ነን! በሰይፍ አንገት ቆርጠን ወይ በእንጨት ሰቅለን ነው የምንገድለው። በል እንደሄድክ ይህን ያልከውን ወንበር እዘዝና ላክልኝ።' ይሉታል። ወንበሩም ተላከ፤ ደረሰ፤ ታየ። ለመፈተሽ ሲሉ አንድ ነገር ይጎድለዋል። ለካስ ኢትዮጵያ ውስጥ ኤሌክትሪክ የለም። ወንበሩ ሥራ ከሚፈታ ብለው አንዱን የራሳቸው መቀመጫ አደረጉትና ሌላውን ለአባ ይትረፍ (ራስ አባተ ቧያለው) ላኩላቸው። ወንበሩ አለ፤ ኃይሉ የለም። በኩረጃ ልሳን ዘንድም ይህ ነው የሚሆነው። አንዳንዶቹ ከልባቸው ልሳን ተናጋሪ ጴንጤቆስጣውያን ናቸው ብያለሁ። ግን ከምንጩ ያልሆነ ሰው-ሠራሽ ልምምድና ኩረጃ መሆኑን ልባቸው እያወቀም ራሳቸውን ይደልላሉ። ወንበሩ አለ፤ ኃይሉ የለም።

አንዳንዶቹ ድንጋይ ረግጠው የተቃወሙኝ እውነቱን እያወቁ ለጥቅም እና ላለማስቀየም፥ የአገልግሎት ግብዣ ላለማጣት፥ መጽሐፍ ሲያሳትሙ ለማስመረቅና ለመሸጥ ወደዚያ የሚያደርሳቸውን ድልድይ ላለመስበር የተጋጋጡ፥ ከቃሉ ጠቅሰው ሙግት ሳያቀርቡ ነጥብ ለማስቆጠር ብቻ ማሊያ ለብሰው ዱብ ዱብ ያሉ ናቸው።

ሌሎች፥ የሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት ደጋፊዎች እና ካዳሚዎች ናቸው። እነዚህ ለጉዳዩ ግድ ኖሮአቸው ሳይሆን ሐሰተኞቹን የምንናገራቸውን ሰዎች የሚቃወሙ በመሆናቸው፥ በዚህኛው ጉዳይ ደግሞ ሌሎች ተቃዋሚዎችም ስለመጡላቸው አጋጣሚውን የድንጋይ መወርወሪያና የውርወራ መለማመጃ ያደረጉ ናቸው። ለነዚህ ከላይ ላልኳቸው ዓይነቶች ሁሉ ናሙና ስሞችን መጥቀስ እችላለሁ። ነጥቡ ግን ጉዳዩ እንጂ ሰዎቹ አይደሉም።

## ከተናገርኩት ዋናው ነገር . . .

ጴንጤቆስጣዊው እንቅስቃሴ የ125 ዓመት ዕድሜ እንቅስቃሴ ነው። የልሳን ልምምድ ከጴንጤቆስጤ ቀን ወይም ከሐዋርያት በኋላ ጠፍቶ በ1901 የተገኘ ልምምድ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ ከችግርና ከውግዘት ጋር ኖሮ ያውቃል። ያም አካሉን የሚያንጽ ሳይሆን እንግዳ ልምምድ እየሆነ በመከሰቱ ነው። ይህንን ታሪካዊ ገጽታ በመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች ምዕራፍ 3 ጽፌዋለሁ። ብዙዎች ይህንን ቢዘልሉትም፥ ራሱ 1ቆሮ. 14 የችግር ምላሽ ጽሑፍ መሆኑ መረሳት

የለበትም። ከ1901 በኋላ ይህንን ልምምድ ያገነነው ልምምዱ ተቀባይ ማግኘቱና በስፋት መናኘቱ ነው። ተቀባይነቱና መናኘቱ ግን ሰውኛ ልምምዳዊ ጅማሬውን አያደበዝዘውም።

በልሳን መናገር ከጸጋ ስጦታዎች አንዱ ብቻ ነው። ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወይም የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት አይደለም። ልሳን ቋንቋ ነው፤ በተወሰኑ ስሜት-ወለድ ድምጾች ወይም ecstatic utterances የተሠራ ቋንቋ መሳይ ነገር አይደለም። ልሳን ተለማምደው እና ኮርጀው ሊናገሩት የሚችሉት ነገር ነው፤ ያ ታዲያ ቋንቋ አይደለም፤ ቋንቋ ሊባልም አይችልም። ይልቁንም ያ ኬላ-ሰበር ፎርጅድ ነገር እንጂ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታ አይደለም።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በክርስቶስ አምነን ስንድን አንዴ የሚፈጸም የክርስቶስ አካል ብልት የሚያደርገን ግንኙነት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ደግሞ የማያቋርጥ፥ ቀጣይ እና ተደጋጋሚ የሆነ፥ በሙላቱ ሁኔታ ውስጥ የምንኖርበት፥ መንፈስ ቅዱስ አማኝን የሚቆጣጠርበትና በአገልግሎት የሚያጎለብትበት ጥብቅ ግንኙነት ነው። ልሳንና የመንፈስ ቅዱስ ሙላትም ግንኙነት የላቸውም። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ይታወቃ፤ በልሳኑ ሳይሆን በፍሬው ይታወቃል። ልሳን የጸጋ ስጦታ ነው እንጂ ምልክት አይደለም። ምልክት ከሆነ ለማያምኑ ሰዎች የሚሆን ምልክት ነው፤ እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም። (1ቆሮ. 14፥22) ይህ ከመጀመሪያውም እውነት ነው።

ለማያምኑ እንዴት ምልክት ይሆናል? በመጀመሪያ ስለ ልሳን (ባዕድ ልሳን ተብሎ) ትንቢት በተነገረበት በኢሳ. 28፥11-12 ስለ አለማመን የተነገረ ትንቢት ነው። በሐዋ. 2 በግልጽ እንደሚታየው ላላመኑ አይሁድ በየገዛ ቋንቋቸው የተነገረ መልእክት ነው። በሐዋ. 10 የተነገረው ከሐዋ. 2 ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ያ ቋንቋም ቋንቋ ነው። በሐዋ. 19ም ይህንን የተከተለ መሆኑን መገመት እንችላለን። በ1ቆሮ. 14፥22 በግልጽ ለማያምኑ ምልክት መሆኑ ከተጻፈ ይህ ልሳን የማያምኑቱ ሰዎች የሚገባቸው የራሳቸው ቋንቋ እንደሚሆን ማሰብ ጤናማው አፈታት ነው። ያ ቋንቋ ካልሆነም ቋንቋ ነውና ትርጉም ያሻዋል። ለዚያም፥ ምንም እንኳ በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ ባይከበርም፥ ግልጽ ደንብ ተጽፎአል።

በልሳኖች መናገር ትኩረቱ ላላመኑት ምልክትና እንዲሁም እንደ ሌሎች ስጦታዎች ሁሉ ደግሞ ማኅበረ ምዕመናንን ማነጽ ነው። ላላመኑ ምልክት የሚሆነው በነዚያ በማያምኑት ሰዎች ቋንቋ የሚነገር ስለሆነ ነው። ያኔ የሚነገረው ነገር መነገሩ ብቻ ሳይሆን እነርሱን የተመለከተ መሆኑም ይታወቃቸዋል። ልሳን ለማያምኑ ምልክት ነው። በሐዋ. 2 የሆነው ይህ ነው ያላመኑት ናቸው በቋንቋቸው ሲነገር ሰምተው

የዳኑትና የተጠመቁት። የልሳን ለማያምኑ ምልክትነት በጳውሎስ መልእክትም አልተለወጠም። *እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።* 1ቆሮ. 14፥22።

ሲጀመርም በትንቢት የተነገረው ልሳን ለማያምኑ እስራኤላውያን ነበረ። 1ቆሮ. 14፥21 የተወሰደው ከኢሳ. 28፥11-12 ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፤ *በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል፤ እርሱም፦ ዕረፍት ይህች ናት፥ የደከመውን አሳርፉ፤ ይህችም ማረፊያ ናት አላቸው፤ እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ።* ነቢያት ሲነግሯቸው ሲያስጠነቅቋቸው እንቢ ባሉት አይሁድ ላይ በባዕድ ልሳን በማያውቁት ቋንቋ የሚናገሯቸውን አሦራውያንን እና ባቢሎናውያንን ላከባቸው። በኢሳይያስ ዘመን ነበር የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ፈርሶ ወደ አሦር የተጋዘው። ከዘመኑ 100 ዓመት ሳይሞላ ደግሞ ይሁዳ ወደ ባቢሎን ተጋዙ። ባዕድ ልሳን አላመኑምና ለማያምኑ የአለማመናቸው ምልክት ነበረ። ጳውሎስ ይህንን ትንቢት ከጠቀሰ በኋላ ነው ልሳን ለማያምኑ ምልክት መሆኑን የጻፈው።

ልሳን ሲነገር የማያምኑ ከመጡ ምልክት ሊሆናቸውና ወደ መዳን የሚያመጣቸውን እውነት እንዲጨብጡ ሊረዳቸው የተገባ ስጦታ ነው። ይህ የሚሆነው ልሳን ይህንን የምልክትነት ሚና ከተጫወተ ነው። ይህ ካልሆነና፥ እንዲያውም የዚህ ተቃራኒ ከሆነስ? የማያምኑ ሰዎች ልሳንን ሲሰሙ ወደ መዳን ሳይሆን ከመዳን ወደ መራቅ ነው የሚሄዱት። በጳውሎስ ቋንቋ፥ 'አብደዋል!' ነው የሚሉት።

ልሳን ቋንቋ ቢሆንም እንደ መነሻው እንደ ሐዋ. 2 ያለው ቋንቋ ሲነገር ወይም በሰሚዎቹ ሲመሰከር ተደምጦ አያውቅም። እኔም ሰምቼ አላውቅም። ያንን ነው 99.9% ያልኩት። ይህ የ99.9% ጉዳይ ብዙ የውሸትና የግምት ነገርም ያስባለ ነውና በመጀመሪያ በFeb. 20 የጻፍኩትን እዚህ ልድገመው፤

"እኔ ከሰማሁዋቸው የልሳን ንግግሮች ውስጥ 99.9% የሚሆኑት የልምምድ ልሳኖች ናቸው። ቋንቋ ያልሆነ ልሳን የቋንቋ መስፈርትን የማያሟላ ልሳን ማለት ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ዛሬ አንድም በሚታወቅ ምድራዊ ቋንቋ የተናገረ፥ ሰውየው የማያውቀው እና ሰሚዎቹ በሚያውቁት የራሳቸው ቋንቋ ተናግሮ ክርስቶስን እንዲያውቁ ያደረጋቸው ሰው ገጥሞኝም ሰምቼውም አላውቅም።"

ይህንን ነው ያልኩት። ይህንን አሁንም እደግመዋለሁ። አንዳንዶች ምን እስታቲስቲክስ ሠርተህ ነው? Sample sizeህ ምንድር ነው?Methodologyህስ? ወዘተ፥ ብለዋል። ይህ የማስተርስ ወረቀት ግብዓት አይደለምና የነሱን ፍላጎት አሟይ ሪሰርች ሳይሆን፥ 'እኔ ከሰማሁዋቸው የልሳን ንግግሮች ውስጥ' እንደማለቴ መጠን በመቶዎች የሚቆጠሩ

ሰዎችን ባለፉት 40 ያህል ዓመታት ጠይቄም ሰምቼም ያልኩት ነው። መቶዎች ስል #ብዙ_መቶዎች ናቸው። ሪሰርች ብሠራና questionnaire ብበትንም ያን ያህል ቁጥር የምሠራ አይመስለኝም። ዋናው ነጥብ እኔን ገጥሞኝ አያውቅም። ይህንን ማውደቂያው ቀላል መልስ፥ 'አንተን ገጥሞህ አይወቅ እንጂ እኔን ገጥሞኛል። ይኸው ማስረጃው።' መሆን ይችል ነበር። የሆነው ግን ሌላ ነው።

ልሳን የጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ መታወቂያና ልብና ሳንባ ነውና፥ ልሳንና ጴንጤቆስጣዊነትም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸውና፥ ልሳንን መንካት ማስቆጣቱም ማስተማሩም ሦስት ሳምንት ጨርሶ አራተኛውን ያዘ። ይህንን ጉዳይ በስሜት መንጨርጨር የጻፉብኝ፥ የተፉብኝ፥ በውስጥ መስመር የሰደቡኝ፥ ሳያገኙኝ የደበደቡኝ ብዙ ናቸው። ከስነ መለኮት አንጻር መሳሳቴን ሊያሳዩ የሞከሩ ሁለት አሳቦችን ላንሣ።

አንዱ የdescriptive እና prescriptive ጽሑፋት ሚና ጉዳይ ነው። ታሪካውያን እና ትእዛዛውያን ጽሑፋት ማለት ነው። አንዱ የሐዋርያት ሥራን ከ1ቆሮንቶስ ለመነጠል በግልጽ ሉቃሳዊና ጳውሎሳዊ ብሎታል። ጳውሎስና ሉቃስ አብረው ያገለገሉና፥ ሉቃስም የሰፊው የጳውሎስ አገልግሎት ዘጋቢ መሆኑን ያስተዋለው አይመስልም። ከታሪካውያን ጽሑፋት ትምህርቶችን እናገኛለን፤ በታሪኮች ውስጥ ትእዛዛትና ትምህርቶች ይገኛሉ። እነዚህ ትምህርቶች በታሪኮች ውስጥ ይገኙ እንጂ ድርጊቶች አይደሉምና ለይተን እናያቸዋለን። አስተምህሮ ይቀረጻል፤ ድርጊት ግን አይኮረጅም። ከታሪካውያን ጽሑፋት ልምድን እንቀስማለን፤ ማንነትን እናውቃለን፤ ሆኖም ታሪኮች ናቸውና ድርጊቶችን ግን አንደግምም።

ወደ ጴንጤቆስጣዊነት እንቅስቃሴ ጅማሬ ስንሄድ ያየነው ከታሪካዊ ጽሑፋት (descriptive) ጋር የተጋመደውን ልምምዳዊነት እና ከትእዛዛውያን (prescriptive) ምንባባት ጋር የሆነውን መላቀቅ ስነ መለኮታዊ ቅርቃር ነው። ስነ መለኮት ሲወሳ ታሪካዊ ጽሑፋት ትእዛዛዊ ጽሑፋት ላይ አይጎለብቱም። በማርቆስ እባቦችን ስለመያዝ ተጽፏል፤ ጳውሎስም እባብ ከእጁ አራግፏል ብለው እየያዙ ተነድፈው የሞቱ አሉ። በውኃ ላይ ለመሄድ ሞክረው የተወሰዱ አሉ። ስንፍና በየፈርጁ እንዲህም ታይቷል።

ሌላው የanachronism (ወይም anachronistic presumption ብለው ይሻላል) ጉዳይ ነው። ቃሉ ሰፊ ትርጉም አለው፤ እዚህ ሊሉ የፈለጉት ግን ከኋለኛው በመነሣት የቀደመውን ምስል ለመከሰት እንደሞከርኩ በማመልከት፥ 'አሁን ካለው ትርምስ እና የተበላሸ ልምምድ በመነሣት የቀደመውን ጤነኛውን አፈር ከድቤ ከተትከው!' የሚል ነው። ትርምስ እና የተበላሸ ሰው-ሠራሽ ልምምድ መኖሩን ማመናቸውን አደንቃለሁ። ግን ከአሁኑ ተነሥቼ የትኛውን ልሳን ነው ተበላሸ ያልኩት? የሐዋርያት ሥራውን ነው?

አይደለም። የ1ኛ ቆሮንቶሱን ነው? አይደለም። ታዲያ የትኛውን ነው? ለዚህ ነው፥ anachronism ሳይሆን anachronistic presumption ብለው ይሻላል ያልኩት። ሐዋ. 2 እና 1ቆሮ. 14 እንዴት ከአሁኑ በመነሣት እንዴት ውድቅ ሊደረግ ይታሰባል? በሐዋ. 2 ሰዎቹ ቋንቋቸውን ሰሙት እኮ! በቆሮንቶስ ከሥርዓት አልባነት ጋር እውነተኛ ስጦታ መኖሩ እኮ ግልጽ ነው። ያውም ሐዋርያዊ ማኅተም የታተመበት።

የጴንጤቆስጣዊነት እንቅስቃሴ መሠረት ሐዋ. 2 ሳይሆን 1901 (ቶፒካ) እና 1906 (አዙሳ ጎዳና ሎስ አንጀለስ) ነው። ያንን በanachronism እኔ ያጠለሸሁት ሳልሆን የዘመናቸው ሰዎችና ፓርሃምን ጨምሮ አብረውት የነበሩ ሰዎችም እብደት ያሉት ጉዳይ ነው። 'የሰይጣን የመጨረሻው ትውከት' እስከመባልም የደረሰ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቀለም የተቀባ ሰውኛ ልምምድ ነበረ። ከዚያ በፊት ከነበሩት መካከል እንደ ሞንታናውያን ወይም ኧርቪንጋውያን እንቅስቃሴ ያሉትም በዚያው ዘመንም የተወገዙ ነበሩ። 1ቆሮ. 14 ራሱም እኮ በዋናነት የጥያቄዎች መልሶች እና የወቀሳ መልእክት ነው። የምዕራፍ 14 ወቀሳ ደግሞ ሥርዓተ አልበኝነት ነው። Anachronism የሚሉ ሰዎች የተወቀሰውና ስሕተት ነው የተባለው ምን መሆኑን አውቀው ለመቀበል የማይፈልጉ ሰዎች ናቸው።

ያልኩትን በመድገም እደመድማለሁ። እኔ ጴንጤ አይደለሁም። እኔ ወንጌላዊ አማኝ ነኝ። በዳንኩ ቀን በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቅሁ ዳግም ውሉድ ክርስቲያን ነኝ። ልሳንን በተመለከተ፥ እኔ ከሰማኋቸው የልሳን ንግግሮች ውስጥ 99.9% የሚሆኑት የልምምድ እና የኩረጃ ልሳኖች ናቸው። በሐዋ. 2 እንደተጻፈው ያለ ተናጋሪው የማያውቀው እና ሰሚዎቹ በሚያውቁት በራሳቸው ቋንቋ ተናግሮ ክርስቶስን እንዲያውቁ ያደረጋቸው ሰው ገጥሞኝም፥ ሰምቼውም አላውቅም። ባይገጥመኝም፥ ወይም ፎርጅድ ስጦታ አየሩን ቢሞላውም፥ 'የለም' ወይም 'ተቋርጧል' አልልም።

ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

ዘላለም መንግሥቱ።

© 2026